አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3556 | ቅዳሜ ጥር 9 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር







## ጥምቀት እና ሸሮ ሜዳ




4

ፎቶ- ከፋይል

በኮሪደር ልማቱ ምቹ የንግድ ስርዓት የተላበሰው ሸሮ ሜዳ የገበያ ማዕከል

## አዕምሮን የሚያድሱ መናፈሻዎች



12

ፎቶ- በገነት ወንድሙ

የአምባሳደር ፓርክ ውስጣዊ ገጽታ በከፊል

## የአህጉራዊው ውድድር አይረሴ ክስተቶች

20



ፎቶ- ከገፀ ድር

35ኛው የአፍሪካ ዋንጫ በታሪክ ከፍተኛ የተመልካች ቁጥር የተመዘገበበት ውድድር በመሆን አዲስ ታሪክ ፅፏል

# ከብክለት ወደ ውበት

**“በወንዝ ዳርቻ ልማቱ የከተማዋ ወንዞች ከቆሻሻ ጸድተው ለዓይን የሚማርኩ የመዝናኛ ስፍራዎች ሆነዋል”**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ**

3



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በአዲስ አበባ እየተከናወኑ ያሉ የወንዝ ዳርቻ ልማቶችን ተዘዋውረው በመጎብኘት ገለጻ ሰጥተዋል

# የኢትዮጵያ ምልክት ከፍታ

**“አውሮፕላን ማረፊያው አዲስ አበባ በኮንፈረንስ ቱሪዝም ተመራጭና ተጠቃሚ የምትሆንበትን ዕድል ይጨምራል”**

**የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር)**

**በስንታየሁ ምትኩ**

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በዓባይ ውሃ በፍትሐዊነት የመጠቀም የዘመናት ጥያቄን መልስ የሰጠውን ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጉባ ላይ ሲመርቁ ሌላ ብስራት ይዘው ብቅ ብለው ነበር፡፡ በወቅቱ ይፋ ካደረጓቸው እና በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ከሚሰሩ የኢኮኖሚው ማርሽ ቀያሪ ፕሮጀክቶች መካከል በአፍሪካ ግዙፍ የሆነው የአየር ማረፊያ ግንባታ ይጠቀሳል፡፡

ጥር 2 ቀን 2018 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን

ወደ ገጽ 5 ዞሯል



ፎቶ ከገጸ ድር

የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ዲዛይን

# የአብሮነት እሴቶችን እንዴት እናጠናክራቸው?

- **በጥምቀት በዓል የሚታየው መከባበር፣ መደጋገፍና መተሳሰብ የኢትዮጵያውያን አብሮነት ስር የሰደደ መሆኑን እንደሚያመላክት ተጠቁሟል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

አቶ ስለሺ ደቻሳ ትውልድና እድገታቸው ካዛንቺስ ነው፡፡ ጥምቀት ሁሌም በጉጉት የሚጠብቁት በዓል እንደሆነ ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል። ከቤተሰብ፣ ከአብሮ አደግ ጓደኞቻቸው፣ ከህዝበ ክርስቲያን ጋር በመሆን፣ ታቦታትን እያጀቡ ማክበርም ልዩ ደስታን ይፈጥርላቸዋል፡፡

እንደ አቶ ስለሺ ገለጻ፣ ጥምቀት የኢትዮጵያውያን አብሮነት የሚታይበት በዓል ነው፡፡ በበዓሉ የተለያየ

ወደ ገጽ 6 ዞሯል







**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## የወንዝ ዳርቻዎች ልማቱ የአዲስ አበባን የቱሪዝም የስበት ማዕከልነት ከፍ የሚያደርግ ነው!

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ መዲና ብቻ ሳትሆን፣ ከዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ ማዕከልነቷ አንጻር ከኒው ዮርክና ከጄኔቫ በመቀጠል በሶስተኛ ደረጃ የምትጠቀስ የአፍሪካ አህጉር ኩራት ናት። ይሁን እንጂ ከተማዋ ለዘመናት ይህን ግዙፍ ስምና ዝና የማይመጥን፣ የተበከሉ ወንዞችና የማይስብ ገጽታ ነበራት። በስም ብቻ የገነነችውን ከተማ በተግባርም እንድትገኝ ለማድረግ በአሁኑ ወቅት እየተከናወነ ያለው የወንዞች ዳርቻ ልማት ታሪክን የለወጠ ታላቅ እርምጃ ሆኗል።

የአሁኑ የልማት ስራ አዲስ አበባን "እንደ ስሟ አዲስ" እያደረጋት ይገኛል። ቀደም ሲል የቆሻሻ መጣያና የመጥፎ ሽታ ምንጭ የነበሩት ወንዞች፣ ዛሬ በግሩም ሁኔታ ለምተው ለከተማዋ ውበትና ለነዋሪዎቿ መዝናኛ እየሆኑ ነው። በከተማዋ 76 ወንዞች ያሉ ሲሆን፣ በኢትዮጵያውያን አቅም በስምንት ወንዞች ላይ የ47 ኪሎ ሜትር የወንዝ ዳርቻ ልማት ስራው እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ከእንጦጦ እስከ ፒኮክ ያለው ወንዝ ብቻ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች እና መሰረተ ልማቶችን ሳይጨምር 21 ኪሎ ሜትር ይረዝማል፡፡ በዚሁ የወንዝ ዳርቻ ውስጥ ሰባት ፓርኮች ይገኛሉ፡፡

በመዲናዋ ወንዞች ላይ የተጀመረው ይህ የወንዝ ዳርቻ ልማት የወንዞችን ገፅታ ከመቀየሩም በላይ ለዓመታት የዘለቀውን የከተማዋን ነዋሪዎች ጥያቄ የመለሰ እርምጃም ጭምር ነው፡፡

እነዚህ የወንዝ ዳርቻ ልማቶች የአዲስ አበባን ገጽታ ከቀየሩት እንደ ወዳጅነት አደባባይ እና የእንጦጦ ፓርክ ያሉ ስራዎች ጋር ተደማምሮ የከተማዋን የቱሪዝም መዳረሻነት በከፍተኛ ደረጃ አሳድገውታል። የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በአንድ ወቅት እንደተናገሩት "አዲስ አበባ ስሟን የምትመጥን፣ ለነዋሪዎቿ የምትመችና ለጎብኚዎቿም የምትናፍቅ ከተማ የማድረግ ራዕያችን በተግባር እየታየ ነው" ያሉት ንግግር የዚህን ለውጥ ጥልቀት ያሳያል።

የአዲስ አበባ ወንዞች ዳርቻ ልማት ከተማዋ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታ የገነባችው ግዙፍ ፕሮጀክት ነው። ይህ ልማት ከተማዋ ያላትን የኮንፈረንስ ቱሪዝም አቅም ወደ ላቀ ደረጃ ያሸጋግረዋል። በየዓመቱ በሺዎች የሚቆጠሩ ዲፕሎማቶችና እንግዶች ለስብሰባ ወደ መዲናዋ ሲመጡ፣ ከስብሰባ አዳራሾች ባለፈ ልብን የሚያርሱና ዓይንን የሚስቡ የወንዝ ዳርቻ መናፈሻዎችን ማግኘታቸው የከተማዋን ገቢና ዝና በእጥፍ ያሳድገዋል።

በወንዝ ዳርቻ ልማቱ የተገኘው ውጤት ዘላቂ እንዲሆን የከተማዋ ነዋሪዎች ሚና ወሳኝ ነው። እነዚህን ውብ ስራዎች ከብክለት የመጠበቅና የመንከባከብ ኃላፊነት የሁላችንም ነው። ቆሻሻን ወደ ወንዞች አለመጣልና አካባቢን በባለቤትነት ስሜት መጠበቅ ከተማዋን ለትውልድ የምትሻገር የአፍሪካ እንቁ ያደርጋታል። ዜጎች ይህንን የልማት በረከት እንደ አደራ ሊጠብቁት ይገባል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጀመረውን የተቀናጀ የልማትና የለማውን የመጠበቅ ስራ አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። የአካባቢ ጥበቃ ቁጥጥርን ማጥበቅ፣ የማህበረሰብ ግንዛቤን ማሳደግና የህግ ማስከበር ስራዎችን በዘላቂነት መተግበር የግድ ይላል። አዲስ አበባ የዲፕሎማሲና የቱሪዝም የስበት ማዕከል ሆና እንድትቀጥል፣ የከተማዋ ነዋሪዎችም የወንዞቿ ጽዳትና ውበት ተጠብቆ እንዲቀጥል የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል። ውብ ከተማ ለጤናማ ማህበረሰብና ለበለጸገ ኢኮኖሚ መሰረት ነውና ለልማቱ ዘላቂነት ሁሉም የየራሱን ሚና ሊወጣ ይገባል፡፡

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## ግብይት በበዓል ሰሞን እና በማግስቱ

**በሰናይ ምግባሩ**

ከገና በዓል አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ከባለቤቴ ጋር በመሆን በቅዳሜና እሁድ ገበያዎች 10 ኪሎ ሽንኩርት ኪሎ በ30 ብር ሂሳብ ገዛን፡፡ ይህን ማድረግ የፈለግነው ቀናት በተቃረቡ ቁጥር "የዋጋ ጭማሪ ሊኖር ይችላል" ከሚል ስጋት የተነሳ ነው፡፡ በዓሉ ሲደርስ ሌሎች የፍጆታ ግብዓቶችን ለመግዛት ወደ ግብይት ቦታዎቹ አቀናን፤ ሆኖም ሽንኩርት በዚያው ዋጋ በአንዳንድ አካባቢዎች እንደውም በአነሰ ዋጋ ሲሸጥ ተመለከትን። የጥንቃቄ እርምጃችንን እያደነቅኩ ከዚህ ባልተናነሰ መልኩ በበዓል ሰሞን የዋጋ ጭማሪም ሆነ የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይኖር የሰሩ ሰዎችን ማመስገን ይገባል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ዛሬ እና ነገ ደግሞ የጥምቀት በዓልን ምክንያት በማድረግ ግብይቶች ይካሄዳሉ፡፡ እነዚህ ግብይቶች ልክ እንደ ገና እና ከዚያ በፊት እንደተከበሩት በዓላት የተረጋጋ ዋጋ እና በቂ ምርት ይቀርብባቸዋል ብዬ አምናለሁ፡፡ የሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥርም እንዲሁ፡፡

ይህ መልካም ጅምር በሌሎች ቀናትም ጎልብቶና ተጠናክሮ መቀጠል መቻል አለበት፡፡ የሸማቹ አሁናዊ ጥያቄ በፊት ያነሳው ከነበረው እየተቀየረ መጥቷል ብል ማጋነን አይሆንም፡፡ "የዋጋ ጭማሪ ይኖር ይሆን" የሚለው ስጋቱ ከበዓላት ሰሞን ይልቅ ወደ መደበኛ ቀናት እየተቀየረ ነው፡፡ "የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በመደበኛ ቀናትም የዋጋ ጭማሪ እንዳይኖር የሚያደርጉትን ቁጥጥርና ክትትል አጠናክረው ቢያስቀጥሉ ጥሩ ነው" የሚል ድምጽ የሚያሰሙ ሸማቾች ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ እኔም በዚህ ሀሳብ እስማማለሁ፡፡

የቅዳሜ እና እሁድ እና መሰል የመገበያያ ቦታዎች ያለምንም የደላላ ጣልቃ ገብነት ነጋዴውን እና ሸማቹን በቀጥታ የሚያገናኙ ናቸው፡፡ ስለሆነ ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ ያስቸግራል ብዬ አላስብም። የሚጠይቀው ቅንጅታዊ አሰራርና ቁርጠኛ የሆነ አቋም ብቻ ነው፡፡ ኑሮን ያረጋጋሉ ተብለው መንግስት ተግባራዊ እንዲሆኑ ባደረጋቸው የመገበያያ ስፍራዎች የፍጆታ ምርቶችን የዋጋ ተመን እያስቀመጡ ከሚለጥፉት ባለሙያዎች ጀምሮ የሚመለከተው ሁሉ የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ የዋጋ ዝርዝር ከተለጠፈ በኋላ መለስ ብሎ ግብይቱን የመቃኘት ነገር ተገቢውን ትኩረት ያሻል፡፡ የከተማዋ ከፍተኛ አመራሮች የበዓል ሰሞን የቅርብ ክትትል በሌሎች ቀናትም ሊደገም ይገባዋል ባይ ነኝ፡፡

ይህን ስል ግን ሸማቹ ምንም ሚና የለውም፤ ነጋዴውን አይመለከተውም ማለት አይደለም፡፡ ነጋዴው በተቀመጠለት ዋጋ መሰረት በመሸጥ ለህዝብ ያለውን ውግንና በተግባር ማሳየቱን አጠናክሮ ማስቀጠል ይገባዋል፡፡ ሸማቹ ደግሞ ከመንግስት አካል ብቻ የመፍትሔ እርምጃ መጠበቅ የለበትም፤ ራሱንም የመፍትሔው አካል ማድረግ ይጠበቅበታል። በሌሎች ቀናት ዋጋ ለመጨመር የሚዳዳቸውን አካላት በተቀመጡ ነጻ የስልክ ቁጥሮች እና ይህን ለሚከታተሉ ባለሙያዎች ማሳወቅ፣ ነጋዴውንም "ትክክል አይደለህም" በማለት በግልጽ በመንገር ከድርጊቱ እንዲቆጠብ ማድረግ ይጠበቅበታል የሚል እምነት አለኝ፡፡ በዚሁ አጋጣሚ ለእምነቱ ተከታዮች መልካም የጥምቀት በዓል እንዲሆንላችሁ ተመኘሁ፡፡

ADDIS MEDIA NETWORK
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
ይግለጡ ዓዴ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ፋንታነሽ ተፈራ
አብርሃም ገብሬ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# ከብክለት ወደ ውበት

## “በወንዝ ዳርቻ ልማቱ የከተማዋ ወንዞች ከቆሻሻ ጸድተው ለዓይን የሚማርኩ የመዝናኛ ስፍራዎች ሆነዋል”

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ**

**በሳህሉ ብርሃኑ**



ፎቶ- ከገፀ ድር

በአዲስ አበባ ከተማ እየተከናወነ የሚገኘው የወንዝ ዳርቻ ልማት ወንዞችን ከብክለት አላቅቆ ውብ ገጽታ እያላበሰ ይገኛል

64 ዓመታትን ወደኋላ መለስ ብለን የታሪክ መዛግብትን ስናገላብጥ የካቲት 17 ቀን እኩለ ለሊት ላይ የተከሰተን አንድ አስከፊ አጋጣሚ እናገኛለን። ‘የሰሜን ባህር ጎርፍ’ (North Sea flood of 1962) በሚል ታሪክ ሲያስታውሰው የኖረው ይህ ክስተት የተፈጠረው በጀርመኗ ከተማ ሃምቡርግ ነበር። የከተማዋ ነዋሪዎች ሰላም አሳድረን ብለው በተኙበት ያልገመቱት ነገር ገጠማቸው፡፡ የሰሜን ባህር ጎርፍ ከምዕራብ ጀርመን የባህር ዳርቻዎች ተነስቶ በሃምቡርግ ከተማ የሚገኘውን የኒደርሃፈን ወንዝን ያጥለቀለቀ ኃይለኛ ጎርፍ ተከሰተ። አደጋው የ315 ሰዎችን ህይወት ሲቀጥፍ ወደ 60 ሺህ የሚጠጉ መኖሪያ ቤቶችን ስለማውደሙ እ.ኤ.አ በ2012 በማክ ፊሊክስ በተጻፈው “የ1962 ታላቅ ጎርፍ በሃምቡርግ“ በተሰኘው መጽሐፍ ላይ ሰፍሯል፡፡

በአንዲት ክፉ ቀን የተከሰተው ያ አጋጣሚ ግን በሃምቡርግ እምብርት በሚገኘው የኒደርሃፈን ወንዝ ላይ አስደናቂ ልማት ወልዷል፡፡ የከተማዋን 6 ሺህ ሕንፃዎች ያወደመው አደጋ የፈጠረው ድንጋጤ አስደናቂ የስነ-ህንፃ ጥበብ የታየበትና የሃምቡርግ ጎርፍ መከላከያን ያካተተ ብቻ ሳይሆን ወሳኝ የሆነ የህዝብ መዝናኛ ቦታዎችን ጭምር ፈጥሯል፡፡ ልማቱ በውስጡ ትናንሽ አምፊ ቴአትሮች፣ ሱቆች፣ ካፌዎች እና ልዩ የብስክሌት መስመሮችን ጨምሮ ሚሊዮኖች የሚዝናኑበት ቦታ ሆኗል፡፡

ልክ እንደ ሃምቡርግ ከተማ ሁሉ ደቡብ ኮሪያ በሴኡል ከተማ የሚገኘውና ለከተማ መታደስ (Urban Renewal) እንደ ትልቅ ተምሳሌት የሚጠቀሰው ታዋቂው ወንዝ ቼአንግዬቾን (Cheonggyecheon) ወደ አስደናቂ መዝናኛነት በመቀየር በዓመት ከ18 ሚሊዮን በላይ ጎብኚዎችን ትስባለች።

ወንዙ በአንድ ወቅት በጣም ከመበከሉ የተነሳ በኮንክሪት ተሸፍኖና በላይኛው በኩል አውራ ጎዳና ተገንብቶበት ለዓመታት ተቀብሮ ቆይቷል። እ.ኤ.አ በ2003 የወቅቱ የከተማዋ ከንቲባና በኋላም የሀገሪቱ ፕሬዝዳንት የሆኑት ሊ ዩንግ ባክ አውራ ጎዳናውን በማፍረስ ወንዙን ወደ ቀድሞ ተፈጥሯዊ ውበቱ የመመለስ ደፋር ውሳኔ ወሰኑ። በውጤቱም ዛሬ 8 ነጥብ 4 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ይህ ወንዝ የሴኡል ዋና የቱሪስት መዳረሻ፣ የህዝብ መዝናኛ እና የከተማዋን ሙቀት በመቀነስ ረገድ ትልቅ ሚና የሚጫወት የተሳካ ፕሮጀክት ሆኗል።

በእርግጥ ለመንደርደሪያ ያህል የሁለቱን ከተሞች ሁኔታ አነሳን እንጂ በተለያዩ የዓለም ሀገራት በአንድ ወቅት “ባዮሎጂካዊ ሞት” ታውጀባቸው የነበሩ ወንዞች አስታዋሽ አግኝተው ለምተው ለከተሞቻቸው የኢኮኖሚ ዋልታ እስከመሆን ደርሰዋል፡፡ የ‘Diving into Rivers: The Complete Guide to River Health and Restoration’ መጽሐፍ ደራሲ ጣሊያናዊው ፓስኳሌ ደ ማርኮ እንደሚሉት ወንዞች ከውሃ ምንጭነት ባሻገርም በአግባቡ የልማት ስራ ከተሰራላቸው ወንዞች ያላቸው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ከፍተኛ ስለመሆኑ ደራሲው ያስረዳሉ፡፡

ለአዲስ አበባም ወንዞች የመቆርቆሯ ምክንያትና የቀደመ ውበቷ መገለጫ ነበሩ። ይሁንና የአዲስ አበባ ወንዞች ለበርካታ ዓመታት የከተማዋ ‘ቆሻሻ ማጠራቀሚያ’ ተደርገው መቆየታቸው የማይካድ ሀቅ ነው። ቀደም ባሉት ጊዜያት ወንዞቹ የፋብሪካና የቤቶች ፍሳሽ መፍሰሻ፣ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ፣ የመጥፎ ጠረን ምንጭ ሆነው ቆይተዋል።

በወንዞቹ አካባቢ የሚያልፍ ሰው ሁሉ አፍንጫውን ይዞ የሚሮጥባቸው፣ የከተማዋን ገጽታ የሚያበላሹና ለበሽታ መፈልፈያ የሆኑ የቆሸሹ ስፍራዎች ነበሩ። ይህ ሁኔታ “አዲስ አበባ በወንዞቿ ትጠላለች” የሚያሰኝ መራራ እውነታን ፈጥሮ አልፏል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የወንዞቹን የቀደመ ገጽታ አስመልክተው ሲናገሩ “የወንጀለኞች መሸሸጊያና የአልባሌ ተግባራት መከወኛ ሆኖ ቆይቷል” ሲሉ ይገልፁታል፡፡ በአዲስ አበባ ብቻ 76 ወንዞች እንዳሉ የጠቆሙት ከንቲባዋ ወንዞቹ ከየመጸዳጃ ቤቱ ፍሳሽ የሚገባባቸው ሆነው መገኘታቸውን ነው የገለጹት።

በለውጡ ዘመን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) “ወንዞቻችንን እናጽዳ ሸገርን እናስውብ” በሚል አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ ከማድረግ ራዕይ ጋር በማስተሳሰር የወንዞች ዳርቻ ልማት መጀመሩን አስታውሰዋል ከንቲባዋ።

የወንዝ ዳርቻ ልማት በወቅቱ ለኢትዮጵያ አዲስ በመሆኑ የውጭ የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ አስፈልጎ እንደነበር አመልክተዋል። ፕሮጀክቱ በተጀመረ አምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ሁለት ኪሎ ሜትር የሚሆን ብቻ ልማት መከናወኑን ጠቅሰው፣ በራሳችን ሀገር በቀል አቅም ለምን አንሰራም? በሚል የዛሬ ዓመት በአዲስ መልክ ስራው መጀመሩን ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያውያን አቅም በስምንት ወንዞች ላይ የ47 ኪሎ ሜትር የወንዝ ዳርቻ ልማት ስራ እየተከናወነ እንደሚገኝም የጠቆሙት ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች፣ ትልቁን ድርሻ የሚይዘውም ከእንጦጦ እስከ ፒኮክ ያለው መሆኑን ገልጸው፣ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች እና መሰረተ ልማቶችን ሳይጨምር 21 ኪሎ ሜትር እንደሚረዝም አስታውቀዋል። በዚሁ የወንዝ ዳርቻ ውስጥ ሰባት ፓርኮች እንደሚገኙና ንግድን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎቶችን እንደሚሰጡም ተናግረዋል።

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እንደሚያብራሩት፣ ከእንጦጦ ተራሮች ተነስተው በከተማዋ በኩል አልፈው የሚጓዙና 47 ኪሎ ሜትር ርዝምት ያላቸው 8 ወንዞች ስለመልማታቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ከእንጦጦ ተራራ በጉለሌ በኩል አፍሪካ ህብረት እንዲሁም ከእንጦጦ በአፍንጮ በር በባንቢስ አድርጎ አቃቂ የውሃ ማጣሪያን በሚሸፍነው ፕሮጀክት በውስጡ 28 የሚደርሱ ድልድዮች፣ ሰው ሰራሽ ሐይቆች፣ አረንጓዴ ቦታዎች፣ የመዝናኛ ማዕከላት፣ የውሃ ትራንስፖርት እና የንግድ ማዕከላት ይገነቡበታል። ለእግር ጉዞና የመሮጫ ትራኮች፣ የብስክሌት መስመሮች፣ ኬብል ካር ትራንስፖርት (የገመድ ላይ መኪና)፣ መዝናኛ ግድቦች እንደዚሁም ሰው ሰራሽ ወንዞችንም ይዟል፡፡

ፕሮጀክቱ የከተማዋን ነዋሪዎች ደህንነት በማሻሻልና እይታ በመለወጥ ረገድ ብዙ ሚና ከመጫወቱ በተጨማሪ፣ የተለያዩ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ መስህቦች እንዲሁም ለጎብኚዎች የእረፍት ጊዜ ማሳለፊያ ስፍራዎችን በማዘጋጀት የውጪ ሀገርና የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችን ወደ አዲስ አበባ መሳብ ያስችላል ተብሎለታል፡፡

ለከተማዋ ነዋሪ ተጨማሪ ቋሚ የስራ ዕድል መፍጠር፣ በወንዞች ዳርቻ እና ህዝብ በሚንቀሳቀስባቸው ቦታዎች የአገልግሎት ዘርፉን በማበረታታት ካፌዎች፣ ምግብ ቤቶች፣ የከተማ አስጎብኚዎችና የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ማመቻቸት፤ የተፋሰስ ወንዞች ዳርቻ እና ፕሮጀክቱ ዳርቻ ያሉና ወደፊት የሚገነቡ የሪል እስቴት ፕሮጀክቶችም የዕቅዱ አካል ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ ስራዎች ታዲያ ለመዲናዋ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ጉልበት እንደሚሰጡ መረዳት ይቻላል። ዛሬ ላይ የአዲስ አበባ ወንዞች ከቆሻሻ ጸድተው የፍሳሽ ቦይ መሆናቸው ቀርቶ፣ የህዝብ መዝናኛ፣ የቱሪስት መዳረሻና ለዓይን የሚማርኩ መዝናኛ ስፍራዎች ሆነዋል።

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች ፣ “በአዲስ አበባ ከተማ በተከናወነው የወንዝ ዳርቻ የልማት ፕሮጀክት አቧራውን አራግፈን የደበዘዘውን ታሪካችንን እና ቅርሶቻችንን በተጨባጭ አልምተናል” ይላሉ፡፡ የወንዝ ዳርቻ ልማቱን ተከትሎ በአካባቢው ለነዋሪዎች ምቹ የሆኑ ጅምናዝየሞች፣ ካፍቴሪያ እና ውብ የእግረኛ መንገዶች ተገንብተዋል፡፡ የፈራረሱና መንገድ አልባ የነበሩ መንገዶች ተስተካክለዋል፡፡

ከንቲባ አዳነች እየተከናወኑ ያሉት የወንዝ ዳርቻ የልማት ፕሮጀክቶችን ተዘዋውረው በጎበኙበት ወቅት በሰጡት አስተያየት የወንጀለኞች መደበቂያ የነበሩ ስርቻዎች ጠርተው አካባቢው ብርሃንና ውበት እንዲላበስ ተደርጓል ብለዋል፡፡

በመዲናዋ የተከናወኑ የወንዝ ዳርቻ የልማት ሥራዎች በመሠረተ ልማት እጦት ተራርቀው የቆዩ ነዋሪዎችን ማገናኘት መቻላቸውንም ከንቲባ አዳነች ያስረዳሉ። በመዲናዋ የተከናወኑ የወንዝ ዳርቻ እና የተለያዩ የልማት ሥራዎችን ተዘዋውረው ሲጎበኙ በሰጡት ማብራሪያ ጉለሌ ላይ ድልድይ ባለመኖሩ ህዝቡ በቅርብ ርቀት ላይ ሆኖ ለመገናኘት ሲቸገር መቆየቱን ተናግረዋል፡፡ የአካባቢው ማኅበረሰብ ብረት እና እንጨት በማስቀመጥ በማይመች ሁኔታ ለመገናኘት ሲሞክር መቆየቱን የገለጹት ከንቲባዋ፣ አሁን ላይ ግን አካባቢውን የማስዋብ ብቻ ሳይሆን የድልድይ ግንባታ በመከናወኑ ሕዝቡን ማገናኘት የሚያስችል ሥራ መሰራቱን አስረድተዋል፡፡

የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክቱ እየተከናወነ በሚገኝባቸው አካባቢዎች በርካታ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ማመቻቸት እንደተቻለ ገልጸዋል፡፡ በዚሁ አንድ ዓመት ውስጥም ከወንዝ ልማቱ ባሻገር የኢሬቻ እና አራዳ ፓርኮች ተካተውበታል፡፡

ወንዞችን ማልማት ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም፡፡ በዓለም ላይ ከ2 ቢሊዮን በላይ ሰዎች በቀጥታ በወንዞች ላይ በመጠጥ ውሃ ጥገኛ ሲሆኑ፣ 25 በመቶ የዓለም የምግብ ምርት የሚቀርበውም ከወንዞች በሚገኝ ውሃ ነው። እንደዚሁም በዓመት ቢያንስ 12 ሚሊዮን ቶን ዓሳ የሚገኘው ከዚሁ ከወንዝ ነው ይላል የአሲሲዮና ገፀ ድር መረጃ፡፡

# ጥምቀት እና ሽሮ ሜዳ

- በሽሮ ሜዳ አካባቢ በተከናወነው የኮሪደር ልማት ምክንያት ሱቆችና በውስጣቸው ያሉ ምርቶች በግልፅ የመታየት እድል በማግኘታቸው የንግድ ስራው መነቃቃቱ ተጠቁሟል




ፎቶ- ከፋይል

በኮሪደር ልማቱ ምቹ የንግድ ስርዓት የተላበሰው ሽሮ ሜዳ የገበያ ማዕከል



ፎቶ- ከፋይል

በኮሪደር ልማት ስራው ውብ ገፅታ የተላበሰው የሽሮ ሜዳ አካባቢ በከፊል

በመለሰ ተሰጋ

ጥምቀት እንደገና! የመወለድ ድንቅ ምስጢር ነው፡፡ ኃይማኖታዊ ትርጓሜው ከነ ታላቅ ክብሩ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ ነብር ዥንጉርጉር የሆነው ቀይ፣ ጠይም፣ ጥቁር እና የቀይዳማው መልካችን በቀለማት ባሸበርቁና በሀገር ልጆች በእነዚያ የማር እጆች በተሸመኑት አልባሳት እንደ ሌት ጨረቃ ግርዶሹን ገፍፎ ይታያል፡፡ በሰሞነ ጥምቀት ሁሉም በባህል ልብሱና ጌጣጌጡ ተውቦ ወደ አደባባይ ይወጣል፡፡

በተለይ አዲስ አበባ እንደ ፅጌሬዳ ፈክታ ከምትታይባቸው የአደባባይ በዓላት መካከል አንዱ ነው፤ ጥምቀት፡፡ በሀገር ልጆች ተሸምነው የቀረቡ የባህል አልባሳትን የተጎናፀፉ የመዲናዋ ነዋሪዎች በተዋቡት ጎዳናዎች ላይ ሽር ብትን ሲሉ ላስተዋለ ሰው አንዳች የውበት ፏፏቴ ከእንጦጦ ተራራ ስር ፈልቆ በውቦቹ የመዲናዋ ጎዳናዎች የፈሰሰ ያህል ይሰማዋል፡፡

በርግጥም ይህንን ሁሉ ወፈ ሰማይ ከባህሉ አስታርቀው እንደ ንጋት ጀምበር ያስዋቡ እጆች ያሉትም እንጦጦ መዳረሻ ሽሮ ሜዳ ላይ ነው፡፡ አዎ! በህብረ ቀለማት የተሸቆጠቆጠው የሽሮ ሜዳ ገበያ በጥምቀት ሰሞን በውበት ላይ ውበትን ደርቦ ይደምቃል፡፡ ይፈካል፡፡ ይዋባል፡፡ ያስውባል፡፡

የመዲናዋ የውበት ምርኮኞች፣ የባህል አርበኞች እና ከራሳቸው የተወዳጁ የበዓሉ ታዳሚዎች ከአዘቦት ቀን በዛ ብለው ወደ ሽሮሜዳ ያመራሉ፡፡ ከዚህ ሰፈ የባህል ሙዚየም ቀልባቸው የወደደውን እና አቅማቸው የፈቀደውን ሸምተው በጥምቀት እንደ ባዘቶ ጥጥ ፈክተው፣ እንደ በጋ ፀሐይ ደምቀው፣ እንደ ንጋት ኮከብም ተውበው ይታያሉ፡፡

‘ሽሮ ሜዳ ወይ እንጦጦ፣

መቼ ቀረ ልቤ ቆርጦ፡፡’ እንዳለች ዘፋኟ፣ በኮሪደር ልማት ዳግም የተወለደችውን ሽሮ ሜዳን ያየ ሰው ልቡ ቆርጦ አይቀርም። ምክንያቱም በሽሮ ሜዳ ኢትዮጵያ በራስ ጥበብ ደምቃ ትታያለችና፡፡ አዎ! ወደ ሽሮ ሜዳ መሄድ ወደ እራስ መቅረብ፤ ከራስም መታረቅ ነው፡፡

ይህንን ፅሑፍ ለማሰናዳት ወደ ስፍራው ባቀናንበት ወቅት የኮሪደር ልማቱ ባመጣው በረከት በእንዝርት መልክ በተሰሩት ውብ መናፈሻዎች ዘና እያለ ያገኘነው ወጣት ታሪኩ ደምሌ እንደሚለው ወደዚህ አካባቢ ሲመጣ በትዝታ ፈረስ ወደ ትውልድ ስፍራው ድንገት ይነጉዳል፡፡ አንዳንዴ የወዳጅ ዘመድ ናፍቆትን አስረስቶ ፈገግ ያሰኘዋል። ደግሞም ይመልሰውና ለሰመመን አስረክቦት ይሄዳል፡፡ ቢሆንም ሽሮ ሜዳ ለሱ መልኩን እንደሚያይበት መስታወት ናት፡፡ ከዓመታት በፊትም ያደንቃት የነበረችው ሽሮ ሜዳ በኮሪደር ልማት የበለጠ በመዋቧ የእሱን ብቻ ሳይሆን የብዙዎችን ደስታ ከፍ ስለማድረጉም አጫውቶናል፡፡

የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያው ዘሪሁን እሸቱ (ዶ/ር) አዲስ አበባ በኮሪደር ልማት እንደመስቀል ወፍ እያየናት ተለውጣለች፡፡ ደምቃለች፡፡ ተውባለች፡፡ ከስሟ ትርጓሜ ጋርም እየተጣጣመች መጥታለች፡፡ ከመንገዶቿ፣ ከወንዝ ዳርቻ፣ ከህንፃዎቿና መሰል ልማቶቿ ባሻገርም የማህበራዊ መስተጋብራችንን የሚያጣፍጡ፣ ሰውን ከተፈጥሮ፣ ሰውን ከሰው፣ ሰውን ከራሱ፣ ሰውን ከባህሉ የሚያስታርቁ ስራዎችም ተከናውነዋል ብለዋል፡፡

ለአብነትም ሽሮ ሜዳና አካባቢውን የጠቀሱት የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያው አካባቢው በኢትዮጵያውያን ሀገር በቀል ዕውቀት የተሰሩ አልባሳት፣ የሽክላ ውጤቶች የሚገኙበት ነው፡፡ በመሆኑም ስፍራው ከንግድ ባሻገር ህብረ ብሔራዊነታችን ከፍ ብሎ የሚታይበት ነው፡፡ ታዲያ የኢትዮጵያውያን ውብ አልባሳት በራስ እጅ ተሸምነው የሚቀርቡበትን ይህንን ስፍራ በኮሪደር ልማት ከነ ሙሉ ክብሩ ከፍ አድርጎ ማልማት ተችሏል፡፡

> “በኮሪደር ልማቱ ምክንያት በሽሮ ሜዳ አካባቢ የጎዳና ላይ መብራቶች፣ ሰፋፊ የተሽከርካሪና እግረኛ መንገዶች፣ ምቹ የመኪና ማቆሚያዎች እና መሰል ልማቶች በመከናወናቸው የንግድ ልውውጡን የተቀላጠፈ አድርጎታል”

እንዲህ አይነት ስፍራዎችን በዚህ መልኩ ማልማት ማለት ትርጉሙ ከፍ ያለ መሆኑን የጠቀሱት የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያው ዘሪሁን (ዶ/ር) ሰው ከባህሉ እንዲወዳጅ፣ አንዱ ባንዱ ባህል እንዲያጌጥና እንዲኮራ በማድረግ ማህበራዊ ትስስራችንን ያጎለብታሉ፡፡ ሀገራዊ አንድነታችንንም ያጠናክራሉ፡፡ ለአብነትም በጥምቀትና መሰል የአደባባይ ለዓላት ለምናየው ውበትና አብሮነት የሽሮ ሜዳ አይነት አካባቢዎች አበርክቶ በቀላሉ የሚታይ እንዳልሆነም ጠቅሰዋል፡፡

የጉለሌ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ወልዴ ወገሴ እንደሚሉት የኮሪደር ልማቱ ያመጣውን በረከት ተከትሎ 800 ዘመናዊ ሱቆች በሽሮሜዳና አካባቢው ተገንብተዋል፡፡ ለ 2 ሺህ ወጣቶችም የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ 1 ሺህ 500 ሰው የሚይዝ ሞል ለሽመና ባለሙያዎች ተገንብቷል፡፡ ክፍለ ከተማው በሽመናና በሽክላ ስራ ለተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ምቹ ሁኔታዎችን እየፈጠረ መሆኑን እና አካባቢውንም የበለጠ የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግም ሰፋፊ ስራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውንም ገልጸዋል፡፡

የጥምቀት በዓልና የሽሮ ሜዳ ሀገር በቀል አልባሳት ገበያ የማይነጣጠል ቁርኝት አላቸው የሚሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ግዛው ማሞ በተለይ ደግሞ የኮሪደር ልማቱ በሽያጭ ሂደትና በደንበኞች ፍሰት ያመጣው ለውጥ ቀላል እንዳልሆነ መታዘባቸውን ነግረውናል፡፡

እንደ ምጣኔ ሀብት ባለሙያው ቀደም ሲል አካባቢው የተጨናነቀ በመሆኑ ለገበያ የቀረቡ ምርቶችን በግልፅ ለማየት ያስቸግር ነበር፡፡ አሁን ግን በኮሪደር ልማቱ መንገዶቹ ሰፍተዋል፡፡ የመሸጫ ሱቆቹም በውስጣቸው ያሉ ምርቶችን በግልፅ የሚያሳዩና ውብ ሆነዋል፡፡

ከዚህ ባሻገርም በምሽትም እንደልብ ሊያሰሩ የሚችሉ የጎዳና ላይ መብራቶች፣ ሰፋፊ የተሽከርካሪና እግረኛ መንገዶች፣ ምቹ የመኪና ማቆሚያዎች እና መሰል ልማቶች በአካባቢው በመከናወናቸው የንግድ ልውውጡን የተቀላጠፈ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ የቱሪስቶችን ደህንነት በጠበቀ መልኩ እንደፈለጉ የሚንቀሳቀሱበት፣ የአካባቢውን ውብ ገፅታ በፎቶ ካሚራቸው ብቻ ሳይሆን በአርበ ልቦናቸው የሚያስቀምጡበትን ዕድልም ይፈጥራል ብለዋል፡፡

“ዛሬ ሽሮ ሜዳ እንደ በባህል ልብሶቻችን ተውባለች” ስትል ሀሳቧን ያጋራችን እና በአካባቢው በሀገር ልብስ ንግድ ስራ የተሰማራችው ወለላ እጅጉ አዲስ አበባ በኮሪደር ልማት ማራኪ ገፅታን ተላብሳለች፡፡ በተለይ ደግሞ ሽሮ ሜዳ ላይ የታየው ለውጥ የሚገርም ነው፡፡ የአካባቢውን የቀደመ መታወቂያ ሳይለቅ ግን ደግሞ መንገዶች ሰፍተውና የተለያዩ መናፈሻዎች ተጨምረው ከመገንባታቸው ባሻገር ለሽያጭ ያቀረብናቸው የሀገር ባህል ልብሶቻችን በአግባቡ ተሰድረው በግልፅ መታየት በሚችሉበት ሁኔታ መሸጥ የምንችልባቸው ዘመናዊ ሱቆች በመገንባታቸው የገዥዎችን ትኩረት መሳብ ተችሏል፡፡ በዚህም ከበፊቱ የተሻለ የንግድ እንቅስቃሴ አለ፡፡ የጥምቀት በዓልን ተከትሎም ወደ ሽሮ ሜዳ ለጉብኝትም፣ ለመግዛትም የሚመጣው ሰው ቁጥርም መጨመሩን እንደታዘበችም ነግራናለች፡፡

የዝግጅት ክፍላችን በቀንና በማታ ባደረገው ምልከታ የሽሮ ሜዳ አካባቢ የቀድሞ ወዝና ለዛውን ጠብቆ አዲስ ውበትን ተጎናፅፎ ይታያል፡፡ ሽሮ ሜዳ፣ ማታ እንደጨረቃ ፈክታ፤ ቀን እንደ ፀሐይ ደምቃ መታየት ጀምራለች፡፡ በተለይም የጥምቀት በዓልን ተከትሎ ልክ እንደ መርካቶ የንግድ እንቅስቃሴው ጦፏል። በርግጥም ሽሮ ሜዳ ከጫጉላ ቤት እንደወጣች ሙሽራ ፊቷ ወዝቷል፡፡ አዲስ አበቤዎች ደግሞ በጥምቀት በዓል ከሽሮ ሜዳ በሸመቱት የሀገር ልብስ ተውበው በአዲስ አበባ ጎዳናዎች እንደ ከዋክብት አምረው ይታያሉ፡፡

# የኢትዮጵያ ... ከገጽ 1 የዞረ



ፎቶ ከገጸ ድር

የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ዲዛይን

ማረፊያ ግንባታ የመሰረት ድንጋይ በማስቀመጥ አስጀምረዋል፡፡ በወቅቱ ባደረጉት ንግግር፣ የአውሮፕላን ማረፊያ ግንባታው የኢትዮጵያ የዝመና ጉዞ፣ የብልፅግና፣ የመለወጥ፣ የኢትዮጵያን ራሷን ችላ በሁለት እግሯ የመቆም መሻት የሚገልጥ ስራ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

በኢትዮጵያ ባለፈው አንድ መቶ ዓመት በኩራት ከሚጠቀሱ የሰመሩ ስራዎች መካከል አንደኛውና ቀዳሚው በኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ የተሰራው ነው፡፡ አየር መንገዱ የጥንታዊት ሀገር ምልክት፣ ኩራትና መሻት ማሳያ ሆኖ ቆይቷል፡፡ የመንግስታት መቀያየር፣ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ፣ ድርቅ፣ በውስጥና በውጭ የተደረጉ ጦርነቶችና ሌሎች ችግሮችን እየተሻገረ ብቻም ሳይሆን እያደገ መምጣቱን ገልጸዋል፡፡

አየር መንገዱ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የገጠሙትን ፈተናዎች በመሻገር የኢትዮጵያ ኩራት፣ የብልፅግና፣ የመሻት ማሳያ ከመሆን ባሻገር የአፍሪካ ኩራትና መመኪያ መሆን የቻለ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አንስተዋል፡፡ የዛሬ 80 ዓመት የአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት ነጻ ሳይወጡ ተመስርቶ መቆም የቻለ ኩባንያ መሆኑንም አክለዋል፡፡

## አውሮፕላን ማረፊያውን መገንባት ለምን አስፈለገ?

አዲሱ አውሮፕላን ማረፊያ በ12 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር ወጪ የሚገነባ ሲሆን የኢትዮጵያ አየር መንገድ 30 በመቶ እንዲሁም የአፍሪካ ልማት ባንክና የተለያዩ አበዳሪዎች ቀሪውን እንደሚሸፍኑ ይጠበቃል፡፡ በአንድ ጊዜ 270 አውሮፕላኖችን የመያዝ አቅም እንደሚኖረውም ተገልጿል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደገለፁት፣ አዲሱ የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ የአውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት የኢትዮጵያ አየር መንገድ በየዓመቱ ሁለት ሚሊዮን አዳዲስ ደንበኞችን እያስተናገደ ይገኛል። የዛሬ ሰባት ዓመት አካባቢ የቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ በዓመት 7 ሚሊዮን ደንበኞችን ያስተናግድ ነበር። በየዓመቱ የሚያስተናግደው ቁጥር እየጨመረ ከመምጣቱ አኳያ ማስፋፊያ ካላደረገ ተጨማሪ ሰዎችን ማስተናገድ አይቻልም። ይህንን በመገንዘብ ለነገ ዛሬ አስቀድሞ መስራት ስለሚያስፈልግ ግንባታው ተጀምሯል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በማህበራዊ ትስስር ገፃቸው እንደገለፁት፣ የተለያዩ አውሮፕላን ማረፊያዎችን የመገንባት ስትራቴጂ ኢትዮጵያን የወደፊቷ የአፍሪካ ግምባር ቀደም የአየር ትራንስፖርት በር የማድረግ ዓላማን ያነገበ ነው። የቢሾፍቱ ዓለምአቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በአፍሪካ ታሪክ ትልቁ የአየር ትራንስፖርት መሠረተ ልማት ፕሮጀክት ይሆናል።

## ግንባታው የሚያካትታቸው ስራዎችና ፋይዳው

የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በሚገነባበት እና በቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ መካከል ያለው ርቀት 38 ኪሎ ሜትር ይሸፍናል፡፡ ይህንን የፍጥነት መንገድ በመገንባት እንዲተሳሰር የሚደረግ ሲሆን በአንድ አቅጣጫ ስድስት፣ በሌላ አቅጣጫ ስድስት በድምሩ 12 መኪኖችን በአንድ ጊዜ ማስተናገድ የሚችል ዘመናዊ መንገድ ይገነባል። የመንገዱ አካባቢም ዙሪያውያን በአረንጓዴ እፅዋቶች የተከበበ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ከአዲስ አበባ እስከ ቢሾፍቱ 38 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው በሰዓት ከ120 እስከ 200 ኪሎ ሜትር መጓዝ የሚችል ፈጣን የባቡር መስመር ግንባታ ይከናወናል፡፡ የባቡር መስመሩም በሀገር ውስጥ ኩባንያዎች እንደሚገነባ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ጠቁመዋል፡፡

በፕሮጀክቱ የመጀመሪያው ምዕራፍ 60 ሚሊዮን መንገደኞችን ማስተናገድ የሚችል የአውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ በፈረንጆች አቆጣጠር 2030 ይመረቃል። በሁለት ምዕራፎች የሚገነባው የአውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ እና ሌሎች የተጀመሩ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ሲጠናቀቁ ከአስር ዓመት በኋላ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2036 ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀዳሚ ኢኮኖሚ ትገነባለች ብለዋል፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፡፡

የአውሮፕላን ማረፊያው የኢትዮጵያ አየር መንገድን በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለም የጥቂት ሀገራት አየር መንገዶች ያሳኩት ደረጃ ላይ ያደርሰዋል፤ በዓመት 110 ሚሊዮን ህዝብ ማጓጓዝ የሚችል አየር ማረፊያ ባለቤትም ያደርገዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) እንደገለፁት፣ ግንባታው የተጀመረው አዲሱ አውሮፕላን ማረፊያ ከቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ በብዙ መልኩ የሚለይ ነው፡፡ የቦሌ አየር ማረፊያ 700 ሄክታር የመሬት ስፋት አለው፡፡ የቢሾፍቱ አውሮፕላን ማረፊያ ደግሞ 3 ሺህ 900 ሄክታር እንዲሁም ከአካባቢው የተነሱ ሰዎች ቦታ ሲጨመር በአጠቃላይ 5 ሺህ ሄክታር ይሸፍናል፡፡ ይህም "በአየር ላይ የሚመላለሱ መርከቦች" ወይም አውሮፕላኖችን በብቃት በማስተናገድ የኢትዮጵያን የእድገት ስብራት የሆነውን ሎጂስቲክስ መፍታት ይቻላል፡፡

አዲሱ የአውሮፕላን ማረፊያ በአዲስ አበባ ደቡብ ምስራቅ 40 ኪሎ ሜትር አካባቢ የምትገኘው እና 1910 ሜትር ከፍታ ባላት ቢሾፍቱ ከተማ አካባቢ እየተገነባ ሲሆን ይህም ለአውሮፕላኖች ሥራ የተመቸ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠቁመዋል፡፡ ቢሾፍቱ "መዳረሻቸውን ኢትዮጵያ ላደረጉም ሆነ ለትራንዚት መንገደኞች ብቁ ሁኔታ ያላት ናት። ለመዲናችን ያላት ቅርበት ከነባሩ የአየር ትራንስፖርት ምኅዳር ጋር በቀላሉ የተዋሃደ አሠራር እንዲኖር ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።" ሲሉም አክለዋል፡፡

በተባበሩት መንግስታት በአስተዳደር፣ ድህነት እና ዘላቂ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ የፖሊሲ አማካሪ፣ በአፍሪካ ሰብዓዊ ኔትዎርክና የተለያዩ የጥናትና ምርምር ተቋማት ቦርድ ሰብሳቢና አባል በመሆን የሰሩት ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር) የአውሮፕላን ማረፊያ ግንባታው ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ትልቅ አንድምታ ያለው መሆኑን አብራርተዋል። አሁን ያለው አውሮፕላን ማረፊያ የተጠቃሚውን ፍላጎት ለማሟላት በቂ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ አየር መንገዶች ጭምር የሚጠቀሙበት ነው፡፡ የቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ሲገነባ አካባቢው ገጠር የነበረ ቢሆንም በሂደት መሀል ከተማ ሆኗል፡፡ በዚህ ምክንያት አካባቢው ላይ መጨናነቅ እየተፈጠረ በመሆኑ የማስፋፊያ ግንባታ ማካሄድ አስፈልጓል፡፡

አዲሱ አውሮፕላን ማረፊያ መኖሪያ ቤቶች፣ የንግድ ድርጅቶችና የተለያዩ አገልግሎት መስጫዎችን ያካተተ የአየር ማረፊያ ከተማ (Airport City) የሚገነባበት ስለሆነ ለሀገር ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንደሚኖረው የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ያስረዳሉ። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ መረጃ እንደሚያሳየው፣ በ2017 በጀት ዓመት አየር መንገዱ 7 ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር ገቢ አግኝቷል፡፡ አሁን ላይ አየር መንገዱ በዓመት ከ20 ሚሊዮን በላይ መንገደኞችን እያገለገለ ሲሆን በአዲሱ አውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ምክንያት 110 ሚሊዮን ሰዎችን ማስተናገድ ይችላል። ይህም አቅሙን በብዙ እጥፍ በማሳደግ ለኢኮኖሚው የሚያበረክተው ድርሻ ከፍ እንዲል ያደርገዋል፡፡

የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር) በማብራሪያቸው፣ "አውሮፕላን ማረፊያው በሚገነባበት ወቅት ለስራ ተቋራጮችና ዜጎች በርካታ የስራ ዕድል ይፈጥራል፡፡ ለግንባታው የሚያገለግሉ ዕቃዎችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎችም ይገነባሉ፡፡ በዚህም ትልቅ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ይፈጠራል። ከዚህ ባሻገር እንዲህ ዓይነት ግዙፍ አውሮፕላን ማረፊያ ሲገነባ በርከት ያሉ ኢትዮጵያውያን አገልግሎት በማቅረብ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ሆቴሎች ስለሚገነቡ በርካታ የስራ ዕድሎች ይፈጠራሉ፡፡ አዲስ አበባ ላይ በርከት ያሉ ስብሰባዎች የሚደረጉበትና በኮንፈረንስ ቱሪዝም ተመራጭና ተጠቃሚ የምትሆንበትን ዕድል ይጨምራል፡፡ የዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ መዲናነቷን ያጠናክራል፡፡ አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎች ይጎበኛሉ" ብለዋል፡፡

ከአውሮፕላን ግንባታው ጋር ተያይዞ አዲስ አበባን ከቢሾፍቱ የሚያገናኙ ፈጣን መንገድና የባቡር መስመር መገንባቱ መንገደኞች በትራፊክ መጨናነቅ እንዳይቸገሩ ያደርጋቸዋል። የከተማዋን መሰረተ ልማት ደረጃ ያሻሽላል፡፡ በ40 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ውስጥ የሚኖረውን ነዋሪ የህይወት ደረጃ እንዲሻሻል በማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረውም ጠቁመዋል፡፡

ፕሮጀክቱ ከኢትዮጵያ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ሪፎርም፣ የኢንዱስትሪ ማስፋፊያ አጀንዳ እና የረጅም ዘመን የአቪየሽን ስትራቴጂ ጋር የተናበበ ነው። የኢትዮጵያ አየር መንገድን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ያጠናክራል። በአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ ንግድ ቀጣና ማዕቀፍ አፍሪካን የማገናኘት አቅም ይጨምራል። የንግድ እና ቱሪዝም ኮሪደሮችን ያሰፋል። ኢትዮጵያንም ቀዳሚ የበይነ አኅጉር ማዕከል እንደሚያደርጋት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ጣሰው እንደተናገሩት፣ የአውሮፕላን ማረፊያ ግንባታው መጀመር ለኢትዮጵያ አየር መንገድና ለመላው አፍሪካውያን የሚያኮራ አጋጣሚ ነው፡፡ በአየር ትራንስፖርት ያለውን የመሰረተ ልማት ክፍተት በመሙላትና ለአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ ንግድ ቀጣና ስምምነት ተግባራዊነት ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡

አየር መንገዱ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ይዞ የሚዞር፣ በአፍሪካ ሰፊ የገበያ ሽፋን ያለው የሀገርና የአፍሪካ ኩራት ነው፡፡ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ባጋጠመበት ወቅት ብዙዎች አየር መንገዶች ሲከስሩና በድጎማ ሲንቀሳቀሱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ትርፋማ ሆኖ የቀጠለ ነው፡፡ አየር መንገዱ እንደ አንድ ትልቅ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚታይ እንደሆነ ያነሱት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር)፣ የአውሮፕላን ማረፊያ ማስፋፊያ ግንባታው በአፍሪካ ያለውን ገበያ በማስፋት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ የሚያድግበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደገለፁት፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የስኬት ምስጢር የኮርፖሬት ባህል መገንባት መቻሉ፣ ለደህንነት ቅድሚያ መስጠቱ፣ በፈጠራና ትጋት፣ በየጊዜው ራሳቸውን ዓለም ከደረሰበት ደረጃ ጋር ለማድረስ የሚጥሩ አመራሮችና ሰራተኞች ያሉት መሆኑ እንዲሁም ሁልጊዜ ለአዲስ ነገር በሩን ክፍት አድርጎ መስራቱ ነው፡፡ በጥገናና ትምህርት እያስመዘገበ ካለው ስኬት ባሻገር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአውሮፕላን መለዋወጫዎችን ለማምረት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

አየር መንገዱ ባለፉት 80 ዓመት ያሳለፈው ጉዞ የተሳካ ነበር፡፡ የሚቀጥለው 80 ዓመት ከባለፈው በብዙ መልኩ ይለያል፡፡ ከደረስንበት ዘመን አኳያ የሰው ሰራሽ አስተውሎት ላይ በደንብ ካልተሰራ ተወዳዳሪ መሆን አይቻልም፡፡ በዚህ ረገድ በአካልና በአዕምሮ ጠንካራ የሆነ ትውልድ ለማፍራት የቀዳማዊ ልጅነት ፕሮግራም በማስጀመር እና የጋራ አረንጓዴ መዝናኛ ስፍራዎችና ስታዲዬሞች በመገንባት በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በዓለም ሁለተኛ የሆነ የሰው ሰራሽ አስተውሎት ዩኒቨርሲቲ በአዲስ አበባ ይጀመራል፡፡ ይህም አየር መንገዱ በሚቀጥለው 80 ዓመት የሚገጥመውን አዳዲስ እውቀትና ፈተና ተቋቁሞ ለማለፍ የሚያስችለውን ብቃት እንዲጎናፀፍ እንደሚያስችለው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

# የአብሮነት ... ከገጽ 1 የዞረ

እምነት ተከታዮች የታቦታት ስፍራዎችና መንገዶችን ማፅዳትን ጨምሮ በልዩ ልዩ መልኩ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ነው። ይህ ደግሞ መከባበርን፣ አብሮነትንና ፍቅርን ያጠናክራል፡፡

ይህንን አብሮነትና መተሳሰብ የሚያጠናክር መልካም ተግባርም በግላቸው ብቻ ሳይሆን "ፍቅር ያሸንፋል" የተሰኘ የበጎ አድራጎት ማህበር በኩል እንደሚያደርጉ አቶ ስለሺ ይናገራሉ። የማህበሩ ዋና ፀሀፊ አቶ ስለሺ እንደገለጹት፣ ይህን በበዓላት ወቅት የሚታየውን የአብሮነትና አንድነት እሴት ለማጠናከር ወጣቱን ጨምሮ ህብረተሰቡን በማስተማር የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ መንግስትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

አቶ ሚስባህ ከድር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሶስት ነዋሪ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያውያን በአንድነት፣ በመተሳሰብና በመረዳዳት አብረው ለዘመናት የኖሩ ህዝቦች ናቸው። እሳቸውም ከተለያየ ብሔርና እምነት ያላቸው ነዋሪዎች ጋር በመተሳሰብና በፍቅር ማደጋቸውን ይናገራሉ፡፡

የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑት አቶ ሚስባህ፣ የጥምቀት በዓል ከመከበሩ አንድ ወይም ሁለት ቀን በፊት ጀለቢያቸውን ለብሰው በዓሉ ወደሚከበርበት ጃንሜዳ በመሄድ ቆሻሻ ካለ በማፅዳትና ቦታውን በማስተካከል እንደሚሳተፉ ይናገራሉ፡፡

ከተለያዩ ሰዎች ጋር በመሆን "ፍቅር ያሸንፋል" የተሰኘ ማህበር ከሰባት ዓመት በፊት በመመስረት እየተንቀሳቀሱ እንደሚገኙ የሚናገሩት አቶ ሚስባህ፣ እሳቸውን ጨምሮ የማህበሩ አባላት የጥምቀት በዓል በሚከበርበት ወቅት አስቀድሞ በዓሉ የሚከበርበትን ቦታ በማፅዳት ለክርስትና እምነት ተከታዮች ያላቸውን ክብር፣ ፍቅርና አጋርነት ያሳያሉ፡፡ የማህበሩ መስራችና ስራ አስኪያጅ አቶ ሚስባህ፣ በጥምቀት በዓል ብቻ ሳይሆን በእስልምና የኢድ አልፈጥርና ኢድ አልአድሃ በዓላት ሲከበሩ እንዲሁም በኢሬቻ በዓል በተለያየ መልኩ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡ ይህም ኢትዮጵያዊ አብሮነትን የሚያጠናክር ተግባር እንደሆነና ወደፊትም እንደሚገፉበት ገልጸዋል፡፡

"ይህን በማድረጋችን በጣም ደስተኛ ነን፡፡ የምናደርገውም የክርስትና ወይም የእስልምና እምነት ተከታዮች ማፅዳት ያቅታቸዋል ብለን አይደለም፡፡ በእምነት ብንለያይም፤ ሰው ነን፤ ከዚህም ባሻገር ኢትዮጵያ በተባለች ሀገር የምንኖር ኢትዮጵያዊ ነን፡፡ የእናንተ ደስታ የእኛ ደስታ ነው" በሚል የጀመሩት እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ ቆሻሻን በማቃጠልና በማስወገድ ሲሳተፉ አብሮ ቆሻሻ የሆነውን አስተሳሰብ እንዲጠፋ በማድረግ አብሮነትና አንድነት እንዲጠናከር እየሰሩ እንደሆነ አቶ ሚስባህ አክለዋል፡፡

ሀምሳ አለቃ እንዳሻው የየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 የኮሪያ ሰፈር ነዋሪ ናቸው፡፡ ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን በበዓሉ ከመሳተፍ ባሻገር ጥር 8 እና 9 ቀን በየዓመቱ ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር በመሆን ጃንሜዳ ለዚሁ አገልግሎት ምቹና ፅዱ እንዲሆን ማድረግ ላይ የመሳተፍ



ፎቶ- ከገፀ ድር
በ2017 ዓ.ም በአዲስ አበባ የተከበረው የጥቅምት በዓል በ6 ኪሎ አካባቢ የነበረው ከፊል ገፅታ

ልምድ አላቸው፡፡ "በዓሉ የሚከበርበትን ስፍራ ከአካባቢው ነዋሪ ጋር በመሆን አፀዳለሁ፤ ይህንን ሳደርግ ደስታ ነው የሚሰማኝ፤ ከተለያየ እምነት ተከታዮች ጋር በመከባበር እንድንኖር፣ እርስ በርስ ያለንን ግንኙነት እንድናጠናክርም የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል" ሲሉ በመሳተፋቸው የሚሰማቸውን ስሜት ይናገራሉ፡፡

የጥምቀት በዓል በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ ሳይንስና ባህል ተቋም (ዩኔስኮ) ከተመዘገቡ የማይዳሰሱ የዓለም ቅርሶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ለይኩን ብርሃኑ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሀዲስ ኪዳን ትርጓሜ መምህር ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት፣ ጥምቀት በቤተ ክርስቲያኗ በታላቅ ድምቀት ከሚከበሩ አበይት በዓላት አንዱ ነው፡፡ የበዓሉ ሃይማኖታዊ መነሻ ኢየሱስ ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ በመውረድ፣ በመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በታላቅ ትህትና የተጠመቀበት፣ ሰው የእግዚአብሔርን ልጅነት ያገኘበት ታላቅ ምስጢር የተገለጠበት ዕለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጅን ለማዳን በገባው ቃል ኪዳን መሰረት ወደ ምድር መጥቶ የማዳን ስራውን የጀመረበት ነው።

የአከባበር ስነ ስርዓቱም መምህር ለይኩን እንደሚገልፁት፣ ጥር 10 ቀን በ"ከተራው" ዕለት በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ታቦታት ከመንበረ ክብራቸው በመውጣት በህዝበ ክርስቲያኑ በዝማሬና እልልታ ታጅበው ከሰዓት በኋላ ባህረ ጥምቀቱ ወደተዘጋጀበት ስፍራ ይወርዳሉ፡፡ ሌሊቱም መዘምራንና ካህናት በማህሌትና በሰዓታት እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ፤ ስርዓተ ቅዳሴም ይከናወናል፡፡

ጥምቀት በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንም በድምቀት ከሚከበሩ በዓላት መካከል አንዱ ነው፡፡ አባ አብርሃም ገብረማርያም በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ምክትል ጠቅላይ ፀሀፊና በሐዋርያዊ ዘርፍ ዋና ኃላፊ፣ የጳጳሳዊ ልዑካን ማህበር በኢትዮጵያ ብሔራዊ ዳይሬክተር ናቸው። ጥምቀት ዳግም መወለድን፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባትን፣ በእግዚአብሔር ማመንን የሚሰጥ፣ የአዲስ ህይወት መጀመር የሚገለጥበት ምስጢር ነው። በቤተ ክርስቲያኗ ጥምቀት የንስሃ መግቢያ ወይም በዓለም ከሞት ወደ ህይወትና በመንፈሳዊነት መነሳትን የሚያስገኝ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በበዓሉ ከሚከናወኑ ስነ ስርዓቶች መካከል በውሃ መረጨት አንዱ ሲሆን ይህም ጥምቀት የሚያነፃ፣ የሚያጥብ፣ ለአዕምሮ ብርሃን፣ ከክርስቶስ አዲስ ብርሃንን የሚሰጥ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

በካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የጥምቀት በዓል በታላቅ መንፈሳዊ ዝግጅትና ደስታ ይከበራል፡፡ ያልተጠመቁት ይጠመቃሉ፤ የተጠመቁት ደግሞ የመጀመሪያ የጥምቀት ቀናቸውን እያሰቡ መንፈሳዊ ህይወታቸውን እና እምነታቸውን ያድሳሉ፡፡ የእምነቱ ተከታዮች ነጭና ያማረ ልብስ ለብሰው ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ፤ ከቤተሰብ፣ ጎረቤትና ማህበረሰብ አብረው ያሳለፉትን የደስታ ጊዜ እያሰቡ፣ በአብሮነትና በደስታ እንደሚያከብሩ አክለዋል፡፡

## የአብሮነት ተምሳሌት

ጥምቀት ኢትዮጵያውያን "የጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ..." በሚለው ብሂል አምረውና ደምቀው የሚታዩበት በዓል ነው፡፡ የተለያየ ማንነት፣ ቋንቋ፣ ባህል ያላቸው ሰዎች በራሳቸው ቀለም ኮርተው፣ ተውበውና ደምቀው ይታያሉ። በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሶሲዮሎጂና አንትሮፖሎጂ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን ዶዳ (ዶ/ር) ከዚህ ቀደም ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ በጥምቀት በዓል በተለያዩ ማህበረሰቦች መካከል የሚታየው መከባበር፣ መደጋገፍና መተሳሰብ የኢትዮጵያውያን አብሮነት ምን ያህል ስር የሰደደ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ልዩ ልዩ የቋንቋና የባህል ማንነት ያላቸው ሰዎች በጋራ በዓልን ማክበር በልዩነት ውስጥ ያለውን አንድነትና ውበት ያሳያል።

ከበዓሉ በፊትም በአዲስ አበባ ከተማ ዋናው ጥምቀተ ባህሩ የሚከናወንበትን ቦታ በማፅዳትና በማዘጋጀት የእስልምና እና የተለያየ እምነት ተከታዮች መሳተፍ ከሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ድንበሮች የዘለለ የመከባበር እና የመተባበር እሴት ትልቅ ማሳያ ነው። የጋራ ሰብአዊነት እና ግቦች ከግለሰባዊ ልዩነቶች የበለጠ ጉልህ እንደሆኑ ያስተምረናል፡፡ በብዝሃ ማህበረሰብ ውስጥ በሰላም አብሮ የመኖር እድልን ያጎላል ይላሉ፤ ዘሪሁን (ዶ/ር)።

የማህበረሰብ ልማት ልዩ ባለሙያ አቶ ዘላለም ይትባረክ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት፣ "የአደባባይ በዓላት ዘርፈ ብዙ ፋይዳ አላቸው። በዓላቱ የበዓሉ ባለቤት ብቻ ሳይሆኑ የመላው ኢትዮጵያ ህዝብ ሀብቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- የጥምቀት በዓል የእምነቱ ተከታዮች ብቻም ሳይሆን የሀገርና የዓለም ሀብት ነው፡፡ ኢኮኖሚን በማነቃቃት፣ ሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ እንድታገኝ በማስቻልና የሀገርን መልካም ገፅታ በመገንባት ትልቅ ሚና አለው" ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የጥምቀት በዓል ሲከበር የእስልምና እምነት ተከታዮች ጎዳናዎችን፣ የታቦታት ማደሪያዎችን በማፅዳት፣ ታቦታት የሚያልፉበት ቦታ በመልቀቅ ጭምር ድጋፍ ሲያደርጉና ሲሳተፉ ይታያል፡፡ በዚህ ብቻም ሳይሆን በሌሎች በዓላትም የሚታየው ይህ አይነቱ መተሳሰብ፣ አብሮነትና መደጋገፍ ለማህበረሰብና ሀገር እድገት ከፍተኛ ፋይዳ ያለው በመሆኑ ቀጣይነት እንዲኖረው መስራት እንደሚገባ አቶ ዘላለም ይናገራሉ፡፡

ዘሪሁን (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በበዓሉ ዝግጅት እና አከባበር ወቅት የተለያየ ማንነት ያላቸው ሰዎች አብረው ሲመገቡ፣ ሲዘፍኑ እና ሲጨፍሩ ማየት በህዝቦች መካከል ያለውን ጠንካራ ማኅበራዊ ትስስርና መስተጋብር የሚያሳይ ነው። ሰዎች በጋራ የአምልኮ ሥርዓቶች እና በዓላት ላይ እንዲሰባሰቡ እድል ይሰጣሉ። የባለቤትነት ስሜትን እና የጋራ ማንነትን ያጠናክራሉ።

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ

እሌኒ ታደሰ (ዐቃቤ ሕግ)



የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ 1156/2011 የወጣበት መሰረታዊ ዓላማ ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን እና ሌሎች ህጋዊ ሰነዶች ጋር የተጣጣመ ህግ ለማውጣት በማስፈለጉ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ለሰራተኞች ምቹ የስራ ሁኔታ ለመፍጠር አስተማማኝ የኢንዱስትሪ ሰላም፣ ዘላቂ ምርታማነትና፣ የገበያ ተወዳዳሪነት አቅም ለመፍጠር፣ የስራ ሁኔታንና የሙያ ደህንነት ጤንነትና የስራ አካባቢ ጥበቃ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ አዋጅ ነው። እንዲሁም ቀደም ሲል የሌበር ህጎች ከማውጣታቸው በፊት ሰራተኞች ለረጅም ጊዜ ያለ እረፍት ይሠሩ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያትም ለጉልበት ብዝበዛ የተጋለጡ ነበር። ይሕ አዋጅ ግን የሰራተኛው መደበኛ የስራ ሰዓት ያስቀመጠና ለሰራተኞች ሊከበሩላቸው የሚገቡ የተለያዩ የእረፍት ጊዜያት ያመቻቸ ነው፡፡ ስለሆነም በስራ ቅጥር ግንኙነቶች ሰራተኞች ደህንነታቸው ተጠብቆና የተለያዩ መብቶቻቸው ተከብሮላቸው ግዴታቸውን የሚወጡበት አግባብ አዋጁ ያስቀመጠበት ሁኔታ አለ፡፡

### የአዋጁ የተፈጻሚነት ወሰን /አንቀጽ 3

ይሕ አዋጅ በቅጥር ላይ በተመሰረተ የስራ ውል ግንኙነት እና በምልመላ ሂደት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በዚህ አዋጅ የማይሸፈኑ አካላት አሉ፡፡ ለምሳሌ ዳኞች፣ አቃቤያነ ህግ፣ ፖሊስና መከላከያ በዚህ አዋጅ አይሸፈኑም፡፡ እንዲሁም ሰራተኛው የስራ መሪ ሲሆን፣ የግል አገልግሎት ቅጥር/ ለምሳሌ የቤት ሰራተኞች፣ የቤት ጥበቃ/ የመኖሪያ ቤት ሞግዚት /ወዘተ..... በዚህ አዋጅ የሚገዙ አይደሉም፡፡ ነገር ግን ለትርፍ በተቋቋሙ የተለያዩ ድርጅቶችና ንግድ ቤቶች ተቀጥረው የሚሰሩ የጽዳት ሰራተኞችና የጥበቃ ሰራተኞች በዚህ አዋጅ የሚሸፈኑ ይሆናል ፡፡

### የስራ ውል ይዘት /አመሰራረት/ አንቀጽ 4

ማንኛውም ግለሰብ ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪው መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ስራ ለአስሪው ለመስራት ቢስማማ በሁለቱ መካካል የስራ ውል ይመሰረታል። የስራ ውል ተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ ማስቀመጥ አለበት፡፡ እንዲሁም ደመወዝ፣ የአከፋፈሉ ሁኔታና፣ ውሉ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ማስቀመጥ አለበት፡፡ የስራ ውል ህግን ወይም ሞራልን የሚቃረን መሆን የለበትም፡፡ ለምሳሌ የሚፈጸመው ስር ውል በህግ የተከለከሉ ተግባራትን ለማከናወን መሆን የለበትም፡፡ ውሉ ህግና ሞራልን የሚቃረን ከሆነ ግን ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

የስራ ውል በህግ በህብረት ስምምነት ወይም በስራ ደንብ ለሰራተኛው ከተሰጡት ጥቅሞች ያነሰ ጥቅም የሚሰጥ መሆን የለበትም፤ ነገር ግን ለሰራተኛው የተሻለ ጥቅም በሚሰጥ መልኩ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ የስራ ውሉ በጽሑፍ ቢሆን ተመራጭ ነው። ነገር ግን የተለየ ፎርም አልተቀመጠለትም፡፡

### የሙከራ ጊዜ /አንቀጽ 11

አንድ ሰው በስራ ውሉ መሰረት ሊመደብበት ለታቀደው ቦታ ተስማሚ መሆኑን ለመመዘን ለሙከራ ጊዜ መቅጠር ይቻላል፡፡ በዚህ አዋጅ የሙከራ ጊዜ ከ60 የስራ ቀናት ሊበልጥ አይችልም። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሰራተኛው ለስራው ተስማሚ ካልሆነ ማስጠንቀቅያ ሳይሰጠው ከስራ ይሰናበታል፡፡ በዚህ ጊዜ አሰሪው ለሰራተኛው የስራ ስንብት ክፍያና ካሳ መክፈል አይጠበቅበትም፡፡ ሰራተኛውም በዚህ ጊዜ ውስጥ ስራውን ካለማስጠንቀቅያ መልቀቅ ይችላል፡፡ በዚህ አዋጅ የሙከራ ጊዜው ሊራዘም የሚችልበት ሁኔታ አዋጁ አልደነገገም፡፡ የሙከራ ጊዜ ሰራተኛ ቋሚ ሰራተኞች ያላቸውን መብትን ግዴታ የለውም። በአዋጁ የተቀመጡ የተለያዩ መብትና ግዴታዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት ሰራተኛው ቋሚ ሰራተኛ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ነው ፡፡

### የአሰሪ ግዴታ / አንቀጽ 12

በዚህ አዋጅ የአሰሪ ግዴታ የሚባለው በስራ ውሉ መሰረት ስራ የመስጠት፣ ለስራው የሚያስፈልግ አስፈላጊ መሳሪያና ጥሬ እቃ የማቅረብ፣ ደመወዝ የመክፈል፣ ሰብዓዊ ክብርን የመጠበቅና የስራ ውሉ በሚቋረጥበት ጊዜ ወይም በማናቸውም ሰራተኛ ሲጠየቅ የስራ ልምድ ማስረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት። ለሰራተኛ የተጠበቁ ልዩ ልዩ መብቶች እንደ የዓመት እረፍት ክፍያ፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣ የወሊድ እረፍት ወዘተ... የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

### የሰራተኞች ግዴታዎች /አንቀጽ 13

ሰራተኛው ከአሰሪ የሚሰጠው ስራ ራሱ መስራት አለበት፡፡ የሚሰጠው ስራ ራሱ ሰራተኛው መስራት አለበት እንጂ በውክልና ማሰራት የለበትም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአሰሪው ትእዛዝ የማክበርና ለስራ ብቁ በሆነ አእምሮና የአካል ሁኔታ በስራ ቦታ መገኘት አለበት። የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችንና ህጎች የማክበርም ግዴታ አለበት፡፡ እንዲሁም ለስራው የተሰጡትን መሳርያዎችና እቃዎች ሁሉ በጥንቃቄ መያዝ አለበት። የራሱንም ሆነ የስራ ባልደረቦቹ አደጋ ላይ የሚጥል ወይም ድርጅቱን ጥቅም የሚነካ ሁኔታ ሲያጋጥመው ወዲያውኑ ለአሰሪው የማስታወቅ ግዴታ አለበት። ከዚህ በተጨማሪም የአሰሪው ምስጢር የመጠበቅ ገዴታ አለበት፡፡

### የተከለከሉት ተግባራት /አንቀጽ 14

በብሔር፣ በጾታ፣ በሀይማኖት በፖለቲካ አመለካከት፣ በኤች አይ ቪ፣ በአካል ጉዳት እና በሌላም ሁኔታ በሰራተኞች መካከል አድልዎ መፈጸም የተከለከለ ነው። እንዲሁም በስራ ቦታ ወሲባዊ ትንኮሳ ወይም ጥቃት መፈጸም፣ አካላዊ ጥቃት መፈጸም፣ ሰራተኛ በሀይል አስገድዶ ስራ እንዲሰራ ማድረግ፣ ሰራተኛን በህይወቱ ላይ አደጋ ሊያደርስበት በሚችል አኳኋን ማሰራት አይቻልም፡፡

### የስራ ውል የሚቋረጥበት አግባብ

የስራ ውል በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡፡

1/ በህግ

2/ በስምምነት

3/ በህብረት ስምምነት

### በህግ

የስራ ውል ከሚቋረጥባቸው ምክንያቶች አንዱ በህግ መሰረት የስራ ውልን ማቋረጥ ነው፡፡ ለምሳሌ ለተወሰነ ስራ የተደረገ የስራ ውል ሲሆን፤ በውሉ በተጠቀሰው ጊዜ ሲያልቅ የስራ ውሉ ይቋረጣል፡፡ እንደዚሁም ሰራተኛው ሲሞት፣ ሰራተኛው በጡረታ ሲገለል፣ ድርጅቱ በመክሰር ሲዘጋ፣ ከፊል ወይም ሙሉ የአካል ጉዳት በመድረሱ ምክንያት ሰራተኛው ለመስራት አለመቻሉ ሲረጋገጥ የስራ ውሉ በህግ መሰረት ይቋረጣል፡፡

### በስምምነት

የስራ ውል በስምምነት የሚቋረጠው ስምምነቱ በጽሑፍ ሲሆን ነው፡፡ ነገር ግን ሰራተኛው በህግ የተሰጠውን መብቱን ለመተው የሚያደርገው ስምምነት የህግ ውጤት አይኖረውም፡፡

### በአሰሪ አነሳሽነት የስራ ውል መቋረጥ /አንቀጽ 22

አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ስራ ውል ያለ ማስጠንቀቅያ የሚቋረጥባቸው ምክንያት ያስቀመጠበት ሁኔታ አለ። እነዚህም በስራው ቦታ ላይ የማታለል ድርጊት መፈጸም፣ በስራ ቦታ አምባጓሮ መፍጠር፣ በአሰሪው ንብረት አላግባብ መጠቀም፣ በ6 ወር ውስጥ ለ8 ቀን የስራ ሰዓት አለማክበር፣ በ6 ወር ውስጥ ለ5 ቀን ከስራ መቅረት ናቸው ፡፡

የአሰሪው ይህ ካለማስጠንቀቅያ የስራ ውል የማቋረጥ መብት የሚጠበቀው ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መኖሩን ካወቀ በ30 ቀን በኋላ በይርጋ ይታገዳል፡፡

### በማስጠንቀቅያ፡-

- ችሎታ መቀነስ
- ሰራተኛው ወደ ሌላ ቦታ ተዘዋውሮ መስራት ካልቻለ
- የስራ መደቡ ሲሰረዝ
- የድርጅቱ ምርታማነት መቀነስ

### የሰራተኞች ቅነሳ

በዚህ አዋጅ መሰረት የድርጅቱ ምርታማነት ሲቀንስ ወይም የመክሰር አደጋ ሲደርስበት 10 ፐርሰንት የሚሆን የድርጅቱ ሰራተኞች መቀነስ ይችላል። የስራ ችሎታቸውና ከፍተኛ የምርት ውጤት የሚያሳዩ ሰራተኞች በስራቸው ላይ እንዲቆዩ ቅድምያ ይሰጣቸዋል ፡፡

### የቅነሳ ቀደም ተከተል፡-

- በድርጅቱ ለአጭር ጊዜ ያገለገሉ
- አነስተኛ ቁጥር ጥገኛ ያላቸው
- አካል ጉዳተኞች
- በስራ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ሰራተኞች
- ነፍሰ ጡር ሰራተኞች ወይም ከወለዱ 4 ወር ያነሰ ጊዜ ያደረጉ ሆኖም በኮንስትራክሽን ስራ ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች ቅደም ተከተል መጠበቅ አይጠበቅባቸውም።

### በሰራተኛው አነሳሽነት የስራ ውል መቋረጥ

የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ ሰራተኛ ማንኛውም ሰራተኛ በአሰሪው የ30 ቀናት ቅድምያ ማስጠንቀቅያ በመስጠት በማናቸውም ምክንያት የስራ ውሉን ማቋረጥ ይችላል፡፡ ሰራተኛው ስራ ውሉን ያለማስጠንቀቅያ ከሚያቋርጥባቸው ምክንያቶች መካከል ሰብዓዊ ክብርና ሞራል የሚነካ ድርጊት ቢፈጸምበት፣ ወሲባዊ ትንኮሳ ሲፈጸምበት ወይም አሰሪው መወጣት የሚገባውን ግዴታ ካልተወጣ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቅያ ማቋረጥ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ውሉን ለማቋረጥ ያለው መብት ድርጊቱ ከተፈጸመ ከ15 ቀን በኋላ ሊቀርብ አይችልም፡፡

### ማጠቃለያ

ከላይ በዝርዝር እንደቀረበው የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 የታወጀበት ዓላማ ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው የተለያዩ የILO conventions ለማጣጣም በማስፈለጉና ደህንነቱ የተጠበቀ የስራ አካባቢ እንዲኖር ለማስቻል ነው፡፡ አዋጁ በርካታ የሰራተኞችና አሰሪ መብትና ግዴታ ያስቀመጠበት ሁኔታ አለ፡፡ ሰራተኞች ከአሰሪያቸው አንጻር ሲታይ ያነሰ የመደራደር አቅም ስላላቸው በዚህ ምክንያት መብታቸው እንዳይሸራረፍ ህጉ ጥበቃ ያደርግላቸዋል፡፡ በአጠቃላይ የሰራተኛና አሰሪ ግንኙነት በህግ የሚመራ ለማድረግም ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡

# 8ኛ ዙር የመሬት ሊዝ ጨረታ ተራዝሟል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ለ8ኛው ዙር የመሬት ሊዝ ጨረታ በየካ፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ፤ ኮልፌ ቀራኒዮ፣ አቃቂ ቃሊቲ፤ አዲስ ከተማ፣ ለሚ ኩራ፣ ጉለሌ፣ ልድታ እና ቂርቆስ ክ/ከተሞች የሚገኙና ለተለያዩ አገልግሎቶች የተዘጋጁ ቦታዎችን በጨረታ አወዳድሮ በሊዝ ለማስተላለፍ ታህሳስ 25/2018 ዓ.ም በአዲስ ልሳን ጋዜጣ በማሳተም ከታህሳስ 27/2018 ዓ.ም እስከ ጥር 12/2018 ዓ.ም ድረስ የሚቆይ የጨረታ ሰነድ ሽያጭ እያከናወነ መሆኑ ይታወቃል፣

ይሁን እንጅ የጨረታ ሰነድ ሽያጩን ማራዘም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ከጥር 13/2018 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥር 26/2018 ዓ.ም ከቀኑ 9፡00 ሰዓት ድረስ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት የጨረታ ሰነድ ሽያጩ የተራዘመ መሆኑን እየገለጽን፣

ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ለማግኘት የቴሌ ብር አካዉንት በመክፈት ከአካዉንታችሁ ተቀናሽ በማድረግ ክፍያ በመፈጸም የጨረታ ሰነዱን በኦን ላይን በ landleasedocument.aalb.gov.et: በመግባት መግዛትና ሰነዱን ፕሪንት በማድረግ መወዳደር ይኖርባቸዋል፡፡

የጨረታ ሰነድ ግዢውን እስከ ጥር 26/2018 ዓ.ም ከቀኑ 9፡00 ሰዓት ድረስ የተራዘመ በመሆኑ ቦታዎቹን በእነዚሁ ቀናት በስራ ሰዓት ጠዋት 3፡00 ሰዓት እና ከሰዓት 8፡00 ሰዓት በየክፍለ ከተማዉ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በመገኘት መጎብኘት የሚቻል መሆኑን እየገለጽን ተጫራቾች የጨረታ መልስ ማቅረቢያ ሰነድ፣ ሲፒኦ፣ የግንባታ አቅም ማሳያ ማስረጃ፣ ሰነዱን ለመግዛት በቴሌ ብር የከፈሉበት ስሊፕ፣ መታወቂያ እና ሌሎች መያያዝ ያለባቸዉና በተጫራቾች መመሪያ ላይ የተገለጹትን በመጨመር በኤንቨሎፕ በማሸግ በኤንቨሎፕ ላይ የተወዳደረበትን የቦታ ኮድ እና የጨረታ ቁጥር በመፃፍ ጥር 26/2018 ዓ.ም ከቀኑ 11፡30 ሰዓት ድረስ ለም ሆቴል አከባቢ ኤም ኤ (MA) ህንፃ ላይ በሚገኘው በከተማው መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ለዚህ በተዘጋጀ የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡ ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ረቡዕ ጥር 27/2018 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ ለተከታታይ ቀናት በቦሌ ክ/ከተማ አስተደዳር አዳራሽ የሚከፈት ሆኖ ዝርዝሩ በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ታህሳስ 25 ቀን 2018 ዓ.ም በወጣው አዲስ ልሳን ጋዜጣ ላይ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ የጨረታ ቁጥር አ/ቃ/ክ/ከ/27/18 የቦታ ኮድ LDR-AKI-MIX-00014927 የቦታ ስፋት 992 ካሜ ተብሎ የተጠቀሰው 233 ካ.ሜ በሚል የተስተካከለ ሲሆን የቦታ ኮዳቸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በንፋስ ስልክ ላፍቶ፣ ለሚ ኩራ፣ ልደታ እና ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ በድምሩ 82 ቦታዎች ከጨረታ መሰረዛቸውን እየገለፅን መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

| ተ.ቁ | የቦታ ኮድ | ክ/ከተማ | ወረዳ | የቦታው ደረጃ | የቦታው ስፋት በካ.ሜ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | LDR-NIF-MIX-00015133 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 467 |
| 2 | LDR-NIF-MIX-00015134 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 482 |
| 3 | LDR-NIF-MIX-00015135 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 500 |
| 4 | LDR-NIF-MIX-00015136 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 500 |
| 5 | LDR-NIF-MIX-00015137 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 500 |
| 6 | LDR-NIF-MIX-00015138 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 500 |
| 7 | LDR-NIF-MIX-00015139 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 500 |
| 8 | LDR-NIF-MIX-00015140 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 500 |
| 9 | LDR-NIF-MIX-00015141 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 1/3 | 500 |
| 10 | LDR-NIF-MIX-00015142 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 2/5 | 500 |
| 11 | LDR-NIF-MIX-00015143 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 2/5 | 500 |
| 12 | LDR-NIF-MIX-00015144 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 2/5 | 500 |
| 13 | LDR-NIF-MIX-00015145 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 2/5 | 500 |
| 14 | LDR-NIF-MIX-00015146 | ን/ስ/ላፍቶ | 15 | 2/5 | 500 |
| 15 | LDR-LIMK-MIX-00015200 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 350 |
| 16 | LDR-LIMK-MIX-00015201 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 367 |
| 17 | LDR-LIMK-MIX-00015202 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 350 |
| 18 | LDR-LIMK-MIX-00015203 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 375 |
| 19 | LDR-LIMK-MIX-00015204 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 350 |
| 20 | LDR-LIMK-MIX-00015205 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 384 |
| 21 | LDR-LIMK-MIX-00015206 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 350 |
| 22 | LDR-LIMK-MIX-00015207 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 385 |
| 23 | LDR-LIMK-MIX-00015208 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 350 |
| 24 | LDR-LIMK-MIX-00015209 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 389 |
| 25 | LDR-LIMK-MIX-00015210 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 350 |
| 26 | LDR-LIMK-MIX-00015211 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 399 |
| 27 | LDR-LIMK-MIX-00015212 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 350 |
| 28 | LDR-LIMK-MIX-00015213 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 407 |
| 29 | LDR-LIMK-MIX-00015214 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 350 |
| 30 | LDR-LIMK-MIX-00015215 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 415 |
| 31 | LDR-LIMK-MIX-00015216 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 350 |
| 32 | LDR-LIMK-MIX-00015217 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 423 |
| 33 | LDR-LIMK-MIX-00015218 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 519 |
| 34 | LDR-LIMK-MIX-00015219 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/3 | 543 |
| 35 | LDR-LIMK-MIX-00015220 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 |
| 36 | LDR-LIMK-MIX-00015221 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 |
| 37 | LDR-LIMK-MIX-00015225 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 431 |
| 38 | LDR-LIMK-MIX-00015226 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 430 |
| 39 | LDR-LIMK-MIX-00015227 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 430 |
| 40 | LDR-LIMK-MIX-00015233 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 |
| 41 | LDR-LIMK-MIX-00015234 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 |
| 42 | LDR-LIMK-MIX-00015235 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 |
| 43 | LDR-LIMK-MIX-00015236 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 |
| 44 | LDR-LIMK-MIX-00015240 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 |
| 45 | LDR-LIMK-MIX-00015241 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 |
| 46 | LDR-LIMK-MIX-00015242 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 |
| 47 | LDR-LIMK-MIX-00015243 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/2 | 500 |
| 48 | LDR-LIMK-MIX-00015244 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 577 |
| 49 | LDR-LIMK-MIX-00015245 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 490 |
| 50 | LDR-LIMK-MIX-00015246 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 499 |
| 51 | LDR-LIMK-MIX-00015247 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 490 |
| 52 | LDR-LIMK-MIX-00015248 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 382 |
| 53 | LDR-LIMK-MIX-00015249 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 292 |
| 54 | LDR-LIMK-MIX-00015250 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 417 |
| 55 | LDR-LIMK-MIX-00015251 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 468 |
| 56 | LDR-LIMK-MIX-00015252 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 500 |
| 57 | LDR-LIMK-MIX-00015253 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 636 |
| 58 | LDR-LIMK-MIX-00015254 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 243 |
| 59 | LDR-LIMK-MIX-00015255 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 264 |
| 60 | LDR-LIMK-MIX-00015256 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 251 |
| 61 | LDR-LIMK-MIX-00015257 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 239 |
| 62 | LDR-LIMK-MIX-00015258 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 226 |
| 63 | LDR-LIMK-MIX-00015259 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 517 |
| 64 | LDR-LIMK-MIX-00015260 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 238 |
| 65 | LDR-LIMK-MIX-00015261 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 269 |
| 66 | LDR-LIMK-MIX-00015262 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 299 |
| 67 | LDR-LIMK-MIX-00015263 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 330 |
| 68 | LDR-LIMK-MIX-00015264 | ለሚ ኩራ | 14 | 3/4 | 297 |
| 69 | LDR-LID-MIX-00015282 | ልደታ | 8 | 1/2 | 642 |
| 70 | LDR-LID-MIX-00015283 | ልደታ | 8 | 1/2 | 500 |
| 71 | LDR-LID-MIX-00015284 | ልደታ | 8 | 1/2 | 451 |
| 72 | LDR-LID-MIX-00015285 | ልደታ | 8 | 1/2 | 500 |
| 73 | LDR-LID-MIX-00015286 | ልደታ | 8 | 1/2 | 542 |
| 74 | LDR-LID-MIX-00015287 | ልደታ | 8 | 1/2 | 801 |
| 75 | LDR-LID-MIX-00015288 | ልደታ | 8 | 1/2 | 1097 |
| 76 | LDR-LID-MIX-00015289 | ልደታ | 8 | 1/2 | 586 |
| 77 | LDR-LID-MIX-00015290 | ልደታ | 8 | 1/2 | 570 |
| 78 | LDR-LID-MIX-00015291 | ልደታ | 8 | 1/2 | 657 |
| 79 | LDR-KOL-MIX-00014981 | ኮ/ቀራኒዮ | 2 | 2/5 | 260 |
| 80 | LDR-KOL-MIX-00014982 | ኮ/ቀራኒዮ | 2 | 2/5 | 198 |
| 81 | LDR-KOL-MIX-00015020 | ኮ/ቀራኒዮ | 3 | 2/3 | 193 |
| 82 | LDR-KOL-MIX-00015022 | ኮ/ቀራኒዮ | 3 | 2/3 | 180 |

**ለተጨማሪ መረጃ የመሬት ልማት አስተዳደር ቢሮ፡- ስልክ ቁጥር +251111570595 በመደወል መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡**

## የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ

# በአዲስ ገጽታ አዲስ ትውስታ

**“ባለፈው ዓመት ለጥምቀት በርካታ ፎቶዎችን አንስቻለሁ፤ ዘንድሮም ብዙ ፎቶ አነሳለሁ ብዬ እጠብቃለሁ”**

**የፎቶ ግራፍ ባለሙያው ሙሉቀን ባዬ**

**በጊዜው አማረ**

ጥምቀት በኢትዮጵያ ከኃይማኖታዊ ስነ- ስርዓትነቱ ባለፈ፣ የጥበብ፣ የባህል እና የሕዝብ አንድነት በታላቅ ድምቀት የሚታይበት ልዩ አጋጣሚ ነው። በየዓመቱ ጥር 11 ቀን የሚከበረው ይህ በዓል፣ ኢትዮጵያን በዓለም አደባባይ በኩራት ከሚያቆሟት የማይዳሰሱ ቅርሶች መካከል አንዱ ነው።

ታቦታት ከየአቢያተ ክርስቲያናቱ ወጥተው በታላቅ ዝማሬና እልልታ ወደ ባሕረ ጥምቀቱ (ማደሪያቸው) ሲያቀኑ፣ መላው የእምነቱ ተከታይ የሆነው ህዝብ አጅቦአቸው ይወጣል። የካህናቱ ያሬዳዊ ወረብ፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ዝማሬ እና የፈረሰኞች ግልቢያ (በገጠር አካባቢ) መንገዱን ሁሉ በደስታ ይሞላዋል። ይህ በዓልና ታቦታትን አጅቦ የሚደረገው ጉዞ የምድራዊ ደስታና የመንፈሳዊ እርካታ ድብልቅ ስሜት የሚፈጥር ልዩ ትርኢት ነው።


ፎቶ- ከገፀ ድር
የበዓሉ አክባሪዎች የተነሱትን ፎቶ በመመልከት ላይ

በዚህ ምክንያት ጥምቀት በብዙዎች ልብ ውስጥ የማይረሳ የልጅነት አሻራ ጥሎ የሚያልፍ በዓል ነው ማለት ይቻላል። ከበዓሉ መንፈሳዊነት ጎን ለጎን፣ ማኅበራዊ ገጽታውና ሰዎች በበዓሉ ወቅት ያሳለፉት የልጅነትም ሆነ አዋቂነት ታሪክ ሁሌም በናፍቆት ይታወሳል።

“ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ” የሚለው ብሂል፣ በዓሉን በአዲስነትና በንጽሕና የመቀበል ባህል መግለጫ ነው። እንዲሁም ወጣቶች ምንጣፍ ለማንጠፍ የሚያደርጉት ጥድፊያ፣ የዘማሪን ጥዑም ድምጽ እና ከባሕረ ጥምቀቱ ጸበል ለመረጨት የሚደረገው ግብግብ የበዓሉን ተናፋቂነት በግልፅ የሚያመላክቱ ናቸው።

በሀገራችን ቴክኖሎጂ እየተስፋፋ ሲመጣ የጥምቀት አከባበር ትዝታን ከአዕምሮ ትውስታ በተጨማሪ በፎቶ ማስቀረት ባህል ማድረግ እየተቻለ ነው። በዚህም ወደ ፎቶ ቤት በመሄድ ፎቶ መነሳት ተለመደ፡፡ በተጨማሪም ፎቶ ግራፍ አንሺዎች ራሳቸው የጥምቀት በዓል ላይ በመገኘት ማንሳት ጀመሩ፡፡

ወይዘሮ ሰላማዊት ገብረአምላክ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት፤ በድሮ ጊዜ ፎቶ ግራፍ መነሳት እንደ ዛሬው ቀላል አልነበረም። ምክንያቱም ዘመናዊ ስልኮችና ካሜራዎች አልነበሩም፡፡ ስለዚህ ቤተሰብ አዲስ ልብሱን ለብሶ ወደ ፎቶ ቤት ይሄዳል። እዚያም በተለያዩ መልከዓ-ምድሮች (ለምሳሌ የተራራ ወይም የፏፏቴ ምስል) በተሳሉ መጋረጃዎች ፊት ለፊት ቆመው ይነሳሉ። ያ ፎቶ ታጥቦ እስኪመጣ ሳምንታት በትዕግስት ይጠበቃል።

“ለምሳሌ እኛ በጥምቀት ዕለት የተነሳናቸው ብዙ ፎቶዎች አሉን፡፡ ፎቶዎች ዛሬ ላይ የቤተሰብ ማስተዋሻ ናቸው” የሚሉት ወይዘሮ ሰላማዊት እንዲያውም አንዳንድ ፎቶዎችን በ2 እና 3 ኮፒ አሳጥበናቸው ነበር፡፡ ምክንያቱም አክስት፣ ዘመድ ወይም ጎረቤት የየራሱን ማስታወሻ መውሰድ ስለሚፈልግ እና ፎቶው ብዙ ሰው ጋር እንዲቀመጥ ለማድረግ ነው በማለት ያብራራሉ፡፡

በእርግጥም ወጣትነት፣ ወደ ውጭ የሄደ አልያም በሞት የተለዩ ዘመድ፣ የልጅነት አዲስ ልብስና ጫማ፣ ያኔ የነበረው የፀጉር አሠራር ሁሉ በእነዚያ ፎቶዎች ውስጥ ይቀመጣሉ። ፎቶው ሲታይ የተነሳበትን በዓል፣ ዕለት፣ ቦታ፣ በዕለቱ የነበረው ደስታና ድባብ ሁሉ በአዕምሮ ውስጥ ዳግም ውል ይላል፡፡

ዘመኑ በቴክኖሎጂ እያደገ ሲመጣ ሰዎች ፎቶ ለመነሳት ወደ ፎቶ ቤት ከመሄዳቸው በተጨማሪ ፎቶ ግራፍ አንሺዎች ራሳቸው ካሜራቸውን ይዘው ታቦቱ በሚያልፍበት መንገድ እና ባሕረ ጥምቀቱ አካባቢ ማንሳት ጀመሩ። ፎቶ፣ ፎቶ፣ ፎቶ... እያሉ ሕዝቡን እያስቆሙ የሚያነሱት ምስል፣ በዓሉን ይበልጥ ሕያው አድርጎት ቆይቷል። የእነ ወይዘሮ ሰላማዊትን ትዝታ ዛሬም ድረስ ህያው ካደረጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ ይኸው ፎቶ ግራፍ ነው፡፡

ዘመናዊ ካሜራዎችና ስልኮች ሲመጡ እንዲሁም በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ማራኪ መንገዶች ሲሰሩ ደግሞ ሰዎች ፎቶ ግራፎችን ከስቱዲዮ ወጣ ባለ መልኩ በመንገዶች፣ በመዝናኛ ስፍራዎችና በተለያዩ ፓርኮች ውስጥ መነሳት ጀመሩ፡፡ ቪዲዮ መቅረጽ ጀመሩ። ወጣት ማቲዎስ ታከለ እንደሚለው፣ የጥምቀት ከጓደኞቹ ጋር ፎቶ መነሳት ከጀመረ ዓመታት አልፈዋል፡፡ በእርግጥ አብዛኛውን ፎቶዎችን የሚነሳው በስልኩ ነው፡፡ በዚህም በተለያዩ የአዲስ አበባ ቦታዎች ታቦት ሲሸኝ የተነሷቸው ፎቶዎች በርካታ ናቸው፡፡

በዚህ ውስጥ ግን አንድ የተቀየረ ነገር አለ፤ ይሄውም የአዲስ አበባ ገጽታ መቀየር ነው፤ ይላል ወጣቱ፡፡ “የአዲስ አበባ አዲስ ውበት መላበስና በርካታ የፎቶ ግራፍ መነሻ ቦታዎች መኖራቸው ከዚህ በፊት ያልነበረ ነው፡፡ በፊት ፎቶ እንነሳ የነበረው በተወሰኑ ቦታዎች ነበር፡፡ አሁን ግን ከፈለግን ፏውንቴን አለ፡፡ ደስ የሚሉ አበባዎች የተተከሉባቸው መንገዶች አሉ። ታቦት ከሸኘን በኋላ ደግሞ ወደተለያዩ ፓርኮች ሄደን መዝናናት፣ ፎቶ መነሳት እና ቪዲዮ መቀረጽ እንችላለን” በማለት ማቲዎስ ያስረዳል፡፡

በእርግጥም የኮሪደር ልማቱ ለፎቶ ግራፍ ምቹ መሆን ለብዙ ወጣቶች የስራ እድል ፈጥሯል፡፡ ቀደም ሲል በቤት ውስጥ ስቱዲዮ ተወስነው ይሰሩ የነበሩ ባለሙያዎች አሁን ካሜራቸውን ይዘው በኮሪደር ልማት ወደተሰሩ ቦታዎች ወጥተዋል፡፡ በተለይም በበዓላትና በእረፍት ቀናት የፎቶ ግራፍ ባለሙያዎች ሰዎችን እያነሱ ወዲያውኑ ወደ ስልካቸው የሚልኩበት አሰራር እየተለመደ መጥቷል፡፡

ሙሉቀን ባዬ ፎቶ አንሺ ነው፡፡ በአንድ ፎቶ ቤት ተቀጥሮ መስራት ከጀመረ 6 ዓመታት አልፎታል፡፡ ከስቱዲዮ ባለፈ በእረፍት ቀናት፣ የጥምቀት፣ የኢሬቻና የመስቀል በዓላት ሲኖሩ በጎዳናዎችና በመዝናኛ ቦታዎች ፎቶዎችን ያነሳል፡፡

የፎቶ ግራፍ ባለሙያው በአስተያየቱ፣ “በበዓላት ሰዎች ከቤተሰቦቻቸው፣ ከጓደኞቻቸውና ከወዳጅ ዘመዶቻቸው ጋር ፎቶ ይነሳሉ፡፡ ባለፈው ዓመት ለጥምቀት በርካታ ፎቶዎችን አንስቻለሁ። ዘንድሮም ብዙ ፎቶ አነሳለሁ ብዬ እጠብቃለሁ” ይላል፡፡

“ዘመኑ የስማርት ስልክ እንደመሆኑ በርካቶች ፎቶ የሚነሱት በስልካቸው ነው፡፡ ይሁን እንጅ ቀላል የማይባል ሰው በካሜራ የመነሳት ፍላጎት አለው። በካሜራ ፎቶ መነሳት ለሚፈልጉ ወዲያውኑ አጥበን እንሰጣቸዋለን፡፡ አሊያም ያነሳነውን ፎቶ በብሉቱዝና በቴሌግራም ወደ ስልካቸው እንልክላቸዋለን፡፡

የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት የአዲስ አበባን ገጽታ ከመቀየር ባለፈ፣ ታቦታት በሚጓዙባቸው መንገዶች ላይ ሰፊና ምቹ የእግር መንገድ፣ ዘመናዊ መብራቶችና የከተማ ውበት ስራዎችን አካትቷል። ታቦታት ከየአብያተ ክርስቲያናቱ ተነስተው ወደ ጥምቀተ ባሕር በሚጓዙበት ወቅት፣ ምዕመናን በነጭ ልብስ አጊጠውና በዝማሬ ታጅበው የሚያደርጉት ጉዞ በአዲሶቹ ሰፋፊ መንገዶች ላይ ሲከናወን ለዓይን የሚማርክ ገጽታን ይፈጥራል፤ ይሄ ለፎቶ ግራፍ ባለሙያ ሌላ ውበትና መልክ የሚሰጥ ትዕይንት ነው” በማለት የፎቶ ግራፍ ባለሙያው ሙሉቀን ያስረዳል ፡፡

በእርግጥም አዲስ አበባ አሁን ላይ ለዓይን ማራኪ ሆናለች። በተለይም በቅርቡ የተከናወነው የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት፣ ለከተማዋ ተጨማሪ ውበትን ፈጥሮላታል፡፡ ሰፋፊ የእግረኛ መንገዶች፣ በዘመናዊ ዲዛይን የተገነቡ አጥሮች፣ ማራኪ የሆኑ አበባዎች እና የሌሊት መብራቶች ከተማዋን ልዩ ውበት አጎናጽፈዋታል፡፡ ይህ ለውጥ ደግሞ በኃይማኖታዊ በዓላት ወቅት፣ በተለይም ታቦታት ከቤተ መቅደስ ወጥተው ወደ ጥምቀተ ባሕር ሲጓዙ ወይም ወደ መንበራቸው ሲመለሱ የሚፈጥረው ድባብ ለየት ያለ ነው።

ቀደም ሲል ታቦታት በሚሸኙበት ወቅት የሚታየው ትዕይንት በጠባብ መንገዶችና በአቧራ የታጀበ ነበር። ዛሬ ግን ምዕመናን በነጭ ልብሳቸው አጊጠው፣ የቤተ ክርስቲያን መዘምራን ደግሞ በያሬዳዊ ዜማቸው እየዘመሩ በእነዚህ ውብና ንጹሕ ጎዳናዎች ላይ ሲጓዙ ማየት መንፈሳዊ ደስታን ብቻ ሳይሆን ልዩ የሥነ-ልቦና እርካታን ይሰጣል። መንገዶቹ መጽዳታቸውና መዋባቸው ምዕመኑ በነፃነት እንዲንቀሳቀስና ታቦታትን እንዲሸኝ እድል ፈጥሯል ማለት ይቻላል። ይህ በአዲስ አበባ ኮሪደሮች ላይ የሚታየው ትዕይንትና የበዓላት ፎቶ ግራፎች ለሰዎች እንደ ማስታወሻ ከማገልገሉም በተጨማሪ ለታሪክ ተመራማሪዎችና ለነገው ትውልድ ትልቅ ትርጉም አለው። ከተማዋ በምን ዓይነት ፍጥነት እየተለወጠች እንደሆነ እንዲረዳ ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሕዝቡ ከዚህ ለውጥ ጋር እንዴት እንደተዋሃደ የሚያሳይ ህያው ምስክር የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ ነው። ታቦት እየሸኙ የሚነሱ ፎቶዎች በቤተሰብ አልበም ውስጥ ሲቀመጡ፣ ከዓመታት በኋላ ልጆች “በዚህ ዓመተ ምህረት አዲስ አበባ እንዲህ ነበረች?” ብለው እንዲጠይቁና እንዲደነቁ ያደርጋቸዋል።

ይህ የሚያሳየው የኮሪደር ልማቱ ያመጣው ትልቁ ስኬት ቁሳዊ ለውጥ ብቻ ሳይሆን፣ የማህበረሰቡን ስነ- ልቦና ማደሱ ነው። ሰዎች በከተማቸው እንዲኮሩ፣ ኃይማኖታዊ ስርዓታቸውን በክብርና በውበት እንዲያከብሩ እድል ሰጥቷል። በአጭሩ፣ በአዲስ አበባ ውብ ጎዳናዎች ላይ ታቦት ማጀብና ያንን ቅጽበት በፎቶ ማኖር፡ መንፈሳዊ እርካታን፣ የውበት አድናቆትን እና የማይረሳ የታሪክ ትውስታን በአንድ ላይ ለማግኘት ያስችላል ይላል የፎቶ ግራፍ ባለሙያው ሙሉቀን፡፡

በአጠቃላይ የኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶች አዲስ አበባን የጥበብና የውበት መድረክ ጭምር አድርገዋታል። ፋውንቴኖቹ፣ አበቦቹና ዘመናዊው የመንገድ ዳር ግንባታዎች የከተማዋን ነዋሪዎች የስነ-ልቦና እርካታ ከመጨመር ባለፈ፣ የፎቶ ግራፍ ጥበብ እንዲያብብ ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ነው። ይህ ውበት ዘላቂ እንዲሆን ደግሞ የመንገዶችን፣ የመዝናኛ ስፍራዎችን፣ የአበቦችንና የፋውንቴኖችን ውበት ጠብቆ ማቆየት የሁሉም ኃላፊነት ነው፡፡

# የመዲናዋ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች እና አዳዲስ ጥበባዊ ስራዎች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም የተለያዩ ጥበባዊ መሰናዶዎች ይደረጋሉ፡፡ ከተሰናዱ ዋና ዋና ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች መካከል የሃሳብ እና መጽሐፍ ውይይት፣ ሙዚቃ፣ የፎቶ ግራፍ እና የሥዕል አውደ ርዕይ፣ የቴአትር መርሃ ግብር እና ሌሎች መሰናዶዎች ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## ፌስቲቫል

ኢትዮጵያዊ ምግቦች የሚቀርቡበት ፌስቲቫል ክፍት ሊሆን ነው። “ጋስትሮኖሚ” የተሰኘውን ይህን ፌስቲቫል የአዲስ አበባ ቱሪዝም ኮሚሽን ጎልደን ግሩፕ ሆስፒታሊቲ ከተሰኘ ድርጅት ጋር አዘጋጅቶታል፡፡ ዛሬ እና ነገ ክፍት የሚሆነውን ይኸን ፌስቲቫል የውጭ ሀገር ዜጎችን ጨምሮ ከ20 ሺህ በላይ ሰዎች ይጎበኙታል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ፌስቲቫሉ የተዘጋጀው ደግሞ በሚሊኒየም አዳራሽ እንደሆነ የአዲስ አበባ ቱሪዝም ኮሚሽነር ሁንዴ ከበደ ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ኤፍ ኤም 96.3 ራዲዮ ገልጸዋል፡፡

## መጽሐፍት

“የፍልስፍና ሐሳቦች” የተሰኘው የትርጉም መጽሐፍ ለንባብ በቃ፡፡ ይህ መጽሐፍ ስድስት መጻሐፍትን በአንድ ጥራይዝ የያዘ መሆኑ ተገልጿል፡፡ የመጽሐፉ ተርጓሚ ሙሉቀን ታሪኩ ሲሆን አርትኦቱ የተሰራው ደግሞ በፋሲካ ግዛውና አማረ ብርሃኑ ነው፡፡

በተጨማሪም በደሳለኝ ከበደ (ኢ/ር) የተጻፈው “የሪል እስቴት ግብይት” መጽሐፍ ታትሞ ለንባብ በቅቷል። ደራሲው ከዚህ ቀደም “ሪል እስቴት ኢንቨስትመንት” የሚል መጽሐፍ ለንባብ ለአንባቢያን ማድረሱ ይታወሳል። አዲሱ መጽሐፍ ለቤት ገዢዎች፣ ለግብይት ወኪሎች (ኤጀንቶች)፣ ደላሎች፣ ለሻጮች እና ለቤት አልሚዎች ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን፣ በሪል እስቴት ገበያ ውስጥ የግብይት ጥረቶችን ውጤታማ ለማድረግ የሚረዱ አዳዲስ ስልቶችን እና ውጤታማ ቴክኒኮችን ያያዘ ነው ተብሏል። በተጨማሪም የግብይት አካሄዶችን ውጤታማ ለማድረግ፣ የሽያጭ ዘዴን እና የአልሚነት ፕሮጀክቶችን ለማሻሻል፣ ገዢዎችንም ለመሳብ የሚረዱ ሃሳቦችን ማካተቱ ተነግሯል፡፡

በሌላ መረጃ “ሸግዬ ሸጊቱ” የተሰኘው መጽሐፍ ለ3ኛ ጊዜ ታትሞ ለንባብ በቅቷል፡፡ በሚካኤል አስጨናቂ የተጻፈውና ተወዳጅነትን ያተረፈው ይኸው መጽሐፍ የአጫጭር ልቦለዶች ስብስብ ነው፡፡

## የሃሳብ ውይይት

በዛሬው እለት “የሃሳብ እና መፅሐፍ” ውይይት መድረክ ይካሄዳል፡፡ ውይይቱ ስለ ቀለም አይነት እና ትርጓሜ፣ ስለ ቀለም ፅብረቃ እና በስነ-ልቦና ላይ ስለሚያደርሱት ልውጥውጥ ስሜቶች፣ ስለ መልክ እንዲሁም ስለ ምልክቶች በተጨማሪም ስለገፅታ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

የውይይት መነሻ ሃሳብ የሚያቀርቡት ኢንጂነር ጌታሁን ሄራሞ (ቀለም ፊሎሶፊ) እና ሰዓሊ ሶሎሜ ጌታቸው ናቸው፡፡ ውይይቱ የሚካሄደው 4 ኪሎ ኢክላስ ህንፃ ዋልያ መጽሐፍት አዳራሽ ሲሆን ከሰዓት 8:00 ሰዓት ጀምሮ መርሃ ግብሩ መካሄድ ይጀምራል ተብሏል።




ፎቶ- ከገፀ ድር

በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## የፎቶ ግራፍ አውደ ርእይ

“በቅጽበቶች መካከል” የተሰኘው የስእል አውደ ርእይ በእይታ ላይ ነው። አሸናፊ የማነ፣ ርብቃ ሲሳይ እና ልዑል መኮንን በጋራ ያዘጋጁት ይህ አውደ ርእይ የተጀመረው ባሳለፍነው ረቡዕ እለት ነው። አውደ ርእይው እስከ ጥር 30 ቀን 2018 ዓ.ም የሚቆይ ሲሆን እየታየ የሚገኘው በሀያት ሪጀንሲ ሆቴል በሚገኘው ፈንድቃ የባህል ማእከል ነው።

## ሙዚቃ

ድምጻዊ ብዙአየሁ ደምሴ አዲስ የሙዚቃ ስራ ለአድማጭ ተመልካች ሊያደርስ ነው፡፡ ቀደም ሲል በሰራቸው በርካታ ሙዚቃ ስራዎች ተወዳጅነትን ያተረፈው ድምፃዊ ብዙአየሁ ደምሴ አሁን ደግሞ “መሸቶ ነጋ” የተሰኘ ሙዚቃ ወደ ህዝብ ለማድረስ ዝግጅቱን መጨረሱ ተሰምቷል፡፡ ከዚህ ቀደም “ሳላይሽ” አልበሙን ለህዝብ ያደረሰው ድምፃዊ አሁን ደግሞ ይኸን አዲስ ነጠላ ዜማውን በናሆም ሪከርድስ አማካኝነት ለህዝብ እንደሚያደርስ ተገልጿል፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የመጀመሪያው $6 \times 8 \div 4 = 12$ ይሆናል፡፡ የሁለተኛው ደግሞ $8 \times 9 \div 4 = 18$ ነው፡፡ በዚህ አመክንዮ (Logic) መሰረት ሶስተኛውና የመጨረሻው $6 \times 10 \div 4 = 15$ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር **15** ነው።




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል። በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# በዓል አድማቂዎቹ የእጅ ጥበቦች

**• የባህል ልብስ ኢንዱስትሪው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር እንደ ጥምቀት ያሉ ሕዝባዊ በዓላት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ተጠቁሟል**

**በአብርሃም ገብሬ**

“ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ!” የሚለው የቆየ ብሂል ኢትዮጵያውያን ለበዓሉ ያላቸውን ክብር ብቻ ሳይሆን፣ አልባሳት ለማኅበራዊ መስተጋብራቸው ያላቸውን ከፍተኛ ቦታ ፍንትው አድርጎ ያሳያል። ጥምቀት ኃይማኖታዊ ሥነ-ሥርዓት ብቻ ሳይሆን፣ የኢትዮጵያ ባሕላዊ የፋሽን ትርኢት በአደባባይ የሚታይበት ታላቅ መድረክ ነው። ህጻናት፣ ወጣቶችና በእድሜ ከፍ ያሉ የክርስትና እምነት ተከታዮች ጥምቀትን አንድም ይባረኩበታል፤ አንድም መስክ ላይ ፈክቶና አብቦ እንደሚታየው የጥቅምት አበባ አደባባዮቹን በውብ የባህል አልባሳት ደምቀው ይታዩበታል፡፡ የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍልም የእነዚህን አልባሳት፣ ውበት፣ ዲዛይንና ቀለም ከሥነ ጥበብ አንጻር በጨረፍታ እንደሚከተለው ዳስሶታል፡፡





ፎቶ- ከገፀ ድር

የጥበብ ውበትን ከሚያንፀባርቁ የጥምቀት አልባሳት ከፊሎቹ

## ውበት፣ ቀለምና የባህል አልባሳት በጥምቀት ሰሞን

በኢትዮጵያ ምድር ጥር 11 ቀን ሲመጣ አየሩ ሁሉ ይቀየራል። የከተራው ዋዜማ ጭብጨባና ዕልልታ፣ የታቦታቱ ጉዞ፣ የካህናቱ ያሬዳዊ ዝማሬ እና ሕዝቡ በባህል አልባሳት አጊጦ በአደባባይ መንቀሳቀሱ ሀገሪቱን በልዩ መንፈስ ይሞላታል። ከዚህ አንጻር ጥምቀት ለኢትዮጵያውያን ኃይማኖታዊ ሥነ- ሥርዓት ብቻ ሳይሆን፤ ከዚያ በላቀ መልኩ ብሔራዊ ማንነት የሚታደስበት፣ ማኅበራዊ ትስስር የሚጸናበት እና የሥነ ጥበብ ክህሎት በአደባባይ የሚመሰከርበት ታላቅ ማህበራዊ በዓል ነው።

ጥምቀት በክርስትና እምነት ተከታይ ኢትዮጵያውያን ዘንድ የትውስታ ማህደራቸው ላይ ግዙፍ ቦታ የያዘ ታላቅ በዓል ነው፡፡ ምንም እንኳን በዓሉ ኃይማኖታዊ ዳራ ያለው ቢሆንም፣ እሱን ተከትሎ ተግባራዊ የሚደረጉ ባህላዊ ክዋኔዎች የበለጠ ድምቀት አጎናጽፈውታል፡፡ ሀገራችን ባህለ-ብዙ መሆኗን በሚገልጽ አኳኋን እንደየአካባቢው ወግና ልማድ ኃይማኖታዊ ዳራውን ሳይለቅ በዓሉ በድምቀት ይከበራል፡፡

ምንም እንኳን የጥምቀት አከባበር ለጎልማሶችና ለአዛውንቶች ታላቅ ትዝታ የያዘ ቢሆንም፤ ለህጻናትና ለወጣቶች ደግሞ ዛሬ ላይ እየተደሰቱ የሚኖሩት እጅግ ተናፋቂ በዓል ነው፡፡ ለዚህ ይመስላል፤ እጅግ አዳዲስ ትዕይንቶችንና ክዋኔዎችን በማከል የጥምቀት በዓል አከባበር ዛሬም እምር ብሎ በአደባባይ መከበሩን የቀጠለው፡፡ በተለይ በህብረ-ቀለማት የአሸበረቁ አልባሳት ለብሰው የሚታዩ ወጣቶችና ሌሎች የበዓሉ አክባሪዎች የበዓል ትዕይንቱን ይበልጥ ተናፋቂ ያደርገዋል፡፡

ራሄል አበራ ተወልዳ ያደገችው ጥቁር አንበሳ አካባቢ ነው፡፡ ይህ አካባቢ የጥምቀት በዓል በድምቀት ከሚከበርባቸው አካባቢዎች መካከል አንዱ እንደሆነ አጫውታናለች፡፡ የጎላ ሚካኤል ታቦትን አጅባ ብዙ ጥምቀቶችን አክብራለች፡፡ አሁን ላይ የምትኖረው ፈረንሳይ ሌጋሲዮን ኬላ የሚባል አካባቢ ነው፡፡ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ከአንዱ በስተቀር አራቱን የጥምቀት በዓል ያከበረችው ተከራይታ በምትኖርበት ፈረንሳይ ሰፈር ነው፡፡ ራሄል የጥምቀት በዓልና የባህል አልባሳትን በሚመለከት ተሞክሮዋን ለአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል አጋርታለች፡፡ ራሄል በአስተያየቷ፣ “ጥምቀት ማህበራዊ መስተጋብር የሚያጠናክር፣ ለልጆችና ለወጣቶች ትልቅ ነጻነትና ደስታ የሚሰጥ በዓል ነው። ልጅ ሆኜ ጥምቀትን በአዲስ ልብስ ነበር የማከብረው፡፡ አባቴ ለእኔና ለወንድሞቼ ለጥምቀት አዲስ ልብስ ይገዛልን ነበር፡፡ በበዓሉ አዲስ ልብስ የመልበስ አዝማሚያ ዛሬም እንደቀጠለ ነው” ብላለች፡፡

ራሄል የዘንድሮውን የጥምቀት በዓል ለማክበር አዲስ ልብስ አሰፍታለች። ከቅርብ ሴት ጓደኛዋ ጋር በመሆን ነው ልብሱን አስቀድመው ያሰፉት። የባህል አልባሳት ዲዛይን እጅግ መሻሻሉን ያነሳችው ራሄል፣ “ዋጋው ግን ትንሽ እየተወደደ ነው፡፡ ቢሆንም ግን ጥምቀት ያለ ባህላዊ አልባሳት የሚደምቅ አይመስለኝም፡፡ ከልጅነታችን ጋር የተያያዘ ስለሆነ በጥምቀት በዓል አዲስ ዲዛይን የተደረገ ልብስ ማሰራቷን” መቼም እንደማታቆም ተናግራለች፡፡ ለጥምቀት የማሰራቸው ልብሶች ጥምቀት ካለፈ በኋላም እንደምለብሳቸው ታሳቢ በማድረግ ነው ዲዛይን የማደርገው፡፡ በተለይ የሳምንቱ ዕረፍት ቀናትና ሌሎች የበዓል ቀናትም ስለምለብሳቸው፣ ለዚህ የማወጣው ወጪ ያን ያህል አያሳስበኝም ብላለች፡፡

በእርግጥ የጥምቀት በዓል ፋይዳ ከአዳዲስ አልባሳት ያለፈ ትልቅ ሀገራዊ ዕሴታችን ነው፡፡ የጥምቀት በዓል ትልቁ ማኅበራዊ ፋይዳው መሰባሰብ ነው። በዘመናዊው ዓለም ግለኝነት (Individualism) እየነገሰ በመጣበት ወቅት፣ በጥምቀት ግን በርካታ ሰዎች በአንድ እንዲሰባሰቡ ያደርጋል፡፡ ሁሉም በነጭ ባሕላዊ ልብስ ተውቦ፣ በአንድነትና በነጻነት ይሳተፋል። በአደባባይ የሚከበረው ይህ በዓል የማኅበራዊ መደብ ልዩነት የማይስተዋልበት በመሆኑ ሀገራዊ ፋይዳው ትልቅ ነው፡፡

የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል የጥምቀት በዓል አከባበርና የባህል አልባሳት መልክና ገጽታን በሚመለከት ዲዛይነርና የባህል አልባሳት የሚሰራው ፀጋዬ ስሜነህን አነጋግሯል፡፡ ዲዛይነር ፀጋዬ ለዓመታት የባህል አልባሳት ሰሪ፣ ዲዛይነርና ሻጭ ነው፡፡ መርካቶ ሸማ ተራ ውስጥ ለዓመታት የባህል አልባሳት ሰርቷል፡፡ አሁን ላይ ቀጨኔ መድሐኒዓለም አካባቢ የባህል አልባሳት ዲዛይን ያደርጋል፡፡ ዲዛይን ያደረጋቸውን ልብሶች በመስራት ለለባሽ ብቻ ሳይሆን የባህል አልባሳት ለሚሸጡ ሰዎች ጭምር ይሸጣል፡፡

ዲዛይነር ጸጋዬ ስለ ጉዳዩ በሰጠው አስተያየት፣ “በጥምቀት ዕለት የሚለበሱት አልባሳት ተራ ጨርቆች አይደሉም። እያንዳንዱ ጥልፍ፣ ጥበብ እና ዲዛይን የአንድን ማኅበረሰብ ታሪክና ጥበብ ይተርካል። ወጣቶች፣ አዛውንቶችና ሕፃናት እንደ አካባቢያቸው ባህል ለብሰው ጥምቀትን ለማክበር ወደ አደባባይ ሲወጡ፣ ሀገሪቱ በአንድ ጊዜ የፋሽን ሳምንት እያከበረች ይመስላል። በየዓመቱ የጥምቀት በዓል ላይ በአደባባዩ የሚታየውም ይኸው ትዕይንት ነው ብሏል፡፡

የጥምቀት በዓል ለዲዛይነሮችና ለሀገር ባህል አልባሳት ሰሪዎች ትልቅ የደንበኛ ማፍሪያና የፈጠራ ማሳያ ነው የሚለው ዲዛይነር ጸጋዬ፣ አዳዲስ የጥበብ ቅርፆች የሚታዩትና የሕዝቡን ቀልብ የሚስቡት በዚህ ወቅት ነው። ይህም የባሕል ልብስ ኢንዱስትሪው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር እንደ ጥምቀት ያሉ ሕዝባዊ በዓላት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳላቸው አጫውቶናል፡፡

ጥምቀትን ተከትሎ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በቡድንና በተናጠል በመሆን የሀገር ባህል አልባሳት ለብሶ መታየት እየተለመደ መምጣቱን በማስታወስ፤ በዚህ ልክ ተወዳጅ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ምክንያት ምንድ ነው? ሲል የዝግጅት ክፍላችን ላቀረበለት ጥያቄ ዲዛይነር ፀጋዬ ሲመልስ፣ “የባህል አልባሳት በብዛት ተፈላጊነታቸው የሚጨምረው ለጥምቀት በዓል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሌሎች በዓላትም ላይ የባህል አልባሳት የበዓል አድማቂዎች ናቸው፡፡ እኔም ለበዓላት በቋሚነት ልብስ የምሰራላቸው ደንበኞች አሉኝ። ደንበኞቼ በዓል በመጣ ቁጥር ትልቁ ፍላጎታቸው ከዚህ ቀደም ያልተለመደ አዲስ አይነት የባህል አልባሳት ዲዛይን እንዳደርግላቸውና እንድሰራላቸው ይፈልጋሉ፡፡ ለዚህ ነው የባህል አልባሳት ገበያ ላለፉት ዓመታት ሞቅ ደመቅ እንዲል ምክንያት የሆነው” ብሏል፡፡

ዲዛይነር ጸጋዬ እንዳጫወተን፣ የጥምቀት አልባሳት መሠረታቸው የ“እጅ ጥበብ” ነው። በኢትዮጵያ ባሕላዊ አልባሳት ውስጥ “ጥበብ” የሚለው ቃል ሁለት ትርጉም አለው፤ አንደኛው የልብሱ ጠርዝ ላይ የሚሠራው ያሸበረቀ ዲዛይን ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የባለሙያው ክህሎት ነው። በቀደመው ዘመን የጥምቀት ልብሶች በዋናነት የሚሰፉት ከነጭ የጥጥ ድርና ማግ ነበር። ይህ ነጭነት የመንፈሳዊ ንጽህና እና የደስታ ምልክት ተደርጎ ይወሰድ እንደነበር ዲዛይነር ጸጋዬ አጫውቶናል፡፡

በጥምቀት በዓል ወቅት የሚታዩ ቀለማት በዘፈቀደ የሚመረጡ አይደሉም የሚለው ጸጋዬ፣ እያንዳንዱ ቀለም የራሱ የሆነ ትርጉም አለው፡፡ ለምሳሌ ነጭ ቀለም በበዓሉ ጎልቶ የሚታይ ቀለም ነው። ይሄ ነጭ ቀለም ንጽህናን፣ ሰላምንና ብርሃንን ይወክላል። ወርቃማና ቢጫ ቀለሞችም የበዓሉ ሌላኛው መገለጫ ናቸው፡፡ በባህላዊ አልባሳት ዲዛይኖች ውስጥ ወርቃማና ቢጫ ቀለሞች መጠቀም የባለቤቱን ማኅበራዊ ደረጃና የክብረ በዓሉን ታላቅነት ያሳያል ብሏል።

የባህል አልባሳት ለዝነጣ እንዲመቹና ዘመኑን እንዲመስሉ ተደርገው ዲዛይን መደረጋቸው በተለይ የወጣቱ ፍላጎት እንዲጨምር እንዳደረገ የሚናገረው ዲዛይነር ፀጋዬ፣ በዚህ ላይ ወጣ ያለና ሰው እንደፍላጎቱ የሚሆንለትን የባህል አልባሳት ለማሰራት እድል ስለፈጠረለት አልባሳቱን ይበልጥ ተመራጭ አድርጓቸዋል። በሰርግና በመልስ ጊዜ ሳይቀር የባህል አልባሳት እየተመረጡ ናቸው፡፡ ይህም ሀገራዊ እውቀትና የግለሰቡ ጥረት ከተጣመሩ ብዙ ሀገራዊ ጉዳዮቻችንን ለማዘመንና ዘመኑን እንዲዋጁ ለማድረግ ጥሩ ማሳያዎች እንደሆኑ አጫውቶናል፡፡

በአጠቃላይ የጥምቀት በዓል ከኃይማኖታዊ ስርዓቱ ባለፈ በውስጡ የያዘው ማኅበራዊ እሴት ወደር የለውም። የዕምነቱ ተከታዮች አጊጠውና ተውበው በአደባባይ መታየታቸው በራስ ባሕል መኩራትና ለህዝባዊ አንድነት መጠናከር የሚሰጠው ፋይዳ ከፍተኛ ነው። ጥምቀት የኢትዮጵያዊነት ድምቀት፣ የእደ ጥበብ መፍለቂያና የአብሮነት ማሳያ ሆኖ ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገረ እዚህ ድረስ መምጣቱ የበዓሉ ታላቅ ዕሴትነት አንዱ ማሳያ ነው፡፡

# አዕምሮን የሚያድሱ መናፈሻዎች

- በአዲስ አበባ 126 ፓርኮች አሉ ፤ ከእነዚህ ውስጥ 104ቱ ኮሪደር ልማቱ ያስገኛቸው አዳዲስ መናፈሻዎች ናቸው



ፎቶ- በገነት ወንድሙ

የአምባሳደር ፓርክ ውስጣዊ ገጽታ በከፊል

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ኮሪደር ልማቱ መልካም አጋጣሚን ከፈጠረላቸው መካከል ፓርኮች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ አዳዲስ ፓርኮች ቁጥራቸው እንዲበራከት ከማድረግ ባለፈ ነባሮችን ወቅቱን በሚመጥን መልኩ የማልማት ስራ ውጤቱ በተጨባጭ እየታየ መሆኑን አምባሳደር ፓርክን በማሳያነት ማንሳት ይቻላል፡፡ የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ "የአዲስ አበባ ወንዞች ትንሳኤ" በሚል ርዕስ በተሰራው ዘጋቢ ፊልም ላይ ይኸንኑ የሚያጠናክር አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ ከተማን እንደ አዲስ መስራት ብቻ ሳይሆን ነባሮቹንም ከዘመኑ ጋር አብረው እንዲሄዱ አድርጎ ማደስና የተበላሸውን ማስተካከል፣ የጎደለውን ማፅዳትና መሙላት እንደሚቻል አምባሳደር ፓርክ በማሳያነት እንደሚጠቀስ ከንቲባዋ ተናግረዋል፡፡

"አምባሳደር ፓርክ የቁርጡሚ እና የቀጨኔ ወንዞች ቆሻሻ ይዘው እየመጡ ሰው እንዳይጠቀምበት አድርገውት ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ወንዞቹ የራሳቸው ማጣሪያ አላቸው፡፡ ፓርኩም ታድሷል ብቻ ሳይሆን እንደ አዲስ ተገንብቷል። አንዱ እንምጣበት ተብሎ የሚጓጓበት ትልልቅና የሚያማምሩ ዛፎች ጭምር ያሉበት ነው" በማለት ነዋሪዎች ፓርኩን እንዲጎበኙት፣ እንዲዝናኑበትም ጭምር ጋብዘዋል፡፡ የዝግጅት ክፍላችን ወደ ስፍራው በማቅናት ምልከታ አድርጓል እና ሰዎችንም አነጋግሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መሰል ፓርኮችን በማበራከት ረገድ እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የመንግስት አካላት አነጋግሯል፡፡

ወጣት ሽኩር ባቲን በአምባሳደር ፓርክ የመግቢያ ገንዘብ ተቀባይ ነው። በፓርኩ ከአንድ ዓመት በላይ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ፓርኩ ከኮሪደር ልማቱ ጋር ተያይዞ ከመታደሱ በፊት የነበረው ገፅታ "ለመዝናናት የማይመች፣ ቆሻሻ ወንዝ ያለበት ነበር፡፡ ፋውንቴኑ ቢኖርም አገልግሎት አይሰጥም ነበር፡፡ ይህም በመሆኑ ጥሩ ነገር ለማየትና ለመዝናናት ከፍለው የሚገቡ ሰዎች እንደጠበቁት ስለማይሆንላቸው ተበሳጭተው ይወጣሉ፡፡ የልጆች መጫወቻ እንዲሁም ለዓይን የሚስብ አበባና ሳር ያልነበረውና ማረፊያ ወንበሮቹን አዕዋፋት ያቆሸሹት ነበር፡፡ ንፁህና በቂ መፀዳጃ ቤትም አልነበረውም፡፡ በአጠቃላይ ለመዝናናትም ሆነ አዕምሮን ለማሳረፍ ምቹ ሳይሆን ቆይቷል" ሲል ገልጾታል፡፡

"አምባሳደር ፓርክ እድሳት ከተደረገለት በኋላ ሳቢና ማራኪ ሆኗል። ከዚህ በፊት ያልነበሩ ማረፊያ ወንበሮች፣ የልጆች መጫወቻዎች፣ መፀዳጃ ቤት፣ አበባና ለምለም ሳር... ተሟልተውለታል፡፡ የሚዝናኑ ሰዎችም እንደ በፊቱ ተሳድበው ሳይሆን ተደስተውና አመስግነው ነው የሚወጡት፡፡ በፊት እንደገቡ ወዲያውኑ ነበር ተመልሰው የሚወጡት፤ በአሁኑ ወቅት ግን ጠዋት ከገቡ እስከ ማታ ድረስ ነው የሚቆዩት፡፡ የግቢው ፅዳት፣ የውሃ አገልግሎቱ በአጠቃላይ ምቹ በመሆኑ እኛም ገንዘብ የምናስከፍለው አንገታችንን ሳንደፋ በደስታ ነው" ሲል እድሳቱ ለተገልጋዮችም ሆነ ለፓርኩ ሰራተኞች ምቹ መሆኑን ነግሮናል፡፡

ወጣት ምህረት ወጣንም ያገኘናት በፓርኩ በዛፉ ጥላ ስር በተመስጦ ተቀምጣ ራሷን ስታዳምጥ ነው፡፡ ፓርኩ ከመታደሱ በፊትም ለመዝናናት ትመጣ ነበር፡፡ የቀደመ ገጽታውን ከአሁኑ ጋር በማነጻጸር ስትገልጽም፣ "ምቹ ያልነበረና ንፅህናውም ያልተጠበቀ ነበር፡፡ ፀሐዩም ያስቸግራል፡፡ ውስጥ ላይ እንድንቆይ የሚስብ ነገር አልነበረም" ስትል ታስታውሳለች፡፡ በአሁኑ ወቅት መፀዳጃ ቤቱ፣ ማረፊያ ወንበሮቹ፣ አበቦቹ፣ ሳሩ ቀልብን ይስባሉ፡፡ በስራ ሲደክመኝና ሃሳብ ሲበዛብኝ በዚህ ቦታ መጥቼ የጥሞና ጊዜ አሳልፋለሁ፡፡ አንዳንዴ ከጎደኞቼ ጋር የመምጣት ልምድም አለኝ፡፡ በነፋሻማ አየሩ የአዕምሮ ሰላም አገኛለሁ፡፡ የኮሪደር ልማቱ እና እድሳቱ ተዳምረው ለአካባቢው ውበትን አላብሰውታል፡፡ በዚህም ወደ ፓርኩ በመምጣቴ ተዝናንቼና ደስተኛ ሆኘ እመለሳለሁ" ብላለች፡፡

የሰባት ዓመት ህፃን ልጃቸውን ይዘው እየተዟዙ ፓርኩ ውስጥ ያለውን ፋውንቴን ሲያሳዩት ያገኘናቸው ደግሞ አቶ ያሲን አብዲ ናቸው፡፡ በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ህጻን ልጃቸውን ሊያሳክሙ ከክፍለ ሀገር መምጣታቸውን ነገሩን፡፡ "ለየት ያለ ነገር ተመልክቻሁ፤ አየሩ፣ የአይን ማረፊያ የሆኑት ዛፎቹና ሳሩ በዚሁ ውለን ብናድር የሚሰለቹ አይደሉም፡፡ በህክምና ተቋሙ የነበረውን ጭንቀት እና መሰል ውጥረቶች በዚህ ተወግዶልኛል፡፡ ልጄም ደስታው ወደር የለውም፡፡ በሌላ ቦታ ብዙ ገንዘብ ከማውጣት በትንሽ ብር መዝናናትና መደሰት የሚቻልበት ቦታ ነው" ብለዋል፡፡

"መዝናናት ብዙውን ጊዜ በስራችንና በህይወታችን የሚያጋጥሙንን ችግሮች ለመቋቋም ይረዳል፡፡ በዚህም ከመጣሁበት አካባቢ እንዲህ አይነት ቦታዎች ቢኖሩ ብዬ ተመኘሁ" ሲሉም አቶ ያሲን አክለዋል፡፡

ወይዘሮ ቤተልሔም አበራ የአምባሳደር ፓርክ ማናጀር ናቸው፡፡ የአምባሳደር መናፈሻ በኮሪደር ልማቱ አማካኝነት ከታደሰ በኋላ እየሰጠ ያለውን አገልግሎት በተመለከተ በሰጡን ማብራሪያ፤ ፓርኩ ለሚዝናኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ምቹ፣ ደረጃውን ጠብቆ እና መሟላት ያለባቸው ነገሮች ተሟልተውለት ታድሷል። በዚህም በፓርኩ ለህፃናት የሚሆኑ መጫወቻዎች፣ የደከመ አካልንና አዕምሮን ጭምር ማሳረፊያ ወንበሮች፣ ዓይንን የሚስብ ፋውንቴን፣ የማታ ፍካት የሆኑ መብራቶች፣ መፀዳጃ ቤት፣ ምግብ ቤት፣ የጀበናና የማሽን ቡና የያዘ የካፍቴሪያ አገልግሎት እንዲሁም ስልክንም ይሁን ላፕቶፕን ቻርጅ ማድረጊያ ሶኬቶች የተሟሉለት ነው፡፡

እንደ ማናጀሯ ገለጻ፣ ፓርኩ ህፃናት የሚጫወቱበት፣ መፃሕፍት የሚያነቡበት፣ የተለያዩ ዝግጅቶች የሚደረጉበት፣ ወላጆች የልጆቻቸውን ልደት የሚያከብሩበት፣ ሙሽሮች የፎቶ መርሃ ግብር የሚያካሂዱበትና የውጭ ሀገር ዜጎች ጭምር የሚዝናኑበት ነው፡፡

በፓርኩ ማህበረሰቡ ንፁህ አየር መቀበል የሚችልበት፣ ሊዝናና የመጣ ሰው ያለገደብ መዝናናት የሚችልበት፣ ከመደበኛ ምግብ ውጭ ማታ ላይ ለሚመጡ ችፕስ፣ ፒዛና በርገር የሚያገኙበት፣ ጥሩ ጊዜ የሚያሳልፉበት መሆኑን የነገሩን ማናጀሯ፤ "ለዚህም የሚመጡ ደንበኞች ምስክር ናቸው። በስራ ቀን ከ60 እስከ 70 እንዲሁም ቅዳሜና እሁድ ቁጥራቸው ባይታወቅም በርከት ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎች በፓርኩ ይዝናናሉ፡፡ ከክፍያ ውጭ ምሳ ለመመገብ የሚገቡ ሰራተኞችም ብዙ ናቸው" ሲሉ እየሰጠ ያለውን አገልግሎት ገልፀውልናል፡፡ ነዋሪዎች የመንፈስ ደስታ፣ የስሜት እርካታ አግኝተው እንዲመለሱ ከልጆች መጫወቻ ጋር ተያይዞ ኬክ እና አይስክሬም እንዲሁም ስጋ ቤት ለመክፈት የወደፊት እቅድ እንዳላቸውም አክለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ እድሳት የተደረገላቸው የህዝብ መናፈሻና መዝናኛ ፓርኮች እየሰጡት ያለውን አገልግሎት አስመልክቶ ለዝግጅት ክፍላችን ማብራሪያ የሰጡት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህዝብ መዝናኛ ቦታዎች አስተዳደር ኮርፖሬሽን የምህንድስና ዘርፍ ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ገረመው ወርቁ ናቸው፡፡ እንደ እርሳቸው ገለጻ፣ በአዲስ አበባ ነባርና ከኮሪደር ልማቱ ጋር ተያይዞ ብዙ ፓርኮች ለምተው ወደ ስራ ገብተዋል፡፡ እነዚህ ፓርኮች ማህበረሰቡ እንዲጠቀምባቸው ምቹ እየተደረጉ ነው፡፡

እነዚህ እድሳት የተደረገላቸው ፓርኮች የከተማዋን አጠቃላይ ገፅታ የሚቀይሩ፣ በኢኮኖሚውም የራሳቸው ጉልህ ፋይዳ ያላቸው ናቸው፡፡ እንጦጦ ፓርክ፣ ፒኮክ መናፈሻ፣ አምባሳደር ፓርክ፣ የኮሪያ ዘማቾች መታሰቢያ ፓርክ፣ ሃምሌ 19 ፓርኮች እድሳት የተደረገላቸው መሆኑን የገለፁት ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚው፤ እነዚህም በሚጠበቀው አግባብ ወይም ዘመኑ በደረሰበትና ትውልዱ በሚፈልገው አንፃር የታደሱና እየታደሱ ያሉ ናቸው፡፡

እድሳቱ ተጠናቅቆ ወደ ስራ የገባው በመሃል ከተማ የሚገኘው አምባሳደር ፓርክ ከመታደሱ በፊት በፅዳቱ፣ ውስጥ ላይ በነበሩ መሰረተ ልማቶች በጣም የተጎዳና ለማህበረሰቡም ተገቢውን አገልግሎት ሳይሰጥ የቆየ ነበር፡፡ ይህንንም መነሻ በማድረግ እድሳት የተደረገለት ፓርኩ፤ የመናፈሻ፣ የካፍቴሪያ፣ የልጆች መጫወቻ ተሟልተውለት፣ ምቹ፣ ደረጃውን በጠበቀ እና ትውልዱንም በሚመጥን መንገድ አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ ገልፀውልናል፡፡

መዲናዋ ለኑሮም ይሁን ለመዝናናት ምቹ ያልሆነች፣ የልጆች መጫወቻ ስፍራ ያልነበሯት ነበረች፡፡ ይህንን ታሳቢ ያደረገ 104 ከኮሪደር ልማቱ ጋር የለሙና 22 ነባር ፓርኮች እንዳሉ የሚናገሩት ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚው፤ እነዚህ ፓርኮች የልጆች መጫወቻዎች ያሏቸው፣ የማህበረሰቡን አቅም ያገናዘቡ፣ ነዋሪዎች ራሳቸውን ከተፈጥሮ ጋር የሚያስተዋውቁባቸው፣ ንፁህ አየር የሚያገኙባቸው፣ ጭንቀታቸውን በማስወገድ ጤናቸውን የሚጠብቁባቸው፣ ጊዜያቸውን አልባሌ ቦታ እንዳያውሉ የሚያደርጉ ናቸው ሲሉ የሚሰጡትን ዘርፈ ብዙ ጥቅም አብራርተዋል፡፡

ፓርኮቹ በዘመናዊ መንገድ የለሙና ከተማዋን ውበት ያላበሱ፣ ምጣኔ ሃብቷንም የጨመሩ፣ አዲስ አበባ እውነትም የአፍሪካ መዲና፣ የተለያዩ የዲፕሎማቶች መቀመጫ መሆኗን ያረጋገጡ፣ ለነዋሪውም የመዝናናትን እድል የፈጠሩ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

አክለውም፤ በከተማዋ ያሉ ፓርኮች በዋጋ የማህበረሰቡን የኑሮ ደረጃ ያገናዘቡ፣ አንዳንዶቹም በነፃ ያለማንም ከልካይ እንዲዝናኑ የሚጋብዙ እንደሆኑ ገልፀው፤ እነዚህን መንግስት ብዙ ወጭ ያወጣባቸውን መዝናኛ ቦታዎች ማህበረሰቡ እንደራሱ ንብረት የመንከባከብ፣ የመጠበቅ ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ላይ እንዲውሉና በእጃቸው ያለውን ንብረት እንዲያውቁ የማድረግ ኃላፊነቱን እንዲወጣ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

# ልጆች፤ የጥምቀት በዓልን እንዴት ነው የምታከብሩት?

**በለይላ መሀመድ**

ልጆች፤ ጥምቀት በየዓመቱ ጥር 11 ቀን በሀገር ውስጥና በተለያዩ የውጭ ሀገራት በሚገኙ የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት የሚከበር የአደባባይ በዓል ነው። በዓሉ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ከጥር 10 ቀን ከተራ ጀምሮ በተለያዩ ስነ ስርዓቶች ይከበራል፡፡ የኃይማኖት አባቶች፣ ወጣቶች፣ ሴቶችና ሕፃናት እንደየችሎታቸውና ማዕረጋቸው በደመቀ ሁኔታ ለማክበር ተዘጋጅተው ነው ወደ አደባባይ የሚወጡት። ካህናት ታቦታቱን ከየመንበራቸው በማውጣት ወደተዘጋጀው ባህረ ጥምቀት ሲጓዙ፤ ወጣቶች በሆታና በዝማሬ እናቶች ደግሞ በእልልታና ጭብጨባ በማጀብ ያደምቃሉ።

የበዓሉ አከባበር ከዋናው የኃይማኖት መሰረታዊ ትርጉም ባሻገር በዓሉ ለሰው ልጆች ባህል፣ ኪነ ጥበብና ስነ ጥበብ ማደግ፣ በሕዝቦች መካከል ተፋቅሮና ተከባብሮ መኖር፣ ለገጽታ ግንባታነት እና ለቱሪስት መዳረሻነት ጠቀሜታው ብዙ ነው። ልጆች፤ ይህ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በታላቅ ድምቀት የሚከበረው በዓል በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ ሳይንስና ባህል ተቋም (ዩኔስኮ) ከተመዘገቡ የማይዳሰሱ ቅርሶች መካከልም አንዱ ነው፡፡


ፎቶ- ከፋይል
በጥምቀት በዓል ተግባራዊ ከሚደረጉ ክዋኔዎች አንዱ

ታዲያ ልጆች ይህ የጥምቀት በዓል ከኃይማኖታዊ አከባበሩም ባለፈ ብዙ ትዕይንት የሚታይበት ነው፡፡ ታቦታት ከሚነሱበት እስከሚያድሩበት ስፍራ ድረስ ረጅም ጉዞ ያደርጋሉ። በተጨማሪም ከጥምቀተ ባህሩ ጸበል ለመረጨት ሁሉም ይሽቀዳደማል፡፡ በዚህ ጊዜ ልጆች ከቤተሰቦቻችሁ ተለይታችሁ እንዳትጠፉና ሌሎች ተጨማሪ ማድረግ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች በተመለከተ የአንድን አባት ምክር እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል፡፡

አቶ አለማየሁ ተፈራ እባላለሁ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ ነዋሪ ነኝ፡፡ ልጆች በቅድሚያ እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ በሰላም አደረሳችሁ፡፡ የጥምቀት በዓል አይደለም እኛ ኢትዮጵያውያንን፤ የውጭ ሀገር ዜጎችም በልዩ ሁኔታ ያከብሩታል፡፡

በዓሉ በከተማችን አዲስ አበባ በተለያዩ ቦታዎች የሚከበር ሲሆን በጃንሜዳ በርካታ ታቦታት ያድራሉ፡፡ ሌሊቱን ሙሉ ማህሌትና ቅዳሴ ሲያደርጉ ካደሩ በኋላ ጠዋት ላይ ፓትርያሪኩ አሊያም ሊቀ ጳጳሱ ጥምቀተ ባህሩን ባርከው ወደ ህዝቡ በሚረጩበት ወቅት ትዕይንቱ ትልቅ ደስታን ይፈጥራል፡፡ ነገር ግን ልጆች ጸበል ሲረጭ እናንተ ከቤተሰብ ተለይታችሁ ወደ ውስጥ መግባት የለባችሁም፡፡ የጸበል መረጨት ሥነ ስርዓቱ የድህነትና የምህረት በመሆኑ ታላላቆቻችሁን ባከበረ መልኩ ማድረግ አለባችሁ፡፡

ይህ የጥምቀት በዓል ሰው የሚበዛበት እንደመሆኑ መጠን በተለይም በእድሜ ትንንሽ የሆናችሁ ልጆች የእናትና አባቶቻችሁን እጅ በመያዝ ነው መንቀሳቀስ ያለባችሁ፡፡ ጥምቀተ ባህሩ አካባቢ ጸበል ለመረጨትም ሆነ ሌሎች መርሀ ግብሮችን ለመከታተል መሀል ውስጥ ገብታችሁ እንዳትጠፉ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባችኋል። ልጆች፤ ሁልጊዜ ጨዋታ ሊያታልላችሁ አይገባም። የቤተሰቦቻችሁንና የታላላቆቻችሁን ምክር መቀበልና መተግበር አለባችሁ፡፡ ከጓደኞቻችሁ ጋር የመጣችሁ ልጆችም ብትሆኑ በዓሉን ስታከብሩ ከጓደኞቻችሁ ተለይታችሁ እንዳትጠፉ እርስ በእርሳችሁ እጅ ለእጅ ተያይዛችሁ መሆን አለበት፡፡

ልጆች ሌላው ጥንቃቄ ማድረግ ያለባችሁ ነገር መንገድ ላይ ያያችሁትን ነገር ሁሉ ግዙልን እያላችሁ ወላጆቻችሁን ማስጨነቅ፣ ራሳችሁንም ጤናችሁን ሊጎዱ የሚችሉ ምግቦችን ከመመገብ ልትቆጠቡ ይገባል፡፡

ብዙ የእግር ጉዞና እንቅስቃሴ ስለምታደርጉ ውሃ ሊጠማችሁ ይችላል። በዚህ ምክንያት ወላጆቻችሁን ያልተገባ ወጪ ከማስወጣት በምትኩ ከቤታችሁ በትምህርት ቤት ኮዳችሁ ወይንም በሌላ ለመያዝ በሚያመቻችሁ እቃ ይዛችሁ ብትወጡ ይመረጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጸሐይ እንዳይመታችሁ ኮፍያ ቢኖራችሁ ተመራጭ ነው፡፡

አዎ! ልጆች እንግዲህ በጥምቀት በዓል ገና ከቤት ወጥታችሁ ጥምቀቱን ወደ ማክበር ከመሄዳችሁ በፊት የወላጆቻችሁን ምክር ማዳመጥ ተገቢ ነው፡፡ ከሄዳችሁም በኋላ ምክራቸውን መተግበር ላይ ልትዘናጉ እንደማይገባችሁ ከወዲሁ ልነግራችሁ እወድዳለሁ፡፡ ልጆች መልካም በዓል ይሁንላችሁ፡፡

## 5 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**በሦስት እግሩ ቆሞ የሚፈነጥዝ**

**መልስ፦** ለ. ወጥ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**መሰላል ያላት ግን ሰው የማይወጣባት**

ሀ.ተልባ
ለ. ሽንበቆ
ሐ. ማሽላ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ።**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል የመንግስት አገልግሎት ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የአገልግሎት ልህቀት በአዲስ መሶብ

**በደረጀ ታደሰ**

ወይዘሮ መርያም ሲራጅ ይባላሉ። ወደ አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ዋና መሥሪያ ቤት መጥተው ነው ያገኘናቸው፡፡ የመጡበት ምክንያት መንጃ ፈቃድ ለማደስ ነው። አገልግሎቱን በፈጣንና ቀልጣፋ ሁኔታ በማግኘታቸው ተደስተዋል። ደስታቸውን ለብቻቸው ማጣጣም አልፈለጉም። የመንግስት አገልግሎትን በዚህ ደረጃ አዘምኖ፣ አቀላጥፎ፣ አፍጥኖ፣ ከእጅ ንክኪ አላቅቆ... እንዲቀርብ ያስቻለውን አካል ማመስገን እንዳለባቸው አምነዋል። አገልግሎት ባገኙበት ሕንፃ ወለል ላይ የተገልጋዮችን ግብረ-መልስ ለመቀበል ወደሚጠባበቁ ሙያተኞች አቀኑ። የተገልጋይን አስተያየት ለመሰብሰብ የተዘጋጀን መጠይቅ በታብሌት ላይ በመሙላትም ሃሳባቸውን ሰጡ፡፡

እኛም፤ ከታብሌቱ ጋር የነበራቸውን የተመስጦ መስተጋብር እንዳጠናቀቁ ስላገኙት አገልግሎት የተሰማቸውን ሃሳብ እንዲያጋሩን ጠየቅናቸው፡፡ ምላሻቸው አጭርና ግልፅ ሲሆን እንዲህ ነበር ያሉት፤ "ወደ ተቋሙ ስመጣ የገመትኩት ሌላ ነበር፡፡ ነገር ግን ግምቴ የተቀየረው ገና ወደ ቅጥር ግቢው ስገባ ነው፡፡ የሠራተኞቹ አቀባበል፣ ከቅጥረ ግቢው እስከ እያንዳንዱ የሕንፃው ወለል ያለው ውበት፣ ፅዳት እና ፀጥታው ልዩ ነበር። በመረጃ ሰጪዎች ድጋፍ ተራ መያዣ ትኬት ይዤ አገልግሎት ወደማገኝበት ክፍል አመራሁ፡፡ ወረፋ ስላልነበረ ወዲያው ተራዬ ደርሶ ተስተናገድኩ፡፡ በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ተገልግዬ አውቃለሁ፡፡ በዚህ ፍጥነት እና ቅልጥፍና አገልግሎት ያገኘሁበት ጊዜም፣ ቦታም የለም፡፡ በዚህ ያየሁት ግን እጅግ የሚያስደንቅ ነው፡፡ ይህ ጅምር በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ቢስፋፋ ምኞቴ ነው፡፡"

የወይዘሮ መርያምን አስተያየት ብዙዎች ይጋራሉ፡፡ ለዚህ ውጤታማነት ዘመኑን የዋጀ የሥራ አቀላጣፊ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጥቅም ላይ መዋላቸው ትልቁን ሥፍራ ይይዛል፡፡ "ለመሆኑ በተቋሙ በሥራ ላይ የዋሉ መሠረታዊ የሥራ ማቀላጠፊያ ቴክኖሎጂዎች ምን ምን ናቸው፣ ሚናቸውስ ምንድን ነው?" የሚሉ ጥያቄዎችን፤ በአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና የዲጂታላይዜሽንና የአንድ ማዕከል ዘርፍ ኃላፊ ለሆኑት አቶ ደረጀ አየለ አንስተንላቸዋል፡፡ እሳቸውም ለጥያቄዎቹ ምላሽ እና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

"መንግስት ትልቅ ትኩረት ከሰጣቸው ቁልፍ ተግባራት መካከል በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የመንግስት አገልግሎት በቴክኖሎጂ ማዘመን ነው፡፡ ለሥራው መሳካት ቁልፍ መሣሪያ ደግሞ ወቅቱን የዋጀ ቴክኖሎጂን በአግባቡ መጠቀም መቻል ነው" የሚሉት የዲጂታላይዜሽንና የአንድ ማዕከል ዘርፍ ኃላፊው፤ በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሃሳብ አመንጪነት፣ በከንቲባ አዳነች አቤቤ አመራር ሰጪነት



ፎቶ- በገነት ወንድሙ
ወይዘሮ መርያም ሲራጅ በማዕከሉ ስላገኙት አገልግሎት አስተያየት ሲሰጡ



ፎቶ- በገነት ወንድሙ
የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና የዲጂታላይዜሽንና የአንድ ማዕከል ዘርፍ ኃላፊ አቶ ደረጀ አየለ

በከተማ አስተዳደር ደረጃ የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎትን በማቋቋም ከጷጉሜን 5 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ፤ በከተማ አስተዳደር ስር ያሉ 13 ተቋማትን እንዲሁም 5 የፌደራል ተቋማትን በማካተት፣ በድምሩ ከ107 በላይ አገልግሎቶች በማስተሳሰር በአንድ ቦታ እየተሰጠ እንደሚገኝ አስታውሰዋል።

የዲጂታላይዜሽንና የአንድ ማዕከል ዘርፍ ኃላፊው አቶ ደረጀ እንደገለፁት፤ በማዕከሉ የሚሰጡ አገልግሎቶች ከብልሹ አሠራር የፀዱ፣ ተገልጋይን ያከበሩ፣ የሥራ ስነ ምግባርን የተከተሉ፣ ጊዜና ገንዘብን ያላባከኑ፣ በዋናነትም የተገልጋይን እርካታ ከፍ የሚያደርጉ በቴክኖሎጂ የተደገፉ ዘመናዊ የሥራ ማቀላጠፊያዎች ለምተው ለአገልግሎት በቅተዋል፡፡ እነዚህ ሲስተሞች የለሙት በኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ነው፡፡ ከቴክኖሎጂዎቹ አንዱ ኤፒአይ (Application Program Interface-API) ይባላል፡፡ ሲስተሙ በማዕከሉ አገልግሎታቸውን የሚሰጡ ተቋማትን አገልግሎቶች በአንድ ቦታ በማሰባሰብ፣ በማስተሳሰርና በማቀናጀት ለተገልጋዩ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል፡፡

ሌላኛው በማዕከሉ አገልግሎት ላይ የዋለው መተግበሪያ (ሲስተም) ኪው ማኔጅመንት ሲስተም (Q Management System-QMS) ይባላል፡፡ ይህ ሲስተም፤ ተገልጋዮች የሚፈልጉትን አገልግሎት በመምረጥ እና በመመዝገብ፣ ከማሽኑ የሚሰጠውን የወረፋ መጠበቂያ ቁጥር በመያዝ፣ በወረፋቸው አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቸ አሠራር ነው፡፡ ሲስተሙ ተገልጋዩ እንደ አመጣጡ ስለመገልገሉ፣ በምን ያክል ጊዜ ውስጥ አገልግሎቱን እንዳገኘ፣ በማን እንደተገለገለ፣ አገልግሎቱ በሙያዊ ስነ ምግባር ስለመከናወኑ እና የመሳሰሉ መረጃዎችን ለማጠናቀርና ለሚመለከተው የአመራር ቡድን ለማድረስ ያስችላል፡፡

የተገልጋይ እርካታ ግብረ-መልስ የሚሰበሰብበት (Feedback Collection System) በሦስተኛነት ሊጠቀስ የሚችል ቴክኖሎጂ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ደረጀ እንዳብራሩት ከሆነ፤ ተገልጋዩ አገልግሎቱን አግኝቶ እንደጨረሰ፣ ባገኘው አገልግሎት ምን ያክል እንደረካ ክትትል የሚደረግበት ዘመናዊ አሠራር ነው፡፡ ተገልጋዩ ስለአገልግሎቱ የተሰማውን አስተያየት መሰረታዊ በመጠይቆችን ከታብሌት ላይ በማንበብና በመሙላት ይሰጣል፡፡ ተግባሩን በተሳካ ሁኔታ ለመፈፀም የተመደቡ በጎ ፈቃደኞች ለተገልጋዮች ሲስተሙን በማሳወቅ እና እንዲጠቀሙ በማድረግ ድጋፍ ያደርጋሉ። በዚህ ሲስተም አማካኝነት፡- ምን ያክል ተገልጋይ አስተያየት እንደሰጠ፣ አስተያየቱ ምን እንደሆነ፣ የእርካታ መጠኑ (ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ) ምን ደረጃ ላይ እንደተቀመጠ... መረጃዎች ይሰበሰባሉ። የተጠናቀረው መረጃ በማዕከል ደረጃ ላሉ አመራሮች ይደርሳል፡፡ ለክፍተቶች ፈጣንና ተገቢ መፍትሄ ይሰጣል፡፡

የተሰበሰቡ የተገልጋይ እርካታ ግብረ-መልሶችን አጠናቅሮና ተንትኖ መረጃ የሚያቀርብ (Business Intelligence Analysis) አራተኛው ሲስተም ነው። ይህ ሲስተም የኪው ማኔጅመንት ሲስተም (Q Management System-QMS) እና የተገልጋይ እርካታ ግብረ-መልስ የሚሰበሰብበት (Feedback Collection System) መረጃዎችን በመጠቀምና በመተንተን ለአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ተጨባጭ መረጃዎችን የሚሰጥ ነው፡፡ በአዲስ መሶብ አገልግሎታቸውን ባቀረቡ እያንዳንዱ ተቋማት ምን ያክል አገልግሎት እንደተሰጠ፣ ስለ አገልግሎቶቹ ዓይነት፣ ስለተገልጋይ ብዛት፣ የአገልግሎት አፈፃፀም ውጤት ለማወቅ የሚያግዝ ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል፡፡ የተገልጋዮችን የእርካታ ደረጃንም በመረጃ ያሳውቃል፡፡

በአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ያሉ ተቋማዊ መሠረተ ልማቶች እና ግብዓቶች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን ሁኔታ እየተከታተለ ፈጣንና ትክክለኛ መረጃ የሚሰጠውን ሲስተም በአምስተኛነት የሚጠቀስ መሆኑን በመጠቆም፤ አገልግሎትን በተመለከተ የዲጂታላይዜሽንና የአንድ ማዕከል ዘርፍ ኃላፊው አብራርተዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ የአዲስ መሶብ የራሱ የሆነ የመረጃ ቋት (Data Center) አለው። በዚህ የመረጃ ቋት ውስጥ የሚገኙ ሰርቨሮች ተግባራቸውን በምን ሁኔታ እያከናወኑ እንደሆነ፣ ደህንነታቸው እና ተያያዥ መረጃዎችን እየተከታተለ የማሳወቅ ቁልፍ ሚናን የሚወጣው ይህ ሲስተም ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፤ በተቋሙ አገልግሎት ላይ የዋሉ ሌሎች ሲስተሞችን አጠቃላይ ሁኔታ (ምን ያክል ሥራዎችን እያከናወኑ ነው፣ ምን ያክል ስቶሬጅ ወይም መረጃ ማከማቻ እየተጠቀሙ ነው፣ ኔትወርኩ ምን ይመስላል...) የሚሉትን ጉዳዮች በተመለከተ ፈጣን እና ትክክለኛ መረጃ ያቀብላል፡፡

በስድስተኛነት የሚጠቀሰው፤ የሠው ኃይል መረጃን የሚይዝ ሲስተም (Human Resource System) ነው፡፡ ሲስተሙ፤ አንድ የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ሠራተኛ ከተቀጠረበት ጊዜ አንስቶ ያለውን ዝርዝር መረጃ የሚመዘገብበት፣ የሚደራጅበት እና የሚያዝበት ነው። አጠቃላይ የሠራተኛው መረጃ፣ የትምህርት ዝግጅቱ፣ የአገልግሎት ጊዜው፣ አሁን እየሠራበት ያለበት ክፍል፣ የፍቃድ አጠቃቀም እና የመሳሰሉ ዝርዝር መረጃዎች ይያዙበታል።

"በማዕከሉ ተገልጋዮች ምን ያክል ቅሬታዎች ቀረቡ፣ ቅሬታዎቹ ምንድን ናቸው፣ በየትኛው ተቋም ወይም አገልግሎት ላይ ቀረቡ፣ የታዩ ብልሹ አሠራሮች ምንድን ናቸው፣ በማንና በምን ምክንያት ተከሰቱ?... " የሚሉ ዝርዝር መረጃዎችን አጠናቅሮ ለሚመለከተው የአመራር አካል የሚያደርስ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ሲስተም ሌላኛው በአገልግሎት ላይ የዋለ ሲስተም ነው፡፡ የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ገፀ-ድር (Website) የተቋሙን አገልግሎት በማዘመን ሂደት ውስጥ የራሱን ሚና በመወጣት ላይ ያለ ሲስተም ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡

የቁጥጥር (ክትትል) እና ምዘና ሥራዎችን የሚከውን ሲስተም (Monitoring and Evaluation System) በአዲስ መሶብ በሥራ ላይ ካሉ ሲስተሞች መካከል የሚጠቀስ ነው፡፡ ይህ ሲስተም፤ የእያንዳንዱን ሠራተኛ የሥራ እንቅስቃሴ እና አፈፃፀም ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግበት ነው። ሠራተኛው በሥራ ሰዓት በሥራው ላይ መገኘት አለመገኘቱን፣ በሥራ ላይ ስለሰጠው አገልግሎት ብዛት፣ የፈቃድ አጠቃቀሙን፣ የሠጠው አገልግሎት ጥራት፣ የተነሳበት ቅሬታ ... የመሳሰሉትን መረጃዎች በማጠናቀር እና በመተንተን እያንዳንዱ ሠራተኛ በወር፣ በሩብ ዓመት፣ በስድስት ወር ወይም በዓመት ያለውን አፈፃፀም ያጠናቅራል፤ ሪፖርት ያወጣል፡፡

ሙሉ ለሙሉ የዲጂታል አገልግሎት በሚሰጥበት የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ተቋም አሁንም ተገልጋዮች የወረቀት ሰነዶችን ይዘው ይመጣሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ማዕከሉ ተገልጋዮች የያዙት ሰነድ የፈለጉትን አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችላቸው መሆኑን ካረጋገጠ፤ ሰነዳቸውን ስካን በማድረግ ወደ ዲጂታል መረጃነት ይቀይረዋል፡፡ ወደ መረጃ ቋትም ያስገባዋል፡፡ ከዚያም የሚፈልጉትን አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ ይህንን ተግባር የሚከውነው ሲስተም የዶክመንት ሼሪንግ ሲስተም (Document Sharing System) ይባላል፡፡

በማዕከሉ የውስጥ አቅም ለምቶ ጥቅም ላይ የዋለው የመሶብ አፕ (Mesob App) በአዲስ መሶብ ውስጥ በሥራ ላይ ከሚገኙ ሲስተሞች መካከል እንደሚካተት አቶ ደረጀ አንስተዋል፡፡ የሲስተሙን አገልግሎት በተመለከተ ሲያብራሩ፤ "በአዲስ መሶብ ውስጥ አገልግሎታቸውን እያቀረቡ ያሉ ተቋማት፤ በማዕከሉ የተቀናጀ አገልግሎት መስጫ ፕላትፎርም ላይ በሚኖራቸው የእርስ በእርስ ወይም የተናጠል እንቅስቃሴ ውስጥ (በቸልተኝነት፣ በሲስተም መቆራረጥ ወይም በሌላ ምክንያት) የሚፈጠርን መስተጓጎል በፍጥነት ለማሳወቅ እና የመፍትሄ እርምጃ ለመውሰድ እያገዘ የሚገኝ ሲስተም ነው "ብለዋል፡፡

በተጨማሪም፤ የሥራ ቦታ ደህንነትን ለመጠበቅ እንዲቻል፤ የአዲስ መሶብ ተቋም ሕንፃ ውስጣዊና ውጫዊ ክፍል በ360 ድግሪ ውስጥ ያለውን እንቅስቃሴ በካሜራ እየተከታተለ መረጃ የሚሰጥ ሲስተምም በአገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

"ከላይ የተጠቀሱት ሲስተሞች በተናጥል ወይም በተቀናጀ አግባብ ያልተቆራረጠ አገልግሎት እንዲሰጡ የኔትወርክ እና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ወሳኝ ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ የተዋጣላት ሥራ ተሠርቷል፡፡ የኔትወርክም ሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ እንዳይከሰት፤ በመሃል ቢከሰት እንኳን አንድም አገልግሎት ሳይቋረጥ የሚቀጥልበት አማራጭ በአዲስ መሶብ ተዘርግቷል" ያሉት የዲጂታላይዜሽንና የአንድ ማዕከል ዘርፍ ኃላፊው፤ በቀጣይ ከፀሐይ የኃይል ምንጭነት (Solar Energy System) ለመጠቀም በሂደት ላይ መሆኑን አንስተዋል፡፡ ደህንነቱ የተጠበቀ አገልግሎት ለመስጠት ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢንሳ) ጋር በቅንጅት እየሠራ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ራሱን የቻለ የሳይበር ደህንነት ክፍል አቋቁሞ ወደ ሥራ ማስገባቱንም አንስተዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የሰብል ብክነትን ለመከላከል ምን እየተሰራ ነው?

- **በአዲስ አበባ ከተማ በ2018 የምርት ዘመን 19 ሺህ 361 ነጥብ 63 ቶን የሰብል ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ እስከ ታህሳስ 30 ድረስ 18 ሺህ 620 ቶን ምርት መሰብሰብ መቻሉ ተገልጿል**

**በይግለጡ ጓዴ**

በግብርና ምርት አሰባሰብ ወቅት የሚከሰት ብክነት ለምግብ ዋስትና መረጋገጥ ትልቅ እንቅፋት ነው። ይህ ችግር በተለይ በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት በስፋት የሚታይ ሲሆን፣ ያደጉ ሀገራት ደግሞ በቴክኖሎጂ በመታገዝ ብክነቱን ወደ ዝቅተኛ ደረጃ ማውረድ ችለዋል። በተባበሩት መንግስታት የግብርና እና የምግብ ድርጅት (ፋኦ) መረጃ መሰረት፣ በዓለም ላይ ከሚመረተው ምግብ ውስጥ ሲሶው ወይም አንድ ሶስተኛው በብክነት ምክንያት ጥቅም ላይ አይውልም።

በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ብክነቱ የሚከሰተው ገና ምርቱ ማሳ ላይ እያለ፣ በመሰብሰብ ሂደት፣ በውቂያ እና በማከማቸት ወቅት ነው። ይህም በቴክኖሎጂ እጥረት፣ በመሰረተ ልማት በተለይም በመንገድ አለመሟላት እና በደካማ የማከማቻ ዘዴዎች ምክንያት ነው። እስራኤል፣ ኔዘርላንድስ እና ቬትናም የምርት ብክነትን ለመቀነስ በምሳሌነት የሚጠቀሱ ስኬቶችን ስለማስመዝገባቸው ከፋኦ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡

በሰብል አሰባሰብ ወቅት የሚፈጠር ብክነት ኢትዮጵያንም አብዝቶ የሚያሳስባት ችግር ነው፡፡ ለመሆኑ አሁን አሁን በስፋት እየተለመደ የመጣው የከተማ ግብርና ስራ ከዚህ ችግር የፀዳ እንዲሆን ምን መሰራት አለበት? የሚለውን ነጥብ በዚህ ፅሑፍ እናመላክታለን፡፡

በቦሌ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት የእጽዋት ልማት ቡድን መሪ ወይዘሮ ህይወት በለጠ በ2018 በክፍለ ከተማው 1 ሺህ 213 አርሶ አደሮች በመኸር እርሻ ተሳታፊ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በጥቅሉ 1 ሺህ 8 ሄክታር መሬት በሰብል መሸፈኑን ገልጸዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ህይወት ገለፃ፣ ምርትና ምርታማነትን ከሚጨምሩ ጉዳዮች አንዱ የግብዓት አቅርቦት ነው፡፡ በዚህም 2 ሺህ 420 ኩንታል ማዳበሪያ እና ዩሪያ፣ 328 ኩንታል የጤፍ እና የስንዴ የምርጥ ዘር በወቅቱ በማቅረብ አርሶ አደሮች ምርትና ምርታማነታቸውን እንዲጨምሩ ማድረግ ተችሏል፡፡

ወይዘሮ ህይወት በብተና ከመዝራት ይልቅ በመስመር ሲዘራ የሚዘራው ዘር፣ በጥቅም ላይ የሚውለው ግብዓት መጠኑ በብተና ሲዘራ ከነበረው በጣም የቀነሰ ነው፡፡ በመስመር ሲዘራ የተሻለ ምርትና ምርታማነት ይሰጣል፡፡ ይህም ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር አንዱ አጋዥ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በክፍለ ከተማው ዘርን በመስመር የመዝራት አሰራርን ባህል ለማድረግ ቻይና ኤይድ (China AID) ከተባለ አንድ የቻይና ድርጅት ጋር በጋራ በመሆን የመስመር መዝሪያ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በክፍለ ከተማ 100 ሞዴል አርሶ አደሮች ምርጥ ዘርን በመስመር እንዲዘሩ መደረጉን አስታውቀዋል፡፡ የአረም ቁጥጥር እና የተባይ ቁጥጥርን በጠበቀ መንገድ ለአርሶ አደሮች ድጋፍ እንደሚያደርጉ ቡድን መሪዋ ገልጸው፣ ከተዘራ በኋላ የአረም ቁጥጥር ካልተደረገ የተለያዩ ጸረ ተባይ እና ጸረ በሽታ መከላከያ መድኃኒቶችን በመጠቀም ተባይ መከላከል ተችሏል፡፡ ብክነትን በመቀነስ ምርትና ምርታማነትን በአግባቡ ማሳደግ የሚቻለው እነዚህን መድሐኒቶች በአግባቡ መጠቀም ሲቻል መሆኑን ይናገራሉ፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

በሰብል አሰባሰብ ወቅት የሚከሰትን የምርት ብክነት ለመከላከል የቴክኖሎጂ ድጋፍ ከፍተኛ ነው





እንደ ወይዘሮ ህይወት ገለጻ፣ ምርትን ከብክነት ለማዳን በተቻለ መጠን ምርትን በወቅቱ እንዲሰበስቡ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ የሞዴል አርሶ አደሮች እና የአቅመ ደካማ አርሶ አደሮች ላይ ትኩረት በማድረግ ምርታቸው በዝናብ እንዳይበላሽ፣ የሰብል መሰብሰቢያ ጊዜው አልፎ ምርት እንዳይረግፍ በወረዳ 11 እና ወረዳ 12 የበጎ ፈቃደኛ ወጣቶችን በማስተባበር ሰብል በወቅቱ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

ለአቅመ ደካማ አርሶ አደሮች የማዕከል፣ የክፍለ ከተማ እና ወረዳ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ሰራተኞችን በማስተባበር የአጨዳ ስራ ተሰርቷል፡፡ አቅም ያላቸው አርሶ አደሮችን የማጨጃ ማሽን በመከራየት በወቅቱ በማጨድ ምርታቸውን እንዲሰበሰቡ ማድረግም ተችሏል፡፡ ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ በስንዴ እና በጤፍ የሰብል ምርታማነትን ለማሳደግ ተችሏል፡፡ በ2018 የምርት ዘመን 3 ሺህ 18 ነጥብ 6 ቶን ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

> **“በሰብል ስብሰባ ወቅት የሚከሰትን የምርት ብክነት ለመቀነስ አርሶ አደሩ አስቀድሞ በቂ ዝግጅት ማድረግ ችሏል። ለምርት መሰብሰብና ማከማቸት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን በሚገባ ማዘጋጀቱ ደግሞ የምርት ብክነት መጠን እንዲቀንስ አግዟል”**

በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርናልማት ጽህፈት ቤት የእጽዋት ባለሙያ አቶ ፈለቀ ሞገስ በክፍለ ከተማው በመኸር ሰብል በእርሻ ሥራ 160 አርሶ አደሮች መሳተፋቸውን ጠቁመው፣ 236 ነጥብ 375 ሄክታር መሬት በስንዴ፣ ጤፍ፣ ገብስና በቆሎ ሰብሎች መሸፈኑን ተናግረዋል፡፡

በክፍለ ከተማ በ2017/18 ምርት ዘመን 222 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ እና ዩርያ እንዲሁም 34 ነጥብ 38 ኩንታል ምርጥ ዘር እና 59 ኩንታል 93 ነጥብ 38 ኩንታል የአካባቢ ዘር ጥቅም ላይ መዋሉን ገልጸዋል፡፡

አቶ ፈለቀ በመኸር ሰብል ምርት ዘመን የተሳተፉ አርሶ አደሮች ከባለፉት ዓመታት በተሻለ ሁኔታ በወቅቱ የእርሻ ሥራ መጀመራቸው፣ የእርሻ ድግግሞሽ ከአራት እስከ አምስት ዙር መታረሱ፣ ግብዓትን በወቅቱ ከአዲስ አበባና ከኦሮሚያ ክልል በመግዛት ለአርሶ አደሩ ማድረስ በመቻሉ እና የተፈጥሮ ማዳበሪያም በጥቅም ላይ እንዲውል በመደረጉ የተሻለ ውጤት ለማግኘት ያስችላል የሚል ግምት መያዙን ጠቁመዋል፡፡

በተጨማሪም የአረም ቁጥጥር ሥራ በወቅቱ መካሄዱ፤ አርሶ አደሮች የባለሙያ ምክር በመረዳታቸው፣ የመኸር ሰብል ሥራን ከነቤተሰቦቻቸው በትኩረት በመስራታቸው ለምርት እድገት አቅም ይሆናልም ብለዋል፡፡ በክፍለ ከተማው ለመኸር እርሻ በቂ ትኩረት በመሰጠቱ ካለፈው ዓመት የምርት ዘመን ከተገኘው ምርት የ2017/18 የምርት ዘመን በ13 ነጥብ 89 በመቶ እድገት እንደሚያሳይ ተመላክቷል፡፡

በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ በ2018 የምርት ዘመን 8 ሺህ 169 ነጠብ 75 ኩንታል የሰብል ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የእጽዋት ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት ተወካይ ዳይሬክተር አቶ ሲሳይ እንሴኔ፣ በከተማዋ በ2018 የምርት ዘመን 7 ሺህ 165 ሄክታር መሬት በሰብል መሸፈኑን ጠቁመዋል፡፡ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር ግብዓት ምርጥ ዘር በወቅቱ ማሰራጨት መቻሉን እና ለ850 አርሶ አደሮች እና ለ56 ባለሙያዎች ግንዛቤ መፍጠር መቻሉን አክለው ተናግረዋል፡፡

የምርት ብክነት እንዳይኖር በኮምባይነር መሰብሰብ መቻሉን ገልጸው፣ አርሶ አደሮች በደቦ በጋራ የሰብል ምርት የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል። በከተማዋ እንደ ለሚ ኩራ፣ ቦሌ፣ አቃቂ ቃሊቲ፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ፣ የካ፣ ኮልፌ ቃራኒዮ ያሉ የማስፋፊያ ክፍለ ከተሞች ሰፋፊ የእርሻ ስራ በማከናወን በሰብል ምርት በመሸፈን ሰብልን በወቅቱ በመሰብሰብ ከምርት ብክነት መታደግ መቻሉን ተወካይ ዳይሬክተሩ ይገልጻሉ፡፡

በከተማዋ በ2018 የምርት ዘመን 19 ሺህ 361 ነጥብ 63 ቶን የሰብል ምርት ለመሰብሰብ ታቅዷል፡፡ እስከ ባለፈው ወር ታህሳስ 30 ድረስ 18 ሺህ 620 ቶን ምርት በአግባቡ በመሰብሰብ ከምርት ብክነት መታደግ መቻሉን ጠቁመዋል፡፡

በሰብል ስብሰባ ወቅት የሚከሰትን የምርት ብክነት ለመቀነስ አርሶ አደሩ አስቀድሞ በቂ ዝግጅት ማድረግ ችሏል፡፡ ለምርት መሰብሰብና ማከማቸት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን (ማጨጃ መሳሪያዎች፣ ሸራ፣ ከረጢት፣ ጊዜያዊ የመከመሪያና ማድረቂያ ቦታዎች ወዘተ) በሚገባ አዘጋጅቷል፡፡ ይህም የብክነት መጠኑ እንዲቀንስ አግዟል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ወንዞችን ከብክለት የመታደግ ፋይዳ

- **የኮሪደር፣ የወንዝ እና ወንዝ ዳርቻ ልማት ወንዞች ወደ ተፈጥሯዊ ማንነታቸው እንዲመለሱ በማድረግ ረገድ አይተኬ ሚና እንዳላቸው ተጠቁሟል**

**በለይላ መሀመድ**

ከተሞችና ወንዞች የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ናቸው ማለት ይቻላል። የበርካታ ከተሞች ምስረታ፣ እድገትና ስልጣኔ ወንዝና የወንዝ ዳርቻዎችን ተከትሎ እንደሆነ የዓለም የከተሞች ታሪክ ያሳያል፡፡ ንጽህናው የተጠበቀ የከተማ ወንዝ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የወንዝ ዳርቻው ለመዝናኛነት፣ ለከተማ ግብርና፣ ለመዋኛ፣ ለንጽህና መጠበቂያ፣ አረንጓዴ የከተማ ማዕከላት ለመፍጠር ያገለግላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በወንዝ አካባቢ የሚኖሩትን የተፈጥሮ ሥነ-ህይወታዊ አካላትን (ዓሳና ሌሎችንም የውሃ ውስጥ እንስሳትና ዕጽዋት) ለማቆየትና ለማስቀጠል አስፈላጊ እንደሆነ በአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ዳይሬክተር አቶ ለሜሳ ጉደታ ያብራራሉ፡፡

ወንዞች ለከተሞች የውበት፣ የመዝናኛና የሀብት ምንጭ በመሆን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው ቢሆኑም በተለያዩ ምክንያቶች ተበክለው ይታያሉ። ለመሆኑ የወንዝ ብክለት ሲባል ምን ማለት ነው? የወንዝ ብክለት መንስኤ፣ የሚያስከትለው አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ እንዴት ያለ ነው? ከብክለት መጠበቅስ ምን ጥቅም ያስገኛል? የሚለውን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

የወንዝ ብክለት ማለት ወንዙ ጎጂ በሆኑ ንጥረ ነገሮች ለምሳሌ በኬሚካል ወይም ረቂቅ ተህዋሲያን ሲበከል ወይም ውሃው የተፈጥሮ ይዘቱን በማጣት ለሰውና ለአካባቢ ጥቅም የማይሰጥበት ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ 76 ወንዞች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ወንዞች ብክለት አጋጥሟቸው ቆይቷል። 76ቱም ወንዞች ወደ ትንሹ እና ትልቁ የአቃቂ ወንዝ ይገባሉ፡፡ ከዚያም አባ ሳሙኤል ግድብ በመገናኘት በታችኛው ተፋሰስ ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው የተበከለ ውሃ እንዲኖር ማድረጋቸውን አቶ ለሜሳ ይናገራሉ፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ ወንዞቹ እንዲበከሉ ያደረጓቸው ምክንያቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ ምንጫቸው የሚታወቅ (point source) አንዱ ምክንያት ነው፡፡ ፋብሪካዎች፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ መኖሪያ ቤቶች፣ የኃይል ማመንጫዎች፣ የማዕድን ማውጫዎች ወዘተ የውሃ ብክለት ምንጮች ናቸው:: ምንጫቸው የማይታወቅ (None point source) ለወንዞች መበከል ሌላው ምክንያት ነው። ይህም በጎርፍ አማካኝነት ከተለያየ ቦታ በካይ ነገሮች ወደ ወንዝ ይገባሉ፡፡ ግብርና ከሚካሄድባቸው አካባቢዎች ለምሳሌ የከብቶች አዛባ እና የዶሮ ኩስ በአግባቡ ካልተወገደ በጎርፍ አማካኝነት ወደ ወንዝ የሚገባበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡ ሌላው አትክልት በሚሸጥባቸው ስፍራዎች የአትክልቶቹ ተረፈ ምርትና የተበላሸው ክፍል ባለበት ስለሚጣልና ስለሚበሰብስ ይህም በጎርፍ አማካኝነት ወደ ወንዝ ይገባል፡፡


ፎቶ- ከገፀ ድር
በአዲስ አበባ ወንዞችን ከብክለት የጸዱ ለማድረግ በተሰራው ስራ ተጨባጭ ውጤት እየተመዘገበ ነው

እ.ኤ.አ በ2019 የዓለም ባንክ ያወጣውን መረጃ በመጥቀስ ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት፣ በዓመት በአዲስ አበባ በውሃ ብክለት ምክንያት በሚከሰት ተቅማጥ 467 ሰዎች ህይወታቸውን ያጣሉ፡፡ 5 ሺህ 467 ሰዎች ይታመማሉ። ከዚህ በተጨማሪ በተበከለ ውሃ ሽታ 57 ሰዎች የሚሞቱ ሲሆን 219 ሰዎች ደግሞ ይታመማሉ፡፡ በውሃ ወለድ ነፍሳት የሚከሰተው የሞት መጠን 35 ሲሆን በህመም የመያዝ መጠን 781 ነው፡፡ በዓለም በከተሞች ላይ የሚገኙ አብዛኞቹ ወንዞች የፍሳሽ ሽታ የተለመደ ሲሆን በዋናነት በኢንዱስትሪ ዞኖች ውስጥ የሚገኙት ከመጠን በላይ የተበከሉ ናቸው፡፡ በአፍሪካና በኢትዮጵያ ከተሞች ከኢንዱስትሪዎች፣ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ ከመኖሪያ ቤቶች እና ከሌሎች ምንጮች በሚወጣ የተበከለ ፍሳሽ ሳቢያ ወንዞች ይበከላሉ፡፡

የኢትዮጵያ ርዕሰ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ የህዝብ ቁጥር መጨመርና የከተማ መስፋፋት ለአካባቢ ብክለት እንድትጋለጥ አድርጓት ቆይቷል። በአዲስ አበባ የሚገኙት ወንዞች በከተማው ውስጥ የሚለቀቁትን ሁሉንም ዓይነት ቆሻሻዎች መቀበያ ሆነው ቆይተዋል፡፡ 65 በመቶ የሚሆኑ የሀገሪቱ ኢንዱስትሪዎች የሚገኙባት ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት ያለ ተገቢ ህክምና ቆሻሻቸውን በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ ወንዝ ይለቅቃሉ። በዚህም ወንዞች እንዲበከሉ አድርጓል፡፡

ዳይሬክተር አቶ ለሜሳ እንደሚገልጹት፤ በ2016 ዓ.ም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በወንዞች ላይ ጥናት አካሂዷል፡፡ ጥናቱ ከወንዞቹ ናሙና በመውሰድ ያደረገው ጥናት በውሃ አካላት ውስጥ በካይ ንጥረ ነገሮችና ኬሚካሎች እንዲሁም ባክቴሪያዎች ከላይኛው የተፋሰስ አካባቢ ጀምሮ በከተማ ሲያልፉና ወደ ታችኛው ተፋሰስ ሲጓዙ የብክለት መጠናቸው እየጨመረ እንደሚሄድ አመላክቷል፡፡ ውሃው የደፈረሰ ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቶቹ በጎርፍ ተጠርጎ የሚመጣው አፈርና ቆሻሻ፣ ከመኖሪያ ቤት፣ ከተቋማትና ኢንዱስትሪዎች የሚለቀቁ ፍሳሾች ወደ ወንዝ በመግባታቸው ነው፡፡ አሁን ላይ ይህ ችግር የሚታየው የኮሪደር ልማት እና የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ልማት ባልተካሄደባቸው ወንዞች ላይ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረው የንፅህና አጠባበቅ እና የቆሻሻ አያያዝ ጉድለት ከፍተኛ የአካባቢ ብክለትን በማምጣት የጤና፣ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ሲያስከትል ቆይቷል። የዚህ ችግር ዋና መንስኤው አገልግሎት የሚሰጡ ደረጃቸውን የጠበቁ የፍሳሽ ማስወገጃ መሰረተ ልማቶች በበቂ ሁኔታ አለመኖሩ እንደሆነ የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ዳይሬክትር አቶ ለሜሳ ያስረዳሉ፡፡ ከሚያስከትላቸው ችግሮች የሚከተሉትን በማሳያነት ገልጸዋል

## የወንዝ ብክለት የሚያስከትለው አካባቢያዊ ችግር

የገጸ ምድር እና የከርሰ ምድር ውሃ እርስ በርስ በቅርበት የተሳሰሩ እንደመሆናቸው መጠን ፍሳሽ ወደ ከርሰምድር ውሃ ይሰርጋል። በዚህም በከርሰ ምድር እና በገጸ ምድር ውሃ ላይ የሚደርሰው የብክለት አደጋ እየተስፋፋ እንዲመጣ አድርጎታል፡፡ ይህም በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እጽዋትና እንስሳት ዝርያዎች እንዲጠፉ ያደርጋል፡፡

እንደ ዳይሬክተር አቶ ለሜሳ ገለጻ፤ የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር የ2011 ዓ.ም ያወጣው ሪፖርት እንደሚያሳየው፣ ኢንዱስትሪዎች እየተስፋፉ በመጡበት አካባቢ፣ ያልተጣራ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ በመወገዱ ምክንያት ብክለት እየጨመረ መጥቷል፡፡ ይህም ወንዞች አልፎ ተርፎም አካባቢው እንዲበከል በማድረግ የነዋሪውን የኑሮ የጥራት ደረጃ ይቀንሳል፤ ከተማዋ ለውጭ ባለሀብቶች ያላትን ስበት እና የቱሪዝም ተወዳዳሪነት ያሳጣታል።

## የወንዝ ብክለት የሚያስከትለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር

የወንዝ ብክለት የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ያስከትላል፡፡ ከእነዚህ መካከል በታችኛው ተፋሰስ የበካይ ተበካይ ተቃርኖ መኖር፣ ለቤተሰብ ፍጆታ የንጹህ ውሃ አቅርቦት ማነስ እና ፍላጎትን ለማሟላት ተጨማሪ ወጪ መጋለጥ፣ ለግብርና ምርት ሊውል የነበረውን የውሃ ጥራት ማሳጣት፣ ወንዞችና የከርሰ ምድር ውሃ ለማከም የሚወጣ ወጭ ጫና መኖር፣ የጤና ወጪ መጨመር፣ ከቱሪዝምና ከመዝናኛ አገልግሎት የሚገኘውን ገቢ ማሳጣት፣ የምርት ጥራትና መጠን መቀነስ የሚሉት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ወንዞችን ለማጽዳት ወይም ወደ ነበረበት ለመመለስ ከፍተኛ ወጪ መጠየቁ ሌላው ኢኮኖሚያዊ ችግር ሲሆን በተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን እ.ኤ.አ 2019 በተደረገ ጥናት በወንዝ ብክለት ምክንያት በአዲስ አበባ ሊገኝ የነበረን 66 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዶላር ገቢ እንዳሳጣን ያመለክታል፡፡

## የጤና ችግር

በወንዝ ብክለት ምክንያት ከሚመጡ የጤና ችግሮች መካከል ለኮሌራ፣ ታይፎይድ፣ ኢንፌክሽን፣ ተቅማጥ እና ለውሃ ወለድ በሽታ አምጪ ተህዋሲያን መጋለጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በተጨማሪም የተበከለ ወንዝ መድኃኒትን ለተላመዱ ባክቴሪያ፣ ቫይረስና ፈንገሶች ያጋልጣል፡፡ የምግብ ሰንሰለት እንዲበከል ያደርጋል፡፡ ይህ ማለት በተበከለ ወንዝ አትክልት ሲመረት ከፍተኛ መጠን ያላቸው ከባድ ብረቶች ክምችት በውስጣቸው እንዲገኝ ያደርጋል፡፡ ይህ በምግብ ሰንሰለት አማካኝነት ወደ ሰው አካል ውስጥ በመግባት የህብረተሰብ ጤናን ይጎዳሉ። አርሰኒክ ንጥረ ነገር በውሃ ውስጥ መብዛት ለጨጓራ፣ ለቆዳ እና ለነርቭ ጉዳት እንዲሁም ካንሰር በሽታዎች ተጋላጭ ያደርጋል፡፡ የካዲየም ንጥረ ነገር መብዛት የጨጓራ፣ የኩላሊት እና የሳንባ ጉዳት እንዲሁም በሜርኩሪ ምክንያት የአንጎል እና የኩላሊት ጉዳት እና በኒኬል ንጥረ ነገር መብዛት ምክንያት ደግሞ የሳንባ፣ የአንጎል፣ የኩላሊት እና የካንሰር በሽታዎች ይከሰታሉ፡፡

## መፍትሔው ምንድን ነው?

የከተማ ወንዞችን ከብክለት አደጋ ለመታደግ ውሃን በቁጠባ መጠቀም፣ የኬሚካል አጠቃቀምን መቀነስ፣ ለማህበረሰቡ ስለወንዝ ጥቅም እና አስፈላጊነት ግንዛቤ መፍጠር፣ ለበካይ አምራችና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ደረጃቸውን የጠበቀ የፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያ እንዲኖራቸው ማስገደድ፣ በወንዝ ልማት ሥራዎች ላይ መንግሥት፤ መንግስታዊ ያልሆኑና የግል ባለሀብቶችን ማሳተፍ እና ከፕላስቲክ ነፃ የሆኑ ምርቶችን ማምረት ያስፈልጋል፡፡ ወንዞችን ከብክለት ለመከላከል ጠንካራ የአካባቢ ህጎችን ማውጣትና መተግበር፣ የፍሳሽ ማስወገጃ መሠረተ ልማትን ተደራሽ ማድረግ፣ ፍሳሻቸውን ከመንገድ ዳር ያገናኙ መኖሪያዎችና ተቋማት ከዚያ በሙሉ እንዲያላቅቁ ማድረግ፣ የወንዝ ዳርቻ ልማቱን ቀጣይነት ማጠናከር፣ ደረጃውን የጠበቀ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ መስራት እና የወንዞች ብክለት ሁኔታ ላይ የተለያዩ ጥናቶችን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማስጠናት የወንዝና ወንዝ ዳርቻ ልማት ባልተካሄደባቸው ወንዞች ላይ ተጨማሪ መፍትሔ ማፈላለግ እንደሚያስፈልግ የሚገልጹት ዳይሬክተሩ፣ በአሁኑ ወቅት መንግስት ተግባራዊ ባደረገው የኮሪደር ልማት እና የወንዝ እና ወንዝ ዳርቻ ልማት ወንዞች ወደተፈጥሯዊ ማንነታቸው መመለሳቸውን አብራርተዋል፡፡

## ከባለድርሻ አካላት ምን ይጠበቃል?

በቀጣይ በወንዞችና ወንዝ ዳርቻዎች ብክለት በሚያስከትሉ አካላት ላይ ህብረተሰቡ ለሚመለከተው አካል ጥቆማ በመስጠት እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ መሳተፍ ይኖርበታል፡፡ በከተማው የሚገኙ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በምርት ሂደት የሚፈጠረውን ተረፈ ምርት ወይም ውጋጅ ቆሻሻ በአግባቡ አክሞ መልሶ ጥቅም ላይ እንዲያውል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የትኛውም በከተማው ውስጥ የሚገኝ ነዋሪ ከሽንት ቤት የሚወጣውን ፍሳሽ በአግባቡና ህጉ በሚፈቅደው መልኩ ማስወገድ ወይም በከተማው የሚገኝ የሽንት ቤት ፍሳሽ መስመር ማገናኘት ይኖርበታል፡፡ የመንግስት፣ የግል፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የልማት ድርጅቶች አካባቢን ከብክለት ለመከላከልና የተፈጥሮ ሃብትን መንከባከብ የስራቸው አንዱ አካል አድርገው ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ በከተማ ደረጃ በሚካሄዱ የመንገድ ላይ ትዕይንቶች፣ ፌስቲቫሎች፣ ህዝባዊ በዓላት ላይ ስለወንዝ ብክለት አስከፊነት ግንዛቤውን ማሳደግ የወንዝ ብክለትን በመከላከል ረገድ ቁልፍ ሚና እንደሚጫዎት አቶ ለሜሳ አብራርተዋል።

## የአብሮነት... ከገጽ 6 የዞረ

እንደ ኢትዮጵያ ላለ ህብረ ብሔራዊ ሀገር እንደነዚህ አይነት በዓላት እንደ መከባበር፣ ልግስና እና ሰላም ያሉ የጋራ እሴቶችን የሚያጎሉ በመሆናቸው በባህል መካከል ውይይት እና የጋራ መግባባትን ያበረታታሉ። በተጨማሪም እነዚህ ክስተቶች ብዙውን ጊዜ የበጎ አድራጎት ተግባራትን እና የጋራ ድጋፍን ያካትታሉ፣ ለምሳሌ ምግብን ለድሆች ማጋራት ወይም ማጽዳት እንዲሁም የህዝብ ቦታዎችን ማዘጋጀት፣ ይህም በሰዎች መካከል መተማመንን እና አብሮነትን እንደሚፈጥሩ ያስረዳሉ፡፡

### በበዓላት ቀናት ከሚታየው ባሻገር

እንደ ጥምቀት ባሉ በዓላት የሚታዩትን የአብሮነትና የአንድነት እሴቶች ከበዓላት ባሻገር ቀጣይነት እንዲኖራቸው የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት ወሳኝ እንደሆነ የማህበረሰብ ሳይንስ ባለሙያው አቶ ዘላለም ይናገራሉ። "ለምን ብናኝ አታከልም፤ እያንዳንዳችን ኃላፊነታችንን መወጣት ከቻልን በዓልን ተገን አድርገን የምናሳያቸው በጎ ባህሎች ሀገራዊና ተቋማዊ ይዘት እንዲኖራቸው ከማስቻል አኳያ ትልቅ አስተዋፅኦ አላቸው" ይላሉ፡፡

የማህበረሰብ ሳይንስ ባለሙያው አቶ ዘላለም እንደሚናገሩት፣ እያንዳንዳችን የሚጠበቅብንን ኃላፊነት መወጣት ከቻልን እንደሀገርም ሆነ ማህበረሰብ የችግር ጊዜያችን ማሳጠር ይቻላል፡፡ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የተለያዩ ችግሮች አሉብን፡፡ ችግሮቻችንን ይፈታሉ ብለን የምናምንባቸው ምግባሮች ወይም እሴቶች በእለት ተለት ሕይወታችን የምንጠቀምባቸውና ዘላቂ እንዲሆኑ ኃላፊነትን መውጣትና ምላሽ መስጠት አለብን፡፡

እንደ ጥምቀት ባሉ በዓላት ላይ የሚታዩትን የአንድነት እና አብሮነት እሴቶች ቀጣይነት እንዲኖራቸው በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ስለ ኢትዮጵያ የተለያዩ ባህሎች እና ወጎች አስተምህሮዎች ማካተትና ማስተማር እንደሚገባ ዘሪሁን (ዶ/ር) ያነሳሉ፡፡

ሌላው የሃይማኖቶች እና የባህል ውይይቶችን ማበረታታት ያስፈልጋል። የተደራጁ መድረኮች እና ከተለያየ አስተዳደግ የተውጣጡ ሰዎችን የሚያቀራርቡ ዝግጅቶች፣ በህዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር እና ጭፍን ጥላቻን ለመቀነስ ይረዳል።

የማህበረሰብ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ መተግበርም ሌላው በህዝቦች መካከል አንድነትን፣ መረዳዳትና አብሮነትን ለማጠናከር ያግዛል፡፡ የጋራ ጥረት እና የድጋፍ መንፈስን ለማስቀጠል እንደ የጽዳት ዘመቻዎች ወይም የበጎ አድራጎት ዝግጅቶች ያሉ የትብብር ተነሳሽነቶች በመደበኛነት መደራጀት እንዳለባቸው ዘሪሁን (ዶ/ር) ያነሳሉ፡፡

ዘሪሁን (ዶ/ር) እንደሚያስረዱት፣ መገናኛ ብዙሃንም አንድነትን፣ መረዳዳትና አብሮነትን በማጎልበት ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ በዚህ ረገድም የሚዲያ ተቋማት የአብሮነት እና የአንድነት ታሪኮችን ጎልተው እንዲወጡ በማድረግ፤ ሌሎች በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው እነዚህን ልማዶች እንዲኮርጁ በማነሳሳት ቁልፍ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ።

በየደረጃው ያሉ መሪዎችም ማህበረሰቡ ሀይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ እሴቶቻቸውን በተግባራቸው እና በመልእክቶቻቸው በንቃት ማስተዋወቅ እና አርአያ ማድረግ አለባቸው፡፡ ይህም በበዓላት ወቅት የተመሰከረው የአንድነት መንፈስ ቀጣይ እና የህብረተሰብ ህይወት ወሳኝ አካል እንዲሆን እንደሚያስችል ነው የማህበራዊ ሳይንስ ምሁሩ ዘሪሁን (ዶ/ር) የሚያስረዱት፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርን፣ አንድነትን፣ ትህትናን፣ ፍቅርን፣ ከምንም በላይ የራቁትን ማቅረብ፣ የወደቁትን ማንሳትን ነው ያስተማረን ያሉት መምህር ለይኩን፣ የራቀን ሰው ካለ ልክ ኢየሱስ ክርስቶስ ዝቅ ብሎ ሰውን ከውድቀት እንዳወጣውና ከፍ እንዳደረገው ሁሉ እኛም ክብር ልንሰጥ፣ ፍቅርና አንድነታችንም ልናጠናክር ይገባል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

አባ አብርሃም በበኩላቸው፣ የተለያየ እምነት የምንከተል ብንሆንም እግዚአብሔር የፈጠረን ሰዎች መሆናችን አንድ ያደርገናል። የጥምቀት በዓል ሁሉም በመንፈስም፤ በስጋም አብሮ በማክበር የሚደሰትበት፣ አንድነቱን የሚገልፅበትና ኢትዮጵያዊነት የሚታይበት በዓል ነው፡፡ እነዚህን መልካም የሆኑ እሴቶች ከበዓል ባሻገር በዕለት ተለት ህይወት ማሳየት እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

በበዓላት የሚታየውን የአብሮነትና አንድነት እሴት ለማስቀጠል፣ የአንዱ መኖር ለሌላው መኖርና ማደግ ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ፣ አብሮነታችንን ለማጠናከር መስራት ይኖርብናል፡፡ አብሮነትን ለመሸርሸር የሚመጣ ሲኖር ደግሞ በጋራ መታገል እንደሚገባ አቶ ሚስባህ ተናግረዋል፡፡

# ማስታወቂያ

አቶ አንዱአለም ልንገርህ ካሳ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000061007265770002 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በ ጎሹ ጌታሁን ወ/ጊዮርጊስ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦሌ10/17/6/3/52162/00 የሴሪ ቁጥር 017438 የተሰጠበት ቀን 05/03/09 የቦታው ስፋት በሰነድ 450 ሜ.ካ በሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና በ ጎሹ ጌታሁን ወ/ጊዮርጊስ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦሌ10/17/6/3/52162/00 የሴሪ ቁጥር 017438 የተሰጠበት ቀን 05/03/09 የቦታው ስፋት በሰነድ 450 ሜ.ካ በሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ከእጃችን የጠፋ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማናት አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 04 በካርታ ቁጥር 015954 በሴሪ ቁጥር 030996 በመሳይ ስሜ ነጋ ስም የተመዘገበ የኮንዶሚንየም ቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቻምየለሽ በላይ መንግስቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 11 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር AA000081105896130003 በሴሪ ቁጥሩ 142100 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ / ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ዮቴክ ኮንስትራክሺን ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 02 የሚገኘው የይዞታ ካርታ ቁጥር ድ207/98/28761/01 በሴሪ ቁጥሩ 017217 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ሃይለገብርኤል መዝገበ ግደይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 የካርታ ቁጥር ቦ/አራ/11/88/8/3/13917/00 ሴሪ ቁጥር 1434142 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 በሴሪ ቁጥር R 063509 በይዞታ መለያ ቁጥር AA000010701778 በእነ ወ/ሮ ወርቅአገኘሁ ገብረእግዚአብሔር (5 ሰዎች) ስም በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የተሰጣቸው የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) የጠፋብን በመሆኑ ምትክ ይሰጠን በማለት ያመለከቱ በመሆኑ ይኸው የይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) በእኔ እጅ ይገኛል ይዤዋለሁ የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በአየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 1381/2017 አንቀፅ 36(3) መሰረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አራዳ ክፍለ ከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ቅ/ጽ/ቤት በመቅረብ እንዲያመለክት ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአራዳ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በህዋ ገላን ያዴሳ ስም ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በስም በልደታ ክ/ማ ወረዳ በቀድሞ 12፣ ቀበሌ 11 በአዲሱ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 1152፣ የካርታ ቁጥር ል.02/5/6002/11745/01፣ ሴሪ ቁጥር 0631857 የተመዘገበ ይዞታ ካርታ ጠፋብኝ ብለው በቀን 21/04/18 ዓ.ም በማመልከቻ የጠየቁ ስለሆነ፣ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመቻ ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳይ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**ጉዳዩ፡- የደረሰኝ መጥፋት ማሳወቅ**

በአዲስ አበባ ከተማ የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር አዲስ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN)0046031477 የሚታወቀው በላይነሽ መጨከኑ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት አ/አ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ያልተሰራበት የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር 051 እስከ 100 ስለጠፋብን በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራበት እና የጠፋ መሆኑ የሶስተኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው አ/አ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያ የሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም፡- በላይነሽ መጨከኑ**

# ለሁለተኛ ጊዜ የወጣ ግልፅ ጨረታ

**በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 አስተዳደር ፅ/ቤት ስር ላሉት ፅ/ቤቶች በ2018 ዓ.ም በጀት አመት በሁለተኛ ግልፅ ጨረታ የሚያስፈልጋቸውን**

**ሎት1-** የደንብ ልብስ ግዥ - የጨረታ ማስከበሪያ CPO 5000 ብር

**ሎት2-**የፅህፈት መሳርያ- የጨረታ ማስከበሪያ CPO 2000 ብር

**ሎት3-** የፅዳት እቃዎች ግዥ- የጨረታ ማስከበሪያ CPO 2000ብር

**ሎት4-** ደንብ ልብስ ስፌት አገልግሎት - የጨረታ ማስከበሪያ CPO 5000 ብር

**ሎት5-** የመኪና ጎማ እና የተለያዩ እቃዎች - ማስከበርያ CPO 30000

**ሎት6-**የትራንስፖርት አገልግሎት - የጨረታ ማስከበርያ CPO 5000

**ሎት7-**የኤሎክትሮኒክስ ቆዋሚ እቃ ጥገና ግዥ - የጨረታ ማስከበሪያ CPO 10000

ብቃት ያላቸውና በመስኩ የተሰማሩ ተጫራቾችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል በዚህም መሰረት፡-

1. በጨረታው ለመወዳደር ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣ በመንግስት ግ/ን/አስ/ኤጀንሲ ድረ ገፅ ላይ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ፣ የቲን እና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ (ሲፒኦ) በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 ፋይናንስ ፅ/ቤት ስም ከላይ በተጠቀሰው አግባብ ከጨረታው ሰነዳቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. ተጫራቾች ጨረታው በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ አዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት እለት(ቀን) አንስቶ በተከታታይ 10 የስራ ቀናት የማይመለስ 200 ብር (ሁለት መቶ ብር ) በመክፈል በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ1 4ኛ ፎቅ የመንግስት ግዥ ክፍል በመምጣት የጨረታ ሰነዱን መግዛት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዳቸውን በታሸገ ፖስታ ማስታወቂያ ከወጣበት እለት ጀምሮ እስከ 10ኛው ቀን ድረስ ለወረዳው ፅ/ቤት 4ኛ ፎቅ ግ/የ/ሂደት ክፍል ለጨረታው በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ10ኛው ቀን በ10፡30 ሰዓት ታሽጎ በ11ኛው ቀን በ3፡00 ሰዓት በወረዳው 4ኛ ፎቅ የመንግስት ግዥ ክፍል ውስጥ ይከፈታል፡፡

   የመክፈቻ ቀኑ የበአል/ የእረፍት ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ታሽጎ ይከፈታል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ሳጥን ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩባቸው ሎት 1፣ ሎት 2 እና ሎት 3 ናሙና ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን እናሳዉቃለን።
7. ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸው እቃዎችና አገልግሎት፤ ለእያንዳንዱ ከቫት ውጭና ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡
8. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸው እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈፃሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
9. ተጫራቾች የጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅት ከሆኑ መጫረት የሚችሉት በተደራጁበት ምርት ውጤት ብቻ ሲሆን እንዲሁም ከአደራጃቸው አካል የሚጫረቱበትን እቃ ማቅረብ እደሚችሉ ማረጋገጫ ደብዳቤ ማያያዝ ይኖርባቸዋል፡
10. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**<u>ለተጨማሪ ማብራሪያ</u>**

**ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 1 ፋ/ፅ/ቤት ስልክ ቁጥር 0115547832**

**አድራሻ፡- ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 1 አስተዳደር መስከረም 1 ት/ቤት ፊት ለፊት ፣**

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በልደታ ክ/ከተማ የወረዳ 1 ፋ/ፅ/ቤት

# የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

## የግዢ ጨረታ ማስታወቂያ መለያ ቁጥር 002/2018

በቦሌ ክ/ከተማ አስተዳደር የቦሌ ቡልቡላ ወረዳ 12 ጤና ጣቢያ ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት፡-

ሎት1. የደንብ ልብስ፣ ሎት4. ቋሚ እቃዎች (ኤሌክትሮኒክስ)፣ ሎት5. ልዩ ልዩ /አላቂ የቢሮ እቃዎች/፣

ሎት7. መድሃኒት፣ ሪኤጀንት እና የህክምና መገልገያ እቃዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

በዚህ መሰረት ጨረታውን ለመሳተፍ የሚፈልጉ ህጋዊ ተጫራቾች የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

1. ተጨራቾች በዘርፉ የተሰማሩበትን ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር ለመክፈላቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
2. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በአቅራቢነት የተመዘገበና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
3. የታደሰ የንግድ ፍቃድ ያለው፣
4. ተጫራቾች ናሙና ለተጠየቁባቸው እቃዎች ናሙናውን ቀድመው ጨረታ ሰነዱ ሣጥን ውስጥ ከማስገባታቸው በፊት ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. ተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል እንዲሁም ካሽ ሪጅስተር ያለው ብቻ
6. የህክምና መሳሪያዎች (እቃዎች) ተጫራቾች ሰነድ ለመግዛት ስትመጡ የህክምና መሳሪያዎች አቅራቢ መሆናችሁን የሚያረጋግጥ EFDA ይዘዉ መቅረብ አለባቸው፡፡
7. ተጫራቾች ከዚህ በታች የተጠቀሰውን የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ C.P.O ብቻ ማቅረብ አለባቸው፡፡

| ሎት ቁጥር | የሎት ዝርዝር | የተጠየቀው የጨረታ ማስከበሪያ |
|---|---|---|
| ሎት 1. | የደንብ ልብስ ግዥ | የኢትዮ.ብር 5,000 |
| ሎት 3. | የፅዳት እቃዎች | የኢትዮ.ብር 5,000 |
| ሎት 4. | ቋሚ እቃዎች (ኤሌክትሮኒክስ) | የኢትዮ.ብር 15,000 |
| ሎት 5. | ልዩ ልዩ /አላቂ የቢሮ እቃዎች | የኢትዮ.ብር 3,000 |
| ሎት 7. | መድሃኒት፣ ሪኤጀንትና የህክምና መገልገያ እቃዎች | የኢትዮ.ብር 20,000 |

8. የጨረታ ሰነዱን ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በየሎቱ የማይመለስ ብር 200.00/ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል የተዘጋጀውን ሰነድ ከተቋሙ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 404 /እየቀረቡ መግዛት ይቻላል።
9. ተጫራቾች ጨረታ ከወጣበት ቀን አንስቶ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 409 ድረስ በመምጣት ዋጋው የተሞላበትን የጨረታ ሰነድ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ ለየብቻው በማሸግ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
10. የህክምና መገልገያ እቃዎች ላይ የእቃዉን መግለጫ ካታሎግ በማያያዝ በ3 /በሶስት/ ፖስታ ቴክኒካል ኦርጅናል ለብቻ ፋይናሽያል ኦርጅናል ለብቻ እና ፋይናሽያል ኮፒ በማለት ማስገባት አለባቸው፡፡
11. ጨረታው በ10ኛው ቀን 10፡30 ሠዓት ታሽጎ በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 3፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ የጨረታ መዝጊያና መክፈቻ የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተጠቀሰው ተመሳሳይ ሠዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
12. ተጫራቾች ያሸነፉበትን ዋና የውል ማስከበሪያ 10% ማስያዝ አለባቸው፡፡
13. ተጫራቾች ጨረታ ለሚወዳደሩባቸው ቋሚ ዕቃዎች መስሪያ ቤቱ ባቀረበው ስፔስፊኬሽን መሰረት ማቅረብ አለባቸው፡፡ ስፔስፊኬሽን ላይ የድርጅታቸውን ማህተም ፊርማ መኖር አለበት፡፡
14. የጨረታ አሸናፊ ድርጅት ያሸነፉበትን ዕቃ በራሱ ትራንስፖርት ንብረት ክፍል ድረስ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
15. መ/ቤቱ ለጨረታ ከቀረበው ዕቃ እስከ 20% የመቀነስም ሆነ የመጨመር መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
16. መ/ቤቱ የተሻ ለአማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
17. ተጫራቾች በሰነዳቸው ስማቸውን እና ሙሉ አድራሻቸውን በትክክል መሙላትና በማህተም መረጋገጥ አለበት፡፡

**አድራሻ**

**ስልክ 09-86-38-96-18/0118 88 01 28 በቦሌ ክፍከ ከተማ አስተዳደር የቦሌ ቡልቡላ ወረዳ 12 ጤና ጣቢያ ከማርያም ማዞሪያ 100 ሜ ገባ ብሎ**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቦሌ ክ/ከተማ አስተዳደር የቦሌ ቡልቡላ ወረዳ 12 ጤና ጣቢያ**

---

በኢዛና ካልአዩ ብሩክ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ለ/ኩ/9/4/8/27/152760/00 የሴሪ ቁጥር 1672252 የተሰጠበት ቀን 19/09/2015 የቤቱ ስፋት በሰነድ 61.00 ሜ.ካ በሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና በኢዛና ካልአዩ ብሩክ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ለ/ኩ/9/4/8/27/152760/00 የሴሪ ቁጥር 1672252 የተሰጠበት ቀን 19/09/2015 የቤቱ ስፋት በሰነድ 61.00 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ከእጃቸው የጠፉ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ20 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ20 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ15/60/4/22/56688/00 ሴሪ ቁጥር 151728 በአቶ ማይክ ካሳዬ አዴሎ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንደሚንየም ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ ከ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በወ/ሮ ዘይነባ መሀመድ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ቦ/አያ/18/2983/01 የሴሪ ቁጥር 042450 የተሰጠበት ቀን 6/11/2001 ዓ.ም የቦታው ስፋት በሰነድ 63.51 ካ.ሜ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲፃፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት በወ/ሮ ዘይነባ መሀመድ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ቦ/አያ/18/2983/01 የሴሪ ቁጥር 042450 የተሰጠበት ቀን 6/11/2001 ዓ.ም የቦታው ስፋት በሰነድ 63.51 ካ.ሜ የቦታው የሆነው የኮንዶሚኒየም ማረጋገጫ ካርታ ኦርጅናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማናት አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር W9/9–193-300-9193/02 ሴሪ ቁጥር 070039 በአቶ ዘውዱ መኮንን ወ/ሳሙኤል ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት(ካርታ) የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 27/04/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 13 ቀበሌ 08 በአዲሱ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር G-B5-2(03) በእህተ ደግፌ ቅጣው ስም የወጣው ቁጥሩ አ/13/14/01/2003 ሴሪ ቁጥር 000025 በቀን 17/8/1999 ዓ.ም ወጪ የሆነ ኦርጂናል ካርታ ስለጠፋባቸው በምትኩ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው 01/05/2018 በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡

በመሆኑም የጠየቁትን አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አራዳ ክ/ከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ካልቀረቡ ግን የጠየቁትን አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ተደራጅቶ የሚገኘው የኮፊ ሲቲ ባጃጆች ባለንብረት ኃ/የተ/ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበር በአደረገው ጠቅላላ ጉባዔ ማህበሩ እንዲፈርስ በሙሉ ድምፅ የተወሰነ በመሆኑ ይህን የማህበሩ መፍረስ የሚቃወም ወይም ይገባኛል የሚል አካል ካለ በአንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 92 መሰረት ጋዜጣውን አየር ላይ ከዋለ ጀምሮ በ2 ወራት ውስጥ ተቃውሞውን በአካል በመቅረብ ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ህብረት ስራ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 505 እንዲያቀርብ እየገለፅን በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ንብረት የመጠየቅ መብት የሌለው መሆኑን በመግለፅ ጥሪ እናስተላልፋለን፡፡

**በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ህብረት ሥራ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 01 ክልል ውስጥ በካርታ ቁጥር በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070104425/12 በሴሪ ቁጥር 016189 በወሰኑ አህመድ ዳምጠው ስም የተመዘገበው የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የአህጉራዊው ውድድር አይረሴ ክስተቶች

**በሳህሉ ብርሃኑ**

በአፍሪካ ፀረ-ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ ውስጥ ስመ ጥር ከሆኑት ታጋዮች አንዱ የነበረው ፓትሪስ ሉሙምባ ለሳምንታት ሲከናወን በቆየው የአፍሪካ ዋንጫ ላይ በአካልም ባይሆን በመንፈስ በስታዲየም ታድሟል፡፡ የአፍሪካ የነፃነት ተጋድሎ ምልክት ብቻ ሳይሆን፣ በስፖርቱ ዓለም በተለይም በአፍሪካ ዋንጫ ታሪክ ውስጥ የማይረሳ አሻራ ጥሎ ያለፈው መሪ በአህጉሪቱ የእግር ኳስ ድግስ ላይ መነጋገሪያ ያደረገው ክስተት ተፈጥሯል፡፡

ነገሩ እንዲህ ነው በ35ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ስታዲየሞች በሺዎች የሚቆጠሩ ደጋፊዎች ሲዘፍኑና ሲጨፍሩ፣ አንድ የኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ደጋፊ ግን ለየት ባለ ሁኔታ ትኩረት ስቧል። ይህ ሰው ሚሼል ኩካ ምቦላዲንጋ ይባላል፤ ነገር ግን አሁን መላው አፍሪካ ‘ሉሙምባ ቬያ’ በሚል ቅጽል ስሙ ያውቀዋል። ደጋፊው ሙሉ የጨዋታ ክፍለ ጊዜ ቀኝ እጁን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ ልክ በኪንሻሳ እንደሚገኘው የሉሙምባ ሃውልት በስታዲየም ያስመለከተበት ሁነት በብዙዎች ህሊና ውስጥ ተቀርፆ ቀርቷል። በሞሮኮ የተገኙ የእግር ኳስ ደጋፊዎችም ለአፍሪካ ነውስ በሰጡት አስተያየት 35ተኛውን የአፍሪካ ዋንጫ ከሚሼል ኩካ ምቦላዲንጋን ውጪ ማሰብ አንችልም ሲሉ ተደምጠዋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር
35ኛው የአፍሪካ ዋንጫ በታሪክ ከፍተኛ የተመልካች ቁጥር የተመዘገበበት ውድድር በመሆን አዲስ ታሪክ ፅፏል

ይህንን ጨምሮ ያለፉት ቀናት በሰሜን አፍሪካዊቷ ሀገር ሞሮኮ ሰማይ ስር፣ በአፍሪካ ዋንጫው ክራሞት አስደሳች፣ አነጋጋሪ እንደዚሁም በደስታና በሀዘን፣ በሽንፈትና ቁጭት መካከል የሚዋልሉ ታሪኮችን ሲሰንዱ ከርመዋል። የሞሮኮው የአፍሪካ ዋንጫ መድረክ የጀመረው በ24 ቡድኖች አጀብ ቢሆንም፣ አሁን ግን መጋረጃው ሊዘጋ ጥቂት ሲቀረው መድረኩ ላይ የቀሩት ሁለት ‘ተዋናዮች’ ብቻ ናቸው። በዚህ ጽሑፍም 35ተኛውን የአፍሪካ ዋንጫ ለየት ያሉ ክስተቶች ከብዙ በጥቂቱ አንዳስሳለን፡፡

ነገ መቋጫውን የሚያገኘው የአፍሪካ ዋንጫ፣ ገና ፍፃሜው ሳይደርስ በታሪክ ከፍተኛው የተመልካች ቁጥር የተመዘገበበት ውድድር በመሆን አዲስ ታሪክ ፅፏል። ውድድሩን ለማጠናቀቅ ሶስት ጨዋታዎች እየቀሩት፣ በወጣው መረጃ መሰረት 1 ሚሊዮን 116 ሺህ 950 ተመልካቾች በስታዲየም ተገኝተው ጨዋታዎቹን ታድመዋል። ይህም በአህጉሪቱ የእግር ኳስ ታሪክ ከፍተኛው የተመልካች ቁጥር ሆኖ ስለመመዝገቡ የካፍ መረጃ ያሳያል።

ለዚህ አስደናቂ ቁጥር መመዝገብ በዋናነት የሞሮኮ ዘመናዊ ስታዲየሞች እና በከፍተኛ ቴክኖሎጂ የታገዙና ለተመልካች ምቹ የሆኑ መሠረተ ልማቶች ይጠቀሳሉ። እንደዚሁም ውድድሩ በዲጂታል አማራጮችና በቴሌቪዥን ቀጥታ ስርጭት በመላው ዓለም ከ2 ነጥብ 5 ቢሊዮን በላይ ሰዎች እየተከታተሉት የሚገኝ ሲሆን፣ ይህም የውድድሩን ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ከፍ ስለማድረጉ የኦሎምፒክስ ዶት ኮም መረጃ ያትታል።

ወደሌላኛው የውድድሩ አስገራሚ አጋጣሚ ስናመራ የምናገኘው የቡርኪና ፋሶው የመስመር ተጫዋች ጆርጂ ሚኖንጎን ይሆናል፡፡ በምድብ መጀመርያ ጨዋታዎች 12 ጨዋታዎች ተደርገዋል። በእነዚህ 12 ጨዋታዎች ታዲያ የበርካቶችን ቀልብ ስቦ የነበረው የቡርኪና ፋሶው የመስመር ተጫዋች ጆርጂ ሚኖንጎ ነው፡፡ የ23 ዓመቱ ተጫዋች የተወለደው በኮትዲቯር ባቲብሊ ዶብሊ ይሁን እንጂ ለብሔራዊ ቡድን መጫወትን የመረጠው ግን ለቡርኪና ፋሶ ነው፡፡ እግር ኳሱን በተወለደባት ኮትዲቯር በልጅነቱ የጀመረው ጆርጂ ሚኖንጎ ከሁለት ዓመት በፊት በስፔን ልምምድ ላይ እያለ ድንገት በገጠመው የዐይን ህመም ብዙ ውጣ ውረዶችን አይቷል፡፡

በወቅቱ ወደ ጤና ተቋም ካመራ በኋላ የቀዶ ጥገና ህክምና ቢደረግለትም የገጠመው የዐይን ኢንፌክሽን ታክሞ የሚድን እንዳልሆነ እና ማየት የማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱ ይነገረዋል፡፡ በተጨማሪም የህክምና ባለሙያዎች ዳግም ወደ እግር ኳስ መመለስ እንደማይችልም አሳውቀውታል። ለእግር ኳስ የተለየ ፍቅር ያለው ጆርጂ ሚኖንጎ ምንም እንኳን አንድ ዐይኑን ቢያጣም መጫወትን ግን አላቆመም፡፡ ከቀደመው በተለየ መልኩ ልምምዱን አጠናክሮ በመቀጠል የተዋጣለት ተጫዋች መሆኑንም አስመሰከረ፡፡ በቼክ ሪፑብሊክ እና በአሜሪካ ሜጀር ሊግ ሶከር የመጫወት ዕድል ያገኘው ጆርጂ ሚኖንጎ በአፍሪካ ዋንጫ ቡርኪና ፋሶ ከመመራት ተነስታ ኢኳቶሪያል ጊኒን 2 ለ 1 ባሸነፈችበት ጨዋታ ሀገሩን ቀዳሚ ያደረገችውን ወሳኝ ግብ አስቆጥሯል፡፡

የወቅቱ የሲያትል ሳውንደርስ የመስመር አጥቂ ስለሁኔታው ሲናገር “አይነስውር መሆኔ የተቃራኒ ቡድን ተከላካዮችን ለማየት ፈታኝ ቢሆንብኝም በሂደት ነገሮችን የመረዳት ዕድል አግኝቻለሁ” ብሏል፡፡ በሞሮኮ አፍሪካ ዋንጫ ገና ከጅምሩ ስሙን በደማቅ የጻፈው የ23 ዓመቱ ጆርጂ ሚኖንጎ ሌላ ታሪክ መስራትን ያልማል፡፡

ዶሚኒጌዝ ፔሌምቤ፣ ዴኒስ ኦንያንጎ፣ ፒየር ኤምሪክ አባምያንግ፣ ኢድሪሳ ጋና ጊየ እና ብሩኖ ኢኩውሌ ማንጋ ዕድሜ ከቁጥርነት ያለፈ ትርጉም እንደሌለው ማሳያ የሆኑ አንጋፋ ተጫዋቾች ናቸው።

የ42 ዓመቱ ሞዛምቢካዊ አማካይ ዶሚኒጌዝ ፔሌምቤ የውድድሩ አንጋፋው ተጫዋች ነው። ሞዛምቢክ በኮትዲቯር 1 ለ 0 በተረታችበት የምድብ የመጀመሪያ ጨዋታ ዶሚኒጌዝ በሁለተኛው አጋማሽ ተቀይሮ ገብቶ ተጫውቷል። በሞዛምቢክ ማሊያ መጫወት ከጀመረ 22 ዓመታት ተቆጥረዋል። የቀድሞ የሱፐር ስፖርት ዩናይትድ፣ ማሚሎዲ ሰንዳውንስ እና ቢድቬስት ዊትስ አማካይ በዚህ ጊዜ ለሀገሩ ክለብ ዩዲ ሶንጎ እየተጫወተ ይገኛል።

የ40 ዓመቱ ዩጋንዳዊ ግብ ጠባቂ ዴኒስ ኦንያንጎ በአፍሪካ ዋንጫው የተሳተፈ ሌላኛው አንጋፋ ተጫዋች ነው። ኦንያንጎ ከዚህ ቀደም ዩጋንዳን በ2017 እና በ2019 የአፍሪካ ዋንጫ ውድድሮች በአምበልነት መርቷል። ከአራት ዓመት በፊት ጓንት መስቀሉን ይፋ አድርጎ የነበረ ቢሆንም ውሳኔውን ቀልብሶ ዳግም ወደ ብሔራዊ ቡድኑ ተመልሷል።

ዴኒስ ኦንያንጎ በክለብ ደረጃ ለቅዱስ ጊዮርጊስና ማሚሎዲ ሰንዳውንስ ተጫውቷል። የ37 ዓመቱ ጋቦናዊ ተከላካይ ብሩኖ ኢኩሌ ማንጋ በአፍሪካ ዋንጫው የተጫወተ ሌላኛው አንጋፋ ተጫዋች ነው። ማንጋ ከአውሮፓውያኑ 2006 ጀምሮ በመድረኩ እየተጫወተ ይገኛል። ሞዛምቢካዊው ተከላካይ ሜክሰርም 37 ዓመት ሞልቶታል። ጋቦናዊው ፒየር ኤምሪክ ኦባምያንግ እና ሴኔጋላዊው ኢድሪሳ ጋና ጊየ ደግሞ 36 ዓመት ከደፈኑ በኋላ በአፍሪካ ዋንጫው የተጫወቱ ናቸው።

በአፍሪካ ዋንጫው በርካታ ተጫዋቾች በብቃታቸው ጎልተው የወጡ ሲሆን፣ ሞሮኳዊው የሪያል ማድሪድ ኮከብ ብራሂም ዲያዝ የውድድሩ ኮከብ እንደሚሆን ብዙዎች ግምታቸውን ከወዲሁ ሰጥተውታል፡፡ ዲያዝ የሞሮኮ ብሔራዊ ቡድንን ለመወከል በወሰነው ውሳኔ መሰረት ለመጀመሪያ ጊዜ በዋንጫው ላይ በመሳተፍ አስገራሚ ታሪክ እየሰራ ይገኛል። በ5 ጨዋታዎች ውስጥ 5 ጎሎችን በማስቆጠር የውድድሩ ከፍተኛ ጎል አግቢ ሆኖ እየመራ ነው። ዲያዝ በሜዳ ላይ ያለው ፍጥነትና የኳስ ቁጥጥር (Dribbling) ብቻ ሳይሆን፣ ወሳኝ በሆኑ ሰዓታት ጎል የመፍጠር ብቃቱ የሞሮኮን የማጥቃት መስመር እጅግ አስፈሪ አድርጎታል።

ናይጄሪያው አዴሞላ ሉክማን እንደዚሁ በውድድሩ የደመቀው ሌላኛው ኮከብ ሲሆን፣ ባለፈው የውድድር ዓመት በክለቡ አታላንታ ካሳየው ድንቅ ብቃት በኋላ፣ በዘንድሮው የአፍሪካ ዋንጫ ላይም የናይጄሪያ የድል ቁልፍ ሆኖ ቀጥሏል። በምድብ ጨዋታዎች 4 ለጎል የሚሆኑ ኳሶችን በማመቻቸትና 3 ጎሎችን በማስቆጠር ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳርፏል። በምድብ ጨዋታዎች ማጠቃለያ ላይ በካፍ ምርጥ 11 ውስጥ የተካተተ ብቸኛው ናይጄሪያዊ ተጫዋች ሆኗል።

እስካሁን ባለው ሂደት 4 ጎሎችን ያስቆጠረው ግብጻዊው ሞሐመድ ሳላህ፣ በተከላካይ መስመር ላይ ሆኖ በጨዋታ በአማካይ 3 ነጥብ 5 ግልጽ የጎል ዕድሎችን በመፍጠር ቀዳሚው የሆነው አሽራፍ ሀኪሚ እና ሳይቆጠሩባቸው የቀሩ ግቦችን (Expected Goals Prevented - xG Prevented) በተመለከተ ከፍተኛውን ደረጃ የያዘው የደቡብ አፍሪካው ግብ ጠባቂ ሮንዌን ዊሊያምስም አስደናቂ ብቃታቸውን ካሳዩ ተጫዋቾች መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የአፍሪካ ዋንጫው እስካሁን ባለው ሂደት እጅግ አስገራሚ የሆኑ ቁጥራዊ መረጃዎችን እያስተናገደም ይገኛል። ውድድሩ የጎል ድግስ፣ ያልተጠበቁ ውጤቶችና አዳዲስ ታሪኮች የተመዘገቡበት ሆኗል። በአንድ ጨዋታ 2 ነጥብ 85 ጎሎች ሲመዘገቡ ይህ ውድድር ካለፉት 10 ዓመታት የውድድር ታሪክ ከፍተኛው የጎል አማካይ የተመዘገበበትና በምድብ ጨዋታዎች ብቻ ከ90 በላይ ጎሎች የተቆጠሩበት ስለመሆኑም የ‘ኦፐታ’ (Opta) መረጃ ያሳያል፡፡ እንደዚሁም በሞሮኮ እና ታንዛኒያ ብሔራዊ ቡድኖች መካከል በተደረገው የምድብ የመክፈቻ ጨዋታ ላይ በ18ኛው ሰከንድ ላይ የተቆጠረው ፈጣኑ ጎል በውድድሩ ታሪክ ካለፉት ፈጣን ጎሎች ተርታ የሚመደብ ሲሆን፣ ይህም ደጋፊው ገና ወንበሩ ላይ ሳይደላደል ስታዲየሙን ያስገረመ ክስተት ሆኖ አልፏል።

‘ኦፐታ’ን (Opta) ዋቢ አድርገን ስንቀጥል ሌሎች አስገራሚ መረጃዎችን እናገኛለን። በዚሁ መሰረት የአፍሪካ ዋንጫ ላይ የቪዲዮ ረዳት ዳኛ (VAR) በሁሉም ጨዋታዎች ላይ ጥቅም ላይ እየዋለ ሲሆን፣ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ያለው ስህተት ካለፈው ውድድር በ15 በመቶ ቀንሷል። የሴኔጋል ብሔራዊ ቡድን አማካይ አማዱ ኮናቴ 17 ዓመት በውድድሩ ላይ የተሳተፈው ትንሹ ተጫዋች ሲሆን፣ ይህ ወጣት በውድድሩ ላይ ጎል በማስቆጠርም አዲስ ታሪክ ጽፏል። ከፍተኛ ጎል አግቢው ብራሂም ዲያዝ በምድብ ጨዋታዎች ብቻ ያስቆጠራቸው የጎል ብዛት 5 ሲሆን፣ ይህም የወርቅ ጫማውን ፉክክር እጅግ አጓጊ አድርጎታል።

በአጠቃላይ፣ በሞሮኮ ምድር የተስተናገደው 35ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ከእግር ኳስ ውድድርነቱ ባሻገር፣ አህጉሪቱ ያላትን የስፖርት መሰረተ ልማት ግንባታ ብስለትና የተጫዋቾቿን ታክቲካዊ እድገት ለዓለም ያስመሰከረበት ታላቅ መድረክ ሆኖ ተጠናቋል። የሞሮኮው ድግስ በነገው ዕለት ፍጻሜውን ቢያገኝም፣ በስታዲየሞቹ የታየው ስሜትና በኦፐታ መረጃዎች የተመዘገበው የታሪክ አሻራ ግን በአፍሪካ የእግር ኳስ ማህደር ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሲታወስ ይኖራል። አሁን ጥያቄው በውድድሩ የታየውን ይህን የላቀ ደረጃ በቀጣይ ውድድሮች እንዴት ማስቀጠል ይገባል? የሚለው ሆኗል።